# የሞት ጉዞ

## እውነተኛ እና አሳዛኝ ታሪክ

በግሩም ተ/ሀይማኖት

© መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው

ALL RIGHTS RESERVED

የመጀመሪያ እትም ሰኔ 2006ዓ.ም ታተመ

**ለአስተያየትዎ**

ፖ.ሳ.ቁጥር፡-11773 ሰነዓ-የመን

**ኢሜል**...girum_tekl@yahoo.com

Girum18@gmail.com

**ሚጢጢ ማሳሰቢያ**

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ የተካተቱትን ፍሬ ሀሳቦች፣ ታሪኮች በጋዜጣ፣ በመጽሔት፣ በሬድዮና በሌሎች የመገናኛ ብዙሀን የሚያሰራጭ ማንኛውም ወገን ያገኘበት ምንጩን ማለት የመጽሐፉን ርዕስ ወይም የጸሀፊውን ስም መግለጽ ይኖርበታል፡፡

በእጅ ከመጻፍ ጀምሮ ኮምፒዩተር ላይ ለቀማ፣ እርማት፣ የውስጥ ገጽ ዲዛይን፣ የፊት ገጽ (ሽፋን) ዲዛይን..የመሳሰሉትን ሁሉ ግድ ስለሆነብኝ በራሴ መወጣት መቻሌ ኩራት ሆኖኛል፡፡ ትኩረት ሰጥቼ ሥነ-ጽሁፋዊ ውበቱን እንዲጠብቅ ለማድረግ ሞክሬያለሁ፡፡ እውነተኛ ታሪክነቱ ሳይፈዝ ሳይጎላ አንባቢዬ እንዳቆበቆበ እንዲከተለኝ ሀዘኑ፣ ደስታው፣ ቁስሉ... እንዲታየው አድርጌያለሁ ብዬ አምናለሁ፡፡ ሁሉን ነገር ብቻዬን መወጣት ግድ ስላለኝ ሊጎል ቢችል እንኳን ከአቅም በላይ ሆኖ ነው፡፡



# ምስጋና

በርካታዎች ታሪኩ ውስጥ ስማችሁን ቀይሬና ሳልቀይር ያሰፈርኳችሁ የስደት ወዳጆቼ ሁሉ በህይወቱ ውስጥ ጉልህ ስፍራ የሰጠኋችሁ ለዛሬ ብቻ ሳይሆን ለነገም ጭምር ነውና አመስግኛችኋለሁ፡፡ በተለይ ለመንግስቱ ለገሰ ልዩ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡ የስደት ጉዞ ታሪካቸውን በመስጠት ለተባበሩኝ የሞያ ጓደኞቼ ጋዜጠኛ ዳንኤል ገዛኸኝና ታምራት ሰርቤሳ ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡ ከግብጽዋ መልኬ ታደሰን ከልቤ እወድሻለሁ፣ አመስግኛለሁ፡፡

የጀርመን ድምጽ ሬድዮ የሳዑዲ አረቢያው ዘጋቢ ጋዜጠኛ ነብዩ ሲራክን ምስጋና ከሚገልጸው በላይ አመስግኜዋለሁ፡፡ ጋዜጠኛ ነጋሽ መሀመድ፣ ሂሩት መለሰና ሌሎችም የDW ሬዲዮ ባልደረባዎች ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ የ**voa** ሬድዮ ጋዜጠኞች አሉላ ከበደና ጻለኔ ገመዳ የመን በጦርነት ማጥ ውስጥ ስትዳክር ስደተኛው ላይ የሚደርሰውን ሁኔታ ተከታትለው በመዘገባቸው ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡ ሌሎችም ስማችሁን ያልገለጽኩት በስደት ጉዳይ ላይ ለወገን የሰራችሁ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ፡፡

ጸሀይ በየነ የምትገርሚ ነሽ..ሀሳብ በማካፈሉ በኩል ሆነ በሌላው የአንቺን ያህል ማን አገዘኝ? ጥሩ ሰው ነሽ መንታ ያድርግሽ፡፡ ‹አሜን!› በይ፡፡ ስደት ላይ ያፈራኋችሁ እህቶቼ ሄለን ገ/እግዚአብሄር፣ አስመረት ገ/እግዚአብሄር፣ ሙሉ ኢዴሳና አይናዲስ (እሙዬ) ኢዴሳ እህታዊ ፍቅራችሁን ሳትነፍጉኝ ከአጠገቤ በመሆናችሁ በአፍ ባላመሰግናችሁም ዛሬ በተግባር ምስጋናዬን እነሆ በረከት ብያለሁ፡፡ አለም መንግስቱ..ተባረኪ፡፡ ዘንባባ ፍቅሬ ያኔ..ከእስር ቤት ጀምሮ ከጎኔ ነበርሽ ዛሬ ሳላመሰግንሽ ባልፍ ህሊናዬ አይቀበለውም፡፡ ክንደይ ሀፍቲ፣ ሽዋዬ ቀልቤሳ፣ ሀና መኮንን፣ አበባ እሹቴ፣ ብርቱካን እሹቴና ባለቤቷ ብርሃኑን የችግር ጊዜዬ ናችሁና ሳመሰግናችሁ እወዳለሁ፡፡ ሰብለወርቅ ታደሰ ሲርበኝ ያበላሽኝ እንዴት ይረሳል? ሊዲቲ (ሊዲያ ዳኛቸው) ትንሽዋ እስተዋይ ሁሌም እወድሻለሁ፡፡ ሄኖክ ምርጥ ነህ፡፡ ሳራ ከበደ (አሁን ካደር ያለች) ባለውለታዬ..ብረሳሽ የስደት ታሪኬ ይርሳኝ፡፡ ጎዳና ከመውደቅ አድነሽኛል፡፡ ቅዱስሀብት በላቸው፣ መርድ እስጢፋኖስ፣ ተመስገን ደሳለኝ፣ ዳዊት ከበደ፣ ሀብታሙ አሰፋ፣ ታምሩ ገዳ፣ ፋሲል የኔዓለም፣ ግርማ እንድሪያስ (መካሪና አጽናኜ ነበርክ አሁንም አከብርሀለሁ)፣ አክሊሉ ታደሰ እና ሌሎችም የነጻ-ፕሬስ ጓዶቼ ታሪክ የማይረሳው ምስጋና ይድረሳችሁ፡፡ ዘላለም ገብሬ ሁሌም ሞራሌ ነህ ያብዛህ ብያለሁ፡፡ ሁላችሁም በዙሪያዬ ቾቦ እንደሆናችሁ ያቆያችሁ፡፡ ሰብለ ሽፈራሁ (ሰብሊና ፍቅር) ከውጥኑ ጀምሮ አብረሽኝ ነበርሽ አመስግኛለሁ፡፡

ሰብለ ዩሀንስ፣ ነብዩ ተስፋዬ፣ ነጅብ፣ ስዒድ ሽዋፊም፣ አብረሃም በቀለ...በስደት ነዋሪ የሆኑ ኢትዮጵያዊያንን በሙሉ ከደላላዎችና ወገናቸውን ከሚሸጡ መጥፎዎች ውጭ ሁላችሁንም ዘራችሁን ያብዛው ብያለሁ፡፡ እንዳልኩት ካደረገው እሰየው፡፡ በመላው ዓለም በስደት ተበታትናችሁ ላላችሁ ወገኖቼ ለማውቃችሁ፣ ለማላውቃችሁ፣ ተስማምቷችሁ፣ ሳይስማማችሁ በሰው ሀገር የምትኖሩ ሁሉ አምላክ ፍቃዱ ሆኖ ለተሻለ ህይወት ወይም ለሀገራችሁ ያብቃችሁ

አሜን!! በሉ

# መታሰቢያነቱ

ይህ መጽሐፍ መታሰቢያነቱ በስደት እያለሁ በሞት ለተለዩኝ ባለቤቴ ዘለቃሽ ጉዲሳና ለወንድሜ ግርማ አየለ እንዲሆን እመኛለሁ:: እዚህ የመን ውስጥ ቃለ-ምልልስ ባደረግን በአመቱ በአሳዛኝ ሁኔታ በመኪና ተገጭታ ህይወቷ ላለፈው መሰረትም መታሰቢያ ይሁን:: ልናድናት ተሯሩጠን ሳንችል እጃችን ላይ ህይወቷ ላለፈው የ5 ዓመቷ ሀዊ መንግስቱ ልዩ መታሰቢያ ይሁንልኝ:: የስደትን ገፈት ከ11 ወር ህጻን ሆና ጀምሮ የቀመሰችው ሀዊ መንግስቱ ባልተስተካከለ ህክምና በአምስት አመቷ ህይወቷ አልፏል:: በስደት እያሉ እሷን መሳይ በህክምና ስህተት ህይወታቸው ላለፈው ሁሉ መታሰቢያ ይሁንልኝ::

*** *** *** ***

በአስቃቂ ህይወት በቤይሩት፣ በሰሪያ፣ በኩዌት፣ በባህሬን፣ በዱባይ፣ በሳዑዲ አረቢያ፣ በየመን፣ በግብፅ፣ በሱዳን፣ በጅቡቲ፣ በሱማሊያ..አጠቃላይ በስደት ላይ.. በስቃይ.. በዱላ፣ በእሳት አልፎ ተርፎ ኢ-ሰብአዊ ድርጊት ተፈጽሞባቸው ሕይወታቸው ላለፈ ወገኖቻችን ሁሉ የመን ውስጥ በተደራጁ መታሰቢያ እንዲሆን እነሆ በረከት ብያለሁ:: በተለይ በእነዚህ አፋኞች ወገኖቻችን ላይ በሚፈጸመው ስቃይ ሰለባ ለሆኑ:: IOM ካምፕ ውስጥ ህክምና ሀይሎች ብልቱን ተቆርጦ ሀረድ ያለው መታሰቢያነቱን በጥቃት ቁጭት ሲደረግለት ራሱን አንቆ ላጠፋው ወጣት እየተርመጠመጥኩ አበረክታለሁ::

*** *** *** ***

በሶማሊያ እና በጅቡቲ አቋርጠው ከ36-40 ሰዓት 16 ሰው በምትጭን አሳ ማስገሪያ ጀልባ ከ100-120 ሰው ሆነው ተፋፍገው በባህር ተጉዘው ወደ የመን ለመሻገር ቀይ ባህርና ህንድ ውቅያኖስ ሰምጠው ለቀሩ በሙቶ ሺህ ለሚቆጠሩ ወገኖቼ ይሁን:: በ3 ጀልባ ሞልተን ተነስተን አንዱ ከ90 ሰው በላይ እንደያዘ እያየነው የሰመጠበት ሁኔታ ከአይነ ህሊናዬ የማይጠፋ ነውና ልዩ መታሰቢያነቱ በዛ ጉዞ ሰምጠው ለቀሩ ወንድሞቼ ነው::

ግሩም ተ/ሀይማኖት



# ማውጫ


እንደ መግቢያ .......................................... 7

1. ስንብተ አካባቢ .......................................... 13
2. ሐረርን ማለፍ.......................................... 31
3. ከጅጅጋ እስከ ጠረፍ.......................................... 39
4. ሐርጌሳ.......................................... 45
5. ጉዞ ወደ በሳሶ .......................................... 50
6. ቆይታ በቦሳሶ .......................................... 55
7. የባህር ጉዞ.......................................... 92
8. የየመን መሬት ላይ.......................................... 104
9. ቆይታ በሰነዓ እስር ቤት.......................................... 119


## ክፍል ሁለት - ሐበሻ በየመን


10. ትውውቅ - እኔና ሰነዓ .......................................... 157
11. ዘመነ-ግርምቢጥ .......................................... 165
12. ጋዜጠኛ ዳንኤል ገዛኸኝ.......................................... 176
13. ስደት ያጠወለገው ልጅነት .......................................... 187
14. ባሕር ተሻግሮ ሕይወትን መሸጥ.......................................... 204
15. በUNHCR ቢሮ በር ላይ የተፈፀመ ግፍ.......................................... 215
16. ሆድ ለባሰው.......................................... 220
17. የጠላት ልጅ.......................................... 232
18. ማንም ፈልጎ አይሸረሙጥም! .......................................... 238

## ክፍል ሦስት - የሞት ጉዞ

19. ሠይጣን የሚቀናባቸው ጭራቆች ........................ 251
20. የታጋቾቹ ሰቆቃ ........................ 258
21. ወደመጥፊያችን የምንሮጥ የእሳት ራቶች ........................ 269
22. ጥቂት ስለ ቤይሩት ........................ 287
23. ሳዑዲ - ጭካኔ፣ ሰቆቃ፣ ውርደት፣ ሞት ........................ 296
24. መደምደሚያ ........................ 313



# እንደ መግቢያ

የምናወራው ስለስደት ነው:: ስደት መቼ ተጀመረ ብሎ መጠየቅም ሆነ ማሰብ አስቸጋሪ ነው:: አዳም ከገነት ሲባረር ይሆን ስደት የተጀመረው? ወይስ ቃየል አቤልን ገድሎ ፈጣሪ «..በምድር ላይ ኮብላይና ተቅበዝባዥ ትሆናለህ..» ባለው አምላካዊ ቃል መሰረት የመጀመሪያው ስደተኛ ሆነ? ዮሴፍ ይሆን ወደ ግብፅ ሲሰደድ ስደትን የጀመረው?..የሚሉ ብዙ መላ ምቶችን እየሰጡ ማየት ይቻላል:: ይሄ የእኔ እሳቤ ነው:: ስደትን ማንም ይጀምረው ማን፤ መቼም ይጀመር መቼ ስደት ባይኖር አለም አሁን የደረሰበት ደረጃ ባልደረሰ ነበር:: ፍጥረት ሁሉ አዳም በኖረበት ቦታ ተፋፍጎ በኖረ ነበር::

የተፈጠረበት ቦታ ነውና::

ስደት ለሰው ልጅ በአለም ላይ መበተን አስተዋጽኦ ቢኖረውም ጥሩም ሆነ አስከፊ ገጽታ አለው:: ስደት ድህነት ነው:: ድህነት ደግሞ አውሬ:: ያውም የዱር አውሬ:: ተናካሺ.. እንደመዥገር ተጣብቆ የማይላቀቅ አውሬ:: ይህን አውሬ አብረን ከመኖር ብዛት ለምደን አላምደን ቤተሰብ (የቤት እንስሳ) አድርገነዋል:: አውሬነቱን ረስተን አብረን ውለን አድረናል::

ከጥንት ጀምሮ ለረጅም ዘመን ድህነትን ለምደን አላምደነው እንደ እድፍ ተመርጎብን እንደካባ ለብሰነው ቆይተናል:: ተስማምቶን ይሁን ታግለን እንደማናሸንፈው ራሳችንን ቀድመን አሳምነን ከመታገል ይልቅ ለብዙ ዘመናት ታቅፈነው፣ ተጎብሮብንም ተኝተናል:: ድህነት አንጼ ከላይ የተጻፈልን እጣ ፈንታችን ይመስል ከዘመን ዘመን አብሮን እየተሻገረ ከመሰረታዊ ፍላጎታችን [illegible] መስሎ ኖሯል:: ድፍን አፍሪካ በድህነት

«ረሀብተኛ» የሚል ቢጠራም የእኛው ባስ፣ ጠና ያለ የጎደፈ ስም ያነገበ የታከለበት ነው።

ኢትዮጵያዊያን በአጠቃላይ ስደትን፣ ርሀብን፣ ድንቁርናን፣ ድህነትን፣ ጦርነትን፣ እንደ ምዕራባዊያን በወሬ እና በፊልም ሣይሆን በተግባር ያየነውእንዲያውም ከማንኛውም ሀገር በተሻለ ሁኔታ ቀምሰን ያጣጣምነው ነን። እያጣጣምነውም ነው። ማጣጣም ብቻም ሣይሆን ከውልደት እስከሞት እያጫወተ፣ እያዋዛ ተታለን ይሁን ዕጣ ፈንታችን ብለን በይሁንታ ተቀብለነው ብቻ ባላወቅነው ምክንያት ተሸክመነው ቆይተናል። አሁን ግን....

በቃ!

ድህነት አውሬ መሆኑን አውቀናል። ድህነት የጣለው ጠባሳ ህሊናችንን ጎድቶታል። በዓለም ላይ ሁሌ በድርቅ መጠራታችን የችግር፣ የርሀብ ምሳሌ መሆናችን ያላንገሸገሸው የለም።

መሮናል!!

በእፍረት አንገት ያልደፋ የሀበሻ ልጅ የለም። እስከመቼ በዚህ ሁኔታ ይቀጥላል?

እስከመቼ?

መቀጠል የለበትም የሚለው ያስማማናል። እንደመፊክር እጃችንን ከፍ አድርገን በአንድ ላይ ባንጮህም ከእጅ አይሻል ደማ ኑሯችን ሊለወጥ ባለመቻሉ እያንዳንዱ ድህነትን ሊታገለው ቆርጦ ተነስቷል። ሲነሳ ያገኘውን ሁሉ በአማራጭነት ይዞታል። በልቶ ለማደር፣ ሰርቶ ለማግኘት በአገኘው አማራጭ ሁሉ ተጓዘ። ከአማራጮቹ ውስጥም ከ1966ዓ.ም ወዲህ በጉልህ የሚታየውን ስደት እንደ አንድ አማራጭ ማየት ግድ ብሏል። ያኔ ከጥይት ለማምለጥ፣ ራስን ለማዳን፣ አሁን ድህነትን ለማሸነፍ፣ ራስን ለማዳን መሰደድ:: በምድር፣ በባህር፣ በሰማይ..መሰደድ..ወደተገኘው ቦታ መሰደድ..። ስደት ደግሞ በጅምላ የምንስማማበት ባህሪው ከጥሩ ገጠመኝ ቀድሞ መጥፎ ጎኑና ስቃዩ መብዛቱን ነው። ጥሩ ጎኑ ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ የሚገኝ ሊሆን ይችላል። በትግል፣ በውጣ ውረድና በትዕግስት ቀና ገጠመኝ ከተገኘም በልፋት የመጣ ፍሬ ይጣፍጣልና ስኬታማነት ነው።

ትናንት አኑብ፣ አዳምጥ የነበረው አሳዛኝ የስደት ታሪኮች ውስጤን ይነኩት ነበር። የተጋነኑ ይመስለኝም ነበር። አሁን ሳየው ግን መጋነን ሳይሆን ታሪኮቹ ገና አልተነኩም የሚያስብል ነው። ስደት እስከወጣሁበት ጊዜ ድረስ እድሉን አግኝቼ፣ አይቼ ለመፃፍ እበቃለሁ ብዬ ህልም አልነበረኝም። ከሀገሬ የመውጣት ፍላጎቱ ስላልነበረኝ እንዴትስ ላስብ?





እንዴትስ ላልም? ህይወት በፈለግነው አቅጣጫ ብቻ ሳይሆን ባልፈለግነው ራሷ በፈለገችው አቅጣጫም ታስጉዘናለች። ይህ ሆነና ወድጄ ሳይሆን ሳልወድ ስደትን ቀምሼ በትክክል ቁስሉን አይቼ ለመጻፍ ተነሳሳሁ።

ስለስደት ለማውራት የሚቀለውን ያህል አይደለም ሁኔታው። የቀመሰው በትንሹም ቢሆን ያውቀዋል። ቁስሉን፣ ሞቱን፣ ስቃዩን ስደትን ያልሞከረው ማሳየት የሚችል አይመስለኝም። ምክንያቱም መስማት እንደማየት አይሆንምና። እኔ ይህን ታሪክ ለመጻፍ ስነሳ ስደትን በልሙጡ አይቼ ግርድፉን ለማስቀመጥ አይደለም። በባህር፣ በየብስ ያለውን ስቃይ፣ ገፈቱን አጣጥሜ ቀምሼዋለሁ። መቅመሴን ብቻም በቂ አድርጌ አልደመደምኩም። የመን በቆየሁበት ጊዜ ከተለያዩ በስደት ከቆዩ፣ ብዙ ካዩ ሰዎች ሀሳብ አካፍሉኝ ብያለሁ። ብዙዎችን ቃለ-መጠየቅ አድርጌ የደረሰባቸውን ስቃይና እንግልት ሰምቻለሁ።

በባህር ተሻግረው ካገኘኋቸው 54 ሰዎች ጋርቃለ-ምልልስም አድርጌያለሁ።መስማት እስኪሰቀጥጠኝ፣ በእንባ እየታጠብኩ ሰምቻለሁ። ሞትን ደጋግመው ከቀመሱ፣ በድብደባ አካላቸውን ካጡ፣ ተደፍረው በበሽታ ከተጠቁ..ልጅ ከወለዱ ጋር ሁሉ አውርቻለሁ። ብዙ ትኩረት ሰጥቼ ጥናት ሳደርግበት ቆይቻለሁ። የመን ውስጥ የስቃይ ወረዳ የተባሉትን ሀረድ፣ አልቀረስ፣ ባብል መንደብን ዞሬ አይቻለሁ። በልመና ከሚተዳደሩ አንስቶ ሰርተው እስከ ተለወጡ፣ ሀገር ቤት ከሚመላለሱ ሀገር መግቢያ እስካጡ አናግሬያለሁ።

ዱባይ፣ ሳዑዲ አረቢያ፣ ሉብናን ካሉ ኢትዮጵያዊያን እህቶቼ ጋር በመፃፃፍ ሀሳብ ወስጃለሁ። በተለይ ፌስቡክ የተባለው ማህበራዊ ድረ-ገፅ ከበርካታዎች ጋር ለመጻጻፍ፣ ለመወያየት አስችሎኛል። ወደሌላ ሀገሮች ስለሚደረጉ ጉዞዎች በቂ መረጃ ለማግኘት ከበርካታ ኢትዮጵያዊን ጋር በኢሜል፣ በስልክ፣ በፖስታ...ቻት በማድረግ ሀሳብ ተለዋውጫለሁ።

ብዙዎች ያላቸውን መረጃ ለመናገር ፍቃደኛ አይደሉም። ፍቃደኛ ሆነውም ታሪኩን የሚያጉደፈድፉት ሞልተዋል። መረጃ ስጠኝ ሲባል ለእኔ የማገኘው ጥቅም ምንድን ነው? የሚልም ያጋጥማል። ያም ሆኖ ግን ያሰባሰብኩት መረጃ ብዙ ነው። ቢሆንም ለአሁኑ ትኩረት የሰጠሁት በሶማሊያና በጅቡቲ አድርገው በባህር አቋርጠው የመን የሚገቡትን ነው። ራሴምከእነዚህ መንገዶች በአንዱ የተጓዝኩ በመሆኑ በቂ መረጃ ያገኘሁ ይመስለኛል። አውጣጥቼ ነው የሠራሁት። ይህን ስል የፈለገውን ያህል መረጃ ባሰባስብም ወደ የመንከዛም ወደ ሳዑዲ አረቢያ የሚጓዙ ስደተኞችን በተመለከተ በዚህች መጽሐፍ ሙሉ ስቃዩ ተገልጿል ለማለት አይደለም። ያሰባሰብኩትን መረጃ ሁሉ አላሰፈርኩትም። የሀሳብ ማሰቡም ይከብዳል። ድሪቶ እንዳይሆን ፈራሁ። ከሁለት መጽሐፍ በላይ ይሆናል። ለጊዜው ዋና

ዋና ያልኩትን ነው የተጠቀምኩበት። ፍቃዱ ሆኖ ከተሳካልኝ ሁለተኛ መጽሐፍ አሳትም ይሆናል አዘጋጅቼዋለሁ።

እስከዚያው በዚህ እናዝግም።

ሰላም ሁኑ

መልካም ንባብ



# ክፍል ሁለት

# ስደት

# - 1 -

# ስንብተ-አካባቢ

ፍርሃት ፍርሃት አለኝ ደፍሮ መለየት
የእናቴ ጠረኗን ማደር ሳላሽት
አልችልም መኖር ርቂ ከሀገሬ
እንኳን ለዘመናት ለአንድ ቀን አዳሬ.

ስደትና ስደተኛ ቁርኝታቸው የሚጀምረው ከየት ነው? ከቤት? ከሰፈር? ከአካባቢ? ተወልደው ካደጉበት ቀዬ፣ ከኖሩበት መንደር፣ ከወረዳ፣ ከአውራጃ፣ ከክ/ሀገር ወይም ጭርሱኑ ከሀገር ሲወጣ? ይሄኛው ይመስላል:: ከባህል፣ ከወግ ሲራቅ? ከእናት፣ ከአባት፣ ከእህት፣ ከወንድም፣ ከሚስት፣ ከልጅ.. ሲለዩ? ሁሉም ልክ ይሆናል:: የእኔ የሚሉትን ትቶ የእኔ ወደማይሉት የራስ ወደ አልሆነው..ወደ ባእድ ሀገር፣ ወደ ባእድ ሰፈር፣ ወደ ባዕድ መንደር፣ ወደ ባዕድ ባህልና ወግ ሲቀላቀሉ? ይሄ ደግሞ ያስፈራል::

እትብት የተቀበረበትን፣ አፈር ፈጭተው ጭቃ አቡክተው፣ ቦርቀው እቃ እቃ፣ ኩኩሉ፣ አባሮሽ፣ ጢባጢቢ፣ ለኞ ማከሰኞ..ብለው ከተጫወቱበት መራቅ ይሆን ስደትና ስደተኛን የሚያቆራኘው? ይሆናል:: ውሀ የተራጩበትን ስንቱን የልጅነት ትዝታ ወደኋላ ትቶ ጉዞ ሲጀመር ይሆን ስደትና ስደተኛ ቁርኝታቸው የሚጀምረው? ችግሩን ሊቀርፍ አለያም ያጣውን ሊያገኝ ወይም የሚፈራውን ሊርቅ፣ ከሚያሳድደው ለመሰወር.. ቢከፋም ቢለማም፣ ቢገፋም.. ቢደፋም ሁሉን ችሎ ለመኖር አስቦ ሲወስን? ወስኖ ሲነሳ ያኔ ነው ቁርኝቱ? እንጃ!!! ያምታታል::

በማንኛውም መንገድ ምንም ይሁን ምን በምክንያት ስለምክንያት በፍቃድ ያለ ፈቃድ ሁኙ የተባለው, ይሆናል:: ያ-ሆነና ስደትና ስደተኛ

ቁርኝታቸው ጀምሮ የስደትን ገፈት ለመቅመስ አንድ ብዬ እርምጃዬን ጀመርኩ:: ብዙ የተነገረለት የግንቦት 7 ምርጫ አንድ ወር ከአንድ ቀን ይቀረዋል:: የምረጡኝ ዘመቻው ተጧጡፏል:: ለእኔ ግን ይህች ዕለት ፍርሃት..ፍርሃት..የሚል ስሜት የፈጠረብኝ ሁኔታ ገጥሞኛል:: ሀሙስ የቀን ቅዱስ እንደሚባለው ቅዱስ ሆኖ ህይወቴን ለማትረፍ አለያም እርኩስ ሆኖ ከፍጻሜው ለመድረስ ወሳኙ ሠዓት ላይ ደረስኩ:: ወዴት እንደምሄድ የማያውቁት ወንድሜን፣ እህቴንና እናቴን ተሰናበትኩ:: ክ/ሀገር ደበቅ ብዬ እንደማሳልፍ ነው የነገርኳቸው:: ጠልጠል በምትደረግ የእጅ ቦርሳዬ ውስጥ ለቅያሪ የሚሆን ልብስ፣ መታወቂያና የተወሰኑ መረጃዎችን ጨምሬ ይገርለሁ:: አዲስ አበባን ከዛም በላይ በፍቅር የምወዳት ተወልጄ ያደኩባት ሰፈሬ 5 ኪሎን (ቅድስተ ማርያም አካባቢን) መቼ ይሆን ዳግም የማያት? የሚል መጀመሪያ ማሰቢያዬ ውስጥ ስንቅር ያለ እሳቤ ነበር::

መልስ የለም::

ጣሟን ያጣጣምኩት፣ አየሯ፣ ጠረኗ የሚናፍቀኝ አዲስ አበባ ለእኔ በፊልም ከማያቸው የፈረንጆቹ ከተማ ትበልጥብኛለች:: እነሱን አላውቃቸው አያውቁኝም:: ጠረናቸውን ስቤ አላጣጣምኩ ጠረኔን አልተነፈስኩላቸው፣ አይናፍቁኝ አልናፍቃቸው.. ቆሎ ቆርጥሜ፣ ሽልጦ ገምጬ..ሽሮ ያውም በሁለት መልክ ታጥቦ የተሰጣውን ሳይፈጭ ጥሬውን ቆርጥሜ፣ ሲፈጭ ወጡን አላምጬ አላጣጣምኩባቸው:: እቃ እቃ ብዬ ውሀ ተራጭቼ አላደኩ ባቸው:: አዲስ አበባዬ ግን (ሰፈራችን ወንዝ ባይኖርም ውሀ መራጫ ቀበና ወንዝ ሄደን ዋኝተናል) ስንት አይቼባታለሁ፤ ስንት አሳልፌባታለሁ:: ታዲያ አዲስ አበባ በማን ትለወጣለች? ፍቅሬን..ትዳሬን ከዚህ በኋላ መቼ ነው የማያት?

መልስ የለም::

ስለትዳሬ ያሰብኩት ያኔ ነው:: አሁን ሁሉም አክትሟል፣ ሀሳቤ ጨንግፎ ተስፋዬ ጨልሟል:: ፍቅሬን..ትዳሬን..የልጄን እናት..በአካል የማግኘቱ ነገር አክትሟል:: ሞት ክንዱን ትዳሬ ላይ አሳርፎ ፍቅሬን ነጥቆኛል:: እኔ ፍቅሬንና ትዳሬን፣ ልጄም እናቱን አጣን:: የስደት አስከፊ ገፅታ በሰበረው ቅስሜ ላይ የባለቤቴ ዘለቃሽን ሞት መርዶ ሰምቼ ይበልጥ ውስጤ በሀዘን ጠቆረ::

ፍቅር ተወኝ ተስፋ ቁረጥ
ውዷ ሄደች ሳትያዝ፣ሳትጨበጥ
ትዳሬም ፈረሰ ፍቅሬ ሜዳ ቀረ
በደንኩኝ በደንኩኝ..ሀዘን በላዬ ሰፈረ..

ሁሌም ሲከፋኝ ሆድ ሲብሰኝ እንደማደርገው ጥልቅ ሀዘን በተሰማኝ በዛን ወቅትም በረጅሙ ከቋጠርኩት ግጥም ላይ ቆንጠር ያደረኩት ነው...





ወደ ጉዞዬ መነሻ ልመለስ:: ድክ ድክ ሲል አይቼ ያልጠገብኩት ልጄ «ጉም» እያለ ሲከላተፍ የተደሰትኩበትን ያህል ሳልጠግበው ልለየው ነው:: የልጅነት ጠረኑን ሳላሽተው፣ እየሳሳሁለት የምለየው ልጄን መቼ ይሆን ዳግም በአካል የማገኘው? እንጃ!:: አድጎ.. ጎልምሶ.. ከ10..ከ20 ዓመት በኋላ?

መልስ የለም::

«የሴት ወንድ ሆና ያሳደገችኝ እናቴንስ የማያት፣ ዳግም የማገኛት መቼ ነው?»

መልስ የለም

«..እህቴን፣ ወንድሜን...ዳግም ላያቸው የምችለው መቼ ይሆን? ጓደኞቼንስ?» መልስ አልባ ጥያቄዎችን ማፍለቅ ያልሰለቸው አእምሮዬ የጥያቄ መዓት ያግተለትላል:: ግን ለጥያቄዎቼ ሁሉ መልስ የለም::

ወንድሜን የማግኘት ሀሳቤ አሁንም ውድቅ ሆኗል:: በስደት ሳለሁ አንዱን የእናቴን ልጅ (የወንድሜን) ሞት ተረዳሁ:: ስደት ያቆሰለኝ፣ የጎዳኝ.. አንሶ ሀዘንም ደጋግሞ ደቆሰኝ:: «አንድ አይን ያለው..» ያስባለኝ ወንድሜን አጣሁት:: አሁን ዳግም የማግኘት ህልሜ ጨነገፈ:: ያለችው ጽዮንን ሰላም ያድርግልኝ ብዬ ከመለመን ውጭስ ምን ማድረግ እችላለሁ::

«..ምነው ሆዴ ባባ አልችል አለ አንጀቴ..» የሚለውን ዘፈን ዜማ አስታወስኩ:: በእርግጥም ሆዴ ባብቷል:: ረቡዕ እለት ሁኔታዎች ስላልተመቻቹ እናቷ ጋ ጫንጮ ያለችው ሚስቴና ልጄን ለመሰነባበት ሄድኩ:: የዚህን ያህል ሆደ ቡቡ ነኝ ወይ እስክል ድረስ ሎንቺና ላይ ሁሉ ሰው ግራ እስኪጋባ ስነፈርቅ ነው ተመልሼ አዲስ አበባ የገባሁት:: አዳሬንም ስረበሽ ነጋ:: ወዴት እንደምሄድ አጥርቼ አልወሰንኩም:: «በሞያሌ አድርጌ ኬንያ...ወይስ ወደ የመን ይኬዳል በተባለው መንገድ?..» ውስጤ ይጠይቃል::

መወሰን ከብዶኝ በሀሳብ እየተንገዳገድኩ ነው:: ጊዜ የለኝም:: ስለሁለቱም ያለኝ መረጃ ደመናማ ነው:: ረቡዕ ዕለት ደብረዘይት ከተማ ያለ ጓደኛዬ ዮሴፍ ወንድሙ ወደ የመን በተባለው መንገድ ስለተጓዘ መረጃ ጠየኩት:: የሚያውቀው ነገር አለመኖሩን ነግሮ ለትራንስፖርት እንዲረዳኝ የወዳጅነቱን 1000 ብር ሰጠኝ:: ያውቃሉ ያልኳቸው ጋ ሁሉ በስልክ አዳረስኩ:: ያገኘሁትን ጥቂት መረጃ ይዤ ጉዞ ልጀምር ነው::

አሁን ሀሙስ ከጠዋቱ ሁለት ሰዓት ነው:: የትውልድ መንደሬን በሀሳቤ እየተሰናበትኩ ነው:: ቅድስተ ማርያም ቤተክርስቲያን በር ላይ ደረስኩ:: ተሳልሜ «በይ እንግዲህ በምልጃሽ አትርሽኝ ታከተይኝ» ብዬ ቁልቁል ወደ አራት ኪሎ ሐውልት ወረድኩ:: ከልጅነት እስከ እውቀት ያደኩባትን

ቅ/ማርያም ቤተክርስቲያንን ቁርጥ አድርጎ መለየት ከብዶኝ ገብቼ ሁሉ ዞሬያለሁ:: ደጋግሜ ተሳለምኩ::

እርምጃዬን በቀጠልኩ ቁጥር ፍርሃቱ እያየለ መጣ:: ለዚህም ነው ወደ አራት ኪሎ በእግሬ የምወርደው:: አካባቢውን ለመስነባበት ውስጡ ባይፈልግ ኖሮ ቅድስተ-ማርያም ጋ ለገሀር ባቡር ጣቢያ የሚወስደኝን ታክሲ መያዝ እችል ነበር:: ዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ጋ ስደርስ ቅር..ቅር..አለኝ:: ለምን እንደሆነ ግን አሁን ድረስ ይገርመኛል:: ምክንያቱም እዚህ ትምህርት ቤት አልተማርኩም:: ከ1-8 በፊት አርመን ይባል የነበረው በኋላ ብሔራዊ ቤተመንግስት የተባለው ት/ቤት፣ ሁለተኛ ደረጃን ደግሞ ኮከበ ጽባሕ እና አቃቂ አጠቃላይ ነው የተማርኩት:: ታዲያ ዳግማዊ ምኒልክ ጋ ስደርስ ለምን ቅር አለኝ? እንጃ!!

ቁልቁል ወረድኩ:: መብራት ሀይል ያለበት ሕንፃ ጋር ስደርስ ከዛ ጊዜ በፊት አንዴ ብቻ ያየሁት የአእምሮ በሽተኛ /እብድ/ እየዘፈነ ከጊቢ ውጭ ያሉትን ተማሪዎችና መንገደኛውን ያስቃል:: እኔ ለመሳቅ ብፈልግም የምችል አልመሰለኝም:: ውስጤ ተበጥብጧል:: ትኩረቴን ግን ሳበው..

«ሰዎች ተጠንቀቁ!! ሌባን ሌባ ሰረቀው..አዎ! አንዱ የሰው ሚስት ሰርቆ ሲሄድ እሱን ሞት ይሰርቀዋል:: የት አባቱንስና..እርፎ አይቀመጥም ነበር?..» ሰዉ ይስቃል:: የእኔንም ትኩረት የበለጠ ሳበው:: ወደ አንዷ ተጠጋ:: ድክም እስክትል ትስቃለች:: «አዎ! ሳቂ!..ሳቂ.. አንቺማ ምን አለብሽ? የሽሮ እትይ የበርበሬ..ቤተሰቦችሽ ትማራለች ብለው ልከዋል:: አንቺ ውጭ ወራጁ ላይ አፍጥጠሽ ታስፈጥጪዋለሽ:: ስቀሽ ታገነፍይዋለሽ:: የዘንድሮ ስሜት እንደሆነ እንኳን ስቀውለት.....ስማሽኝ? እንኳን ስቀውለት ደርሶ ብድግ ነው:: ዘመኑ የውበት ነው እየተባለ እንደፔፕሲ ግንፍል! ክልብስ ይላል ስሜቱ:: እሱን ሊደፉ መጣደፍ በዛው መጠለፍ..አበባ ቀሳሚ ንብ ሳትሆኝ ከወንድ ወደ ወንድ የምትዘይ ዝንብ ነው የሆንሽው:: በሽታሽን ትቀስሚና መልሶ ተማሪልን ላሉህ ወላጆች ጦስ ነው የምትሆኚው ሂሂሂሂጅ እዛ!...»

በጣም የሚገርም አባባል ሆነብኝ:: ፈጽሞ ከአንድ እብድ የምሰማውም አልመሰለኝም:: ለነገሩ ከዛ በፊት ግንፍሌ ድልድይ አጠገብ ያየሁት ጊዜም አስገርሞኛል:: ሲዘፍን ሁሉ ሰምቼዋለሁ::

«ይሞታል ወይ..ይሞታል ወይ ታዲያ..

ይሞታል ወይ ታዲያ...» መዝፈኑን ትቶ «ለምን አይሞት ቀላል ይሞታል እንዴ? እንደ ጉድ ይሞታል እንጂ:: ወይ ጉድ ያውም ክስት ብሎ ሸንቅጦ ሬሳ አቅልሎ ነዋ! የሚሞተው»

መልዕክት አለው:: ሁለቱም በዘመኑ በሽታ ዙሪያ ሲያጠነጥን ነው የሰማሁት:: በእርግጥ ከእብዶች ብዙ ቁም ነገር እንደሚገኝ አውቃለሁ:: ይሄ





ግን በትክክልም ማስተላለፍ የፈለገው መልዕክት አለ:: ከአእምሮ ችግሩ ጋር የተያያዘ ነገር ይኖረው ይሆን? እርግጠኛ መሆን አይቻልም:: የሚያወራው የውስጡን ቁስል፣ ጭንቀቱ የወለደውን ይመስላል::

እሱን አልፌ ትንሽ እንደተጓዝኩ 4 ኪሎ ዩኒቨርስቲ ጋ ስደርስ ትዝ አለኝ:: ሁሉ ነገር እንደፊልም ተግተልትሎ መጣ:: ከዩኒቨርስቲው ፊት ለፊት ወዳለው ዳሽን ካፌ ጎራ አልኩ:: ትዝታዬን ላጣጥም ይሁን ቁርስ አስፈልጎኝ ልብ አላልኩም:: ለመጨረሻ ጊዜ እያልኩ ሁሉን መሰናበት የፈለኩም መሰለኝ:: ድንገት ብልጭ ብሎ እንደፊልም የተግተለተለው የ1993 ዓ.ም የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች አመጽ ነው:: ሚያዚያ 10 ረቡዕ ዕለት በአስከፊ ሁኔታ የተጠናቀቀው የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ተቃውሞ ታወሰኝ:: ስንዳፋ ከመላክ ያመለጥኩበት የቅ/ማርያም ጊቢ ገጠመኝ ትዝታም እንዲሁ::

ቅ/ማርያም ቤተክርስቲያን ውስጥ ተማሪዎችን ቃለምልልስ በምሰራበት ወቅት የጊቢው በር ተዘጋ:: ከቀኑ 11 ሰዓት አካባቢ ነው:: ሰፈሬ መሆኑ ጠቅሞኛል:: የጊቢው በር ሲዘጋ ወደ ሰንበቴ ቤቱ ሄድኩና በአጥር ወደ ቤተክህነት ጊቢ ዘልዬ ገባሁ:: ዘበኛው የሰፈሬ ሰው ቢሆንም «አትወጣም» አለኝ:: ገፍቼው ወጣሁ - ጨክኖ አልታገለኝም:: ሰርክዓለም ፋሲል የህትመት ድርጅቱ ባለቤት ውስጥ መሆኔን ሰምታ ተጨንቃ እያለች ቢሮ ስገባ እንዴት እንደ ተደሰተች በሃሳቤ ታየኝ::

የአራት ኪሎ ዩንቨርስቲ ተማሪዎች አትወጡም ተብሎ በር ተዘግቶባቸዋል:: በመሀል ብጥብጥ አነሱ:: በዚህ ጊዜ ከየት እንደተወረወረ ባልታወቀ ድንጋይ ጀርባዬን የተመታሁበት አውቶቡስ ማቆሚያ ጋ ስደርስ ነው ያ ወቅት ትዝ ያለኝ:: ትዝ ብሎኝም እርምጃዬን የገታሁት:: ዳሽን ካፌ በረንዳ ላይ ቁጭ ብዬ ማሰላሰል ጀመርኩ:: መቼ ነው እርስ በእርስ መባላቱን የምናቆመው? እንጃ!!..መቼ ነው መንግስት ህዝብን የሚያደምጠው? መቼ..መቼ..መቼ... ብዙ መቼዎችን ናፍቀናል:: ጠብቀናል::

በሌላ በኩል ደግሞ መቼ ይሆን ህዝብ መንግስትን የእኔ ብሎ ተማምኖ የሚቀመጠው? ለጥቂቶች የስልጣን ጥም የብዙዎች ህይወት ማለቁ በዚህ መንግስት..በዚህ ምርጫ ያበቃ ይሆን? እረፍት ሊሰጠኝ ያልቻለው አእምሮዬ ጥያቄ ማፍለቁን እንደቀጠለ ነው:: ረቡዕ ሚያዚያ 10 ቀን 1993 ዓ.ም የነበረውን ሁኔታ ከጠዋት ጀምሮ ያየሁትን በሙሉ አርብ በወጣው «ምኒልክ» ጋዜጣ ላይ አሠፈርነው:: ምክንያቱም እኔ በዋና አዘጋጅነት የምሰራባቸው ሁለቱም «ሳተናው» እና «አስኳል» ጋዜጦች ለንባብ የሚበቁት እሁድና ማክሰኞ ነው:: ያለው አማራጭ በዛው ሕሳታሚ ስር የሚታተመው «ምኒልክ» ጋዜጣ የአርብ ዕለት ዕትም ላይ ማስፈር ነው::

ወቅታዊ ነው:: ዜና ደግሞ ወቅታዊነት ይጠይቃል:: «ወቅቱ ያለፈበት ዜና እና ክፍቱን ያደረ ወጥ አንድ ነው» የሚል አለምሰገድ የሚባል ነፃው ፕሬስ ውስጥ ያፈራሁት ጓደኛ ነበረኝ - ነፍሱን ይማረውና:: በወቅቱ ለዜናው «በርካታዎች ሞቱ ቆሰሉ..» የሚል ርዕስ የሰጠው እስክንድር ነጋ ነው:: ያኔ እኔ ምን አይነት ርዕስ እንደሰጠሁት አሁን አላስታውስም:: የማስታውሰው ግን ዜናውን ረቡዕና ሀሙስ ዕለት ያሰባሰብኩትን መረጃ ከተለያየ አቅጣጫ እየቃኘሁ እንደልብ ትንተና ለመስጠት እንዲያመቸኝ በትረካ መልክ ነው ያቀረብኩት:: ለክሳሾቻችን ማን ነው የጻፈው የሚለውን ሳይወጡ ሳይወርዱ እንዲያውቁ እኔው ረዳኋቸው:: ምክንያቱም ትረካዬን ስጀምር

«..ረቡዕ ሚያዚያ 10 ቀን ጠዋት ላይ ከቅድስተ ማርያም ቤተክርስቲያን ፊት ለፊት ካለው መኖሪያዬ ወደ ስራ ለመሄድ ስወጣ እንደ ወትሮዬ ተሳልሜ ለማለፍ ተጠጋሁ:: ከወትሮው የተለየ ሁኔታ ነው የገጠመኝ:: በአመጽ ላይ ያሉት የአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ተማሪዎች ጥያቄያችን ካልተመለሰ አንማርም በማለታቸው ጊቢውን ለቀው እንዲወጡ በመደረጉ..ቤተክርስቲያን ጊቢ ውስጥ ተጠልለዋል:: ትኩረቴን ሳቡት..» በማለት ዜናውን ጀምሬ ቀኑን ሙሉ ተከታትዬ ያየሁትንና የሰማሁትን አስፈርኩኝ:: ከዛ በኋላ ለእነሱ ቅ/ማርያም ፊት ለፊት ያለ ጋዜጠኛ ማነው ብሎ መጠየቅ ብቻ ነው ቀሪው ስራ::

እግዚአብሄር ይስጠኝ:: ራሴ ላይ ጠቁሜ ጠላት አበዛሁ::

በወቅቱ ከቢሮ መኪና አዘጋጁና ተዘዋውሬ ፎቶ አነሳሁ:: ፒያሳ አካባቢ የተሰባበሩ ሱቆች፣ ተመተው የወደቁ ሰዎች፣ ራስ ደስታ ሆስፒታል አካባቢ የተሰባበረ መኪና፣ ተ/ሀይማኖት ጋ የተቃጠለ አውቶቡስ፣ መርካቶ የተቃጠለ ጎማ..የተሰባበረ መኪና፣ የተዘረፈ ሱቅ፣ አውቶቡስ ተራ አጠገብ ያልው ቴሌኮሙኒኬሽን የደረሰበትን ውድመት በካሜራዬ ከያዝኳቸው መካከል የማስታውሳቸው ናቸው::

በማግስቱ ጭምር ተዘዋውሬ ያነሳሁትን ፎቶ በጋዜጣው ፊት ለፊት እና ጀርባ ገጽ ላይ አወጣነው:: ሰው መሞቱን ጭምር ጻፍን:: የሞቱት ሰዎች ቁጥር ያገኘነው መረጃ ውስን በመሆኑ እንጂ ከዚህም በላይ ይሆናል የሚል እምነት ነበረኝ:: እኔ እንኳን ያየሁት ብዙ ነው:: ከሁሉም ግን የማይረሳኝ አራት ኪሎ ቱሪስት ሆቴል አጠገብ ይለምን የነበረው አይነ ስውር ነው:: የአካባቢው ሰው በቅጽል ስም «ቫንዳም» በማለት የሚጠራው የእኔ ቢጤ አሟሟት አይረሳኝም:: በልመና ያጠራቀመው ወደ 3000 የሚጠጋ ብሩን በደረት ኪሱ እንደያዘ በጥይት ተመቶ ወድቋል:: «ቫንዳም» ያጠራቀመውን ብር ሳይበላው በጥይት ተመቶ ተበሳስቷል:: «ቫንዳም» ተብሎ መጠራቱ ካልቀረ የሆሊውድ ጀብደኞች እንደሚያሳዩን





የተጠራቀመው ብር ጥይቱን አላሳልፍ ብሎ እንቅ አርጎ አላዳነው:: ብሩም ተበስቶ ህይወቱንም አጥቶ አሳዛኝ አወዳደቅ ወድቆ ያየሁት ከህሊናዬ መዝገብ ሰፍሮ አለ::

ሌላኛው የማይረሳ የ1993ዓ.ም ሚያዚያ 10 ትዝታዬ..ከቱሪስት ሆቴል አጠገብ ቁልቁል ወደ አሪ በከንቱ መውረጃ መንገድ አለ:: ከዛ ተነስቶ ፓርላማ ፊት ለፊት የሚያወጣው ኮረኮንች መንገድ መገንጠያ ላይ ተባራሪ ጥይት የደፋቸው ጉሊት ይነግዱ የነበሩት ወፍራም ሴትዮ አሟሟት ነው:: ከተቀመጡበት መደባቸው ላይ ወርደው በደረታቸው ድፍት ብለዋል:: ወጣቶቹ ድንጋይ ይወረውራሉ:: *(እዚህ ጋ የማስታውሰው መንገደኛ እንደ ጉልት ነጋዴ አይደሉም የሚል ነገር ነበር::)* በዩኒቨርስቲ ተማሪዎች «ቆንጆዎቹ»[1] የሚል ቅጽል ስም የተሰጣቸው ኃይሎች ድንጋይ መከላከያ ይዘው መሳሪያቸውን ያንጣጡታል:: ግርግሩን ለማሳለፍ እኔም ሆንኩ ከፊቴ የነበረችው ቪዲዮ ካሜራዋን እንዳትደግን የተከለከለችው የቢቢሲዋ ዘጋቢ ኒታ ቫላ ዘለን ከአንድ የጉራጌ ሻይ ቤት ውስጥ ጥልቅ አልን::

ምን ያህል እንደቆየን ባላስታውስም ግርግሩ ጋብ ሲል እና ስወጣ ሴትዮዋ ተደፍተዋል:: ለመኖር ደፋ ቀና ሲሉ ድፍት ብሎ መቅረት ያሳዝናል:: ያውም ልጆች ለማሳደግ:: ስንት ልጆች ያለ እናት ቀሩ? በሰዓቱ ህይወታቸው ነበር፤ በኋላ ማለፋቸውን ሰምቻለሁ:: እናቴ ታወሰችኝ:: እኛን ለማሳደግ ጉሊት ለጉሊት እንጀራ ለመሸጥ የተንከራተተችው ፊቴ ድቅን አለ:: አይኔ እንባን ልቤ ሀዘንን አፍልቀው የዘላለም ቁስል ሆኖብኝ ቀሯ:: እኝህ ሴትዮ ልጆች አሏቸው:: ከልጆቻቸው አንዱ ታዋቂው የባህል ተወዛዋዥ እብዮት ደመቀ እንደሆነ በጊዜው ዜናው ላይ ያስነበበ 1 ጋዜጣን አስታውሳለሁ:: ግን የአብዮት እናት እኔ ያየኋቸው ይሁኑ አይሁኑ ግራ አጋብቶኛል::

አሁን አብዮት አሜሪካን ገብቶ ከEBS ጋር ባደረገው ቃለ-ምልልስ ነገሮች ተማቱ:: ብቸኛ ልጅ መሆኑን እና እጁ ላይ እንደሞቱ ተናግሯል:: ወይ እሱ ተሳስቷል ወይ እኔ ረስቻለሁ:: ግን የረሳሁ አልመሰለኝም:: ድንገት መኖሪያ ፍቃድ ለማግኘት ከሆነ የለወጠው ብዬ ስለሁኔታው ሳናግረው ሞክርኩ አልተስማማም:: ዛሬ..ዛሬ ጊዜው ከመርዘሙ ጋር ሁሉንም ባላስታውስም እኔ ስዞር ካየሁት እና መረጃ ከሰበሰብኩት ውጭ ቀሪውን ባልደረቦቼ ሰርካለም፣ መስፍንና መኩሪያ ናቸው ያሰባሰቡት::

---

[1] *እመጻ በተጀመረ ሰሞን የዩንቨርስቲ ተማሪዎችን ቃለ-ምልልስ በማደርገበት ጊዜ ቆንጆዎቹ..ቆንጆዎቹ እያሉ ሲጠቅሱ ለምን ቆንጆዎቹ እንዳሏቸው ጠየኩ:: «ቆንጆዎቹ» የሚለው መጽሐፍ ላይ በፒካፕ የሚጫኑት ሸርጥ አንገታቸው ላይ የሚጠመጥሙትን ከእነዚህ ጋር ለመሳከር ሉሉኝ:: መጠሪያው ተገቢ እንደሆነ ገባኝ:: ርዕስ አደረኩት:: በዛው ተሰዉደ::)*

እስክንድር ነጋ የሚገርም ተፈጥሮ አለው:: ብዙ ልዩ ነገሮች አሉት:: የዛኑ ያህል ማንም ሰው ጠንቅቆ ሊያውቀው የማይችል ባህሪ አለው:: ግልጽ የሆነ:: በጣም ድንቅ የሆነ:: ልዩ ፍልስፍና፣ ልዩ ተሰጥዖ፣ ልዩ ባህሪ..የግሉ አለም፣ ልዩ ምኞት ያለው ሰው ነው:: እስክንድር ሳይታክት መስራት ይወዳል:: ሳንፎርድ እንደተማረ ውጤት.. ውጤት.. ፈላጊ ነው:: መከራከር ይወዳል:: ሳንፎርድ እንደተማረ በአንድ ወቅት ሲያወራ ሰምቼዋለሁ:: የወጣትነት ጊዜውን ያሳለፈው አሜሪካ ሀገር በትምህርት ነው:: ከእሱ ጋር ስለ እድገቱም ሆነ ማንኛውንም ታሪኩን አውርቼ አላውቅም::

ይህን ያህል ቀርበን የምናወራበት አይነት አቀራረብ የለንም:: ችግሩ ከእኔ ይሁን ከእሱ ለይቼ አላውቅም:: ሳስበው ግን ከእኔ ይመስለኛል:: በስራ ላይ ግን ማውራት በባህሪዬ አብዛኛዎቹን ስለማልቀርባቸው ይሆናል:: ስለራሱ ብዙ ያለብንን እናወራለን:: ስለቤተሰቡም ሆነ ስለ እድገቱ፣ አልሰማሁትም:: ሲያወራም ማውራት የሚያስደስተው አይመስለኝም:: ሲሄድ ቀጥ ቀጥን ብሎ ረዘም ያለ ቁመቱ ግርማ ሞገስ አላብሶታል:: ያለበትን ሰው ከማለቱ ጋር ይበልጥ ረጅም ያስመስለዋል:: መግባባት ጋግርታም ነው:: ለመቅረብ ጊዜ አይወስድበትም:: ካልፈለገ ደግሞ የከፈለው መስዋዕትነት እስክንድር ነጋ በኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስ ታሪክ ውስጥ ለመጀመሪያ ጊዜ በቀላሉ የሚጠቀስ አይደለም:: ነፃ ፕሬሱ ሲጀመር ዋና አዘጋጁ ተፈራ «ኢትዮጲስ» የተባለ ጋዜጣ ያሳተመውም እሱ ነው:: ጋዜጣም ያሳትም አስማሪ ነበር:: «ሀበሻ» የተባለ በእንግሊዘኛ የሚታተም ወንጭፍ የተሰኘ ነበር:: ሀይለኛ ድብደባ ተፈጽሞበት እጁ ተሰብሯል:: በኋላ በለጠፈው ማስታወቂያ ጋዜጣ ጀምሮ «ጎበዝ 5 ዓመት ሞላን እኮ!!!» ብሎ ምን ያልከፈለው ታድኖ ተይዞ መፈጠርን በሚያስጠላ ሁኔታ ተደብድቧል:: መስዋዕትነት አለ?

ዳሽን ካፌ ቁጭ ብዬ ያዘዝኩትን ሻይ ፉት እያልኩ የ1993ዓ.ም. ትዝታዬን አጣጥሜ አወራረድኩና ተነሳሁ:: ያስታወስኩት እስክንድርን «በሰላም ያገናኘን» ብዬ መልካም ተመኝቼ ቁልቁል ወደ ጆሊ ባር ወረድኩ:: ጋዜጣ ነጋዴዎቹን አየሁ:: ለመጨረሻ ጊዜ እንደማያቸው ልቤ አምኗል:: ለወትሮው ጋዜጦቹን ከጋዜጣ ነጋዴዎቹ መካከል «ቸምቤ የት ይሆን?» የማይለየው ተግባቢ ከምሮ ይታይ ነበር:: በጥቁር ጠይምነቱ ላይ ፈገግታ ሰጥቶኛል:: ሂሳብ ነው:: እግዚአብሄር ይስጠው ሳንቲም ሳይኖረኝ በዱቤ ትንፍሽ አልልም:: ኖሮብኝ ሳይሆን በአይን ልሰናበተው ፈለኩት:: ቃላትማ ያውቀዋል ማለት አራት ኪሎ ጆሊ ባርን የሚያውቅ ሁሉ ቸምቤን ጋዜጣ ሻጭ ነው:: ያስደፍራል:: ለረጅም ጊዜ ቦታው ላይ የቆየ አንጋፋ

ለምን እንደሆነ ባላውቅም የተለጠፉትን ማስታወቂያዎች አንድ በአንድ አነበብኩ:: ለኮምፒዩተር ተማሪዎች፣ ክፍት የስራ ቦታ፣ ጨረታ ብዙ ነው





ያነበብኩት:: ትራንስፖርት /ታክሲ/ ይገፍ ወደ ለገሀር አውቶቡስ ተራ መሄድ ስችል አካባቢውን ቶሎ መለየት አቃተኝ:: ለመጨረሻ ጊዜ ሁሉን እያየሁ እየተሰናበትኩ መሄድ ፈለኩ:: ፓርላማው ጋ ስደርስ ሰዓቱን ለማየት ቀና አልኩ:: ሰዓቱን ለማየት መሞከሬ ገረመኝ:: ከልጅነት ጀምሮ ሲሰራ ሲበላሽ የማውቀውን ሰዓት አየሁት አላየሁት ምን ትርጉም አለው? እዛ ውስጥ የሚገቡት ሰዎችም ሆነ ሰዓቱ መቼ ይሆን በትክክል የሚሰሩት? የሚል ሀሳብ ሁሌም ይታሰበኝ ነበር:: የዛን ቀን ግን የታሰበኝ እዚህ ለመግባትና ህዝቡ ጫንቃ ላይ ለመፈናጠጥ ነው አይደል የምረጡኝ ዘመቻው? የሚል ነው::

ቁልቁል ወደ ሽራተን ወረድኩ:: ስንዝ ግን እያንዳንዱ ቦታ ላይ ያለኝን ትዝታ እያጣጣምኩ ነው:: ሽራተን እንዲህ ተቆልሎ በግርማ ሞገስ ያረፈበት ቦታ ላይ ይኖሩ የነበሩ አብረውኝ የተማሩ ሰለሞን (ቅጽል ስሙ ሞጋ) የህጻን ልጅ ጉሮሮ የምታክል ጫማ ማደሻ ቤት ነበረቻቸው:: ሸዋዬ የምትባል ቤታቸው ኮረፌ የሚሸጡ ልጅም አስታወስኩ:: ይሄኔ አንዱ አረብ ሀገር ትሆን ስልም አሰብኩ:: በአምባሳደር ቴያትር አድርጌ ብሔራዊ ቴያትርን የመሳለም ያህል ገብቼ ወጥቼ አለፍኩ:: መናፈሻው ላይ ጌትነት እንዳየውን አየሁት:: ሰላምታ ተለዋውጠን ዞር..ዞር..ብዬ ወጣሁ:: ብዙ ሰው ጌትነት በላይ ዘለቀን ሆኖ በሰራው ስራ ያስታውሰዋል:: እኔ ግን ለየት ባለ ሁኔታ አስታውሰዋለሁ:: ለምኒልክ መጽሔት ጥበብ አምድ ቃለ-ምልልስ ስናደርግ በሰጠኝ ፈጣን መልስ አድንቄዋለሁ::

«..የጅማ ልጆች የጅማ ልጅ ነው ይላሉ:: የባህር ዳር ልጆችም የባህርዳር ልጅ ነው ይላሉ አንተ ከየቱ ነህ?» የሚል ጥያቄ አቀረብኩለት::

«ከሁለቱም ነኝ» የእሱ መልስ ነበር::

«ግማሽ ጎንህ ከጅማ ግማሹ ከባህር ዳር መጥቶ አዲስ አበባ ላይ ተገጣጠመ ወይስ ሌላ ምስጢር አለው?» የእኔ ጥያቄ ነበር:: በፈጣን መልሱ «እም!..ከሁለቱም ሆኜ የተገጣጠምኩት አዲስ አበባ ነው:: የተወለድኩትና ለኛ ክፍል ድረስ የተማርኩት ባህርዳር ነው:: አባቴ ወታደር ስለሆነ ጅማ ሄደን እዚያ እስከ 12ኛ ተማርኩ:: አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ደግሞ የሁለቱን ውጤት ገጣጥሞ ይሄው..» ያለኝን አልረሳውም:: ከዚህ ውጭ በግጥሞቹ እወደዋለሁ:: ሰላም ተባብለን እንደተላለፍን «መቼ ይሆን ዳግም የምንተያየው?» የሚለው መልስ አልባ ጥያቄ ውስጤ ብልጭ አለ::

ለገሃር መኪና ተራ ስደርስ 4 ሰዓት ከ20 ነበር:: «ናዝሬት..ሞጆ.. ናዝሬት..ሞጆ..» በሚለው ካቻማሊ የሚባለው ቅጥቅጥ አውቶቡስ ላይ ከመሰቀሌ በፊት አንዳንዴ ረጅም መንገድ ስሄድ እንደማደርገው ጫት ያዝኩ:: አንድ ሊትር ተኩሉን ሐሸግ ውሀ ገዛሁ እና ተሳፈርኩ:: ልቤ ግን

ምቱ የቤተክርስቲያን ደውል እስኪመስል ይደልቃል:: በስደት ከርመው የመጡ ሰዎች ሲነግሩኝ በተለያየ ጊዜ ለትምህርትም ሆነ ለስራ ወደ ውጭ ሀገር የተጓዙ ኢትዮጵያዊያን ሁሉ ወደ ሀገራቸው የሚመለሱበትን፣ የእናት ሀገራቸውን ምድር የሚረግጡበትን ቀናት ይቆጥሩና ይናፍቁ እንደነበር ነው:: እኔ ደግሞ ገና ከአዲስ አበባ ሳልወጣ የምመለስበትን ጊዜ ሁሉ መናፈቅ ጀመርኩ::

መኪናው ሲንቀሳቀስ አሁንም ልቤ የፍርሃት አዶክብሬውን አጠናክሮ ይደልቃል:: የተሳፈርኩበት አውቶቡስ ውስጥ የተለጠፈውን ምስል ላይ መለማመን ጀመርኩ:: «አቤቱ..ጌታዬ ሆይ ከፍቶኝ ቤት፣ ሚስቴን፣ ልጄን፣ እህቴን፣ እናቱን፣ ወንድሜን ተለይቼ.. ወድጄ ሳይሆን አማራጭ አጥቼ ሀገር ለቅቄ ህይወቴን ለማትረፍ ኑሮዬን በትኜ ስደት ልገባ ነው:: መንገድም ብርሃንም የሆንከው አልፋና ኦሜጋ አንተ ተከተለኝ:: ውስጤን ፍርሃት.. ፍርሃት..ይለዋልና ብርታቱን፣ ቆራጥነቱን ስጠኝ:: ህይወቱ በሙሉ በፈተና የታጠረ ነውና በቃ ብለህ ይህን የመጨረሻ አርገው:: (የእኔ ብቻ ሳይሆን በስደት በየቦታው መሰቃየቱ በዚህ አሁንስ ለሀገሬ፣ ለወገኔ ሁሉ በቃ! ይበለን:: ደግሞም ከዚህ ለከፋ ችግር አጋልጠህ ይበቃ!..) ለከፋ ችግርም አታጋልጠኝ:: ደግሞም ከዚህ ለከፋ ችግር አጋልጠህ እንደማትሰጠኝ አምናለሁ::

ልጄንም ሳላሳድገው ሀገር ጥዬ እየሄድኩ ነው:: እኔ የአባቴን ጣዕም ሳላውቅ የ14 ዓመት ልጅ እያለሁ ነው የሞተው:: ለዛውም በሹፍርና ከክ/ሀገር ክ/ሀገር ሲዞር የአባትነት ወጉን ሳያሳየን አለፈ:: የጎደሎነት ስሜት ይገፍ ልጆች ስለ አባታቸው ሲያወሩ እየቀናሁ፣ እየተቆጨሁ ነው ያደኩት:: ይህ ልጄም ተጋርቶ እንዳያድግ ነበር ፍላጎቴ:: አልሆነም:: የባሰ ያንን ስሜት ልጄም ተጋርቶ እንዳያድግ ነበር ፍላጎቴ:: አልሆነም:: የባሰ እየራኩት መሄዴ ውስጤን በሀዘን እንዲሰበር አደረገኝ::

«..ልጄንም፣ እናቱንም፣ እናቴንም አደራ የምለው ለአንተ ነው» አልኩት፣ ፈጣሪዬ የተሳፈርኩበት አውቶቡስ መስታወት ላይ ተለጥፎ ያለ ይመስል መስታወቱ ላይ አፍጥጬ:: ያለው ምስሉ ብቻ ነበር:: የንስሀ አባት ሳያስፈልገኝ ጭንቀን ለራሴው ንስሀ እንድገባ አደረገኝ:: አሁን ያላስታወስኩት ብዙ የተምታታ የጭንቀት ነገር ለምኜው ብዙ ነገርም አስቤ እንደነበር አውቃለሁ:: ስሜቱ ውሉ ጠፍቶ ሌላ ጊዜ እንደማደርገው ስናደድ፣ ሲከፋኝ..ቅር ሲለኝ...ግጥም ለመጻፍ ቶሎ ወረቀትና ብዕር የምመዘው ዛሬ አልሆነልኝም:: ጨርሶ ፍርሃት..ፍርሃት ይለኛል:: ለምንስ አይለኝ? ከክ/ሀገር ወደ አዲስ አበባ አለያም ወደ ክ/ሀገር የምንሄደውን ነው ስደት የምንለው:: ጠቅልሎ ቢከፋም የማይመለሱበት አይነት ከሀገር የሚወጣበት ስደት በወሬ ከማውቀው ውጭ ሞክሬውም፣ አስቤውም አልማውም አላውቅም::





የአዲስ አበባ ጠረፍ የሆነው አቃቂ ላይ ነን:: ቱሉ ዲምቱ ፍተሻ ጣቢያ ጋ ከመድረሳችን በፊት አለም ባንክ የሚባለው ሰፈርን ሳየው ትዝታዬ ሁሉ ትዝ አለኝ::

አቃቂ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት 11ኛ እና 12ኛ ክፍልን የተማርኩበት ነው:: ዘጠነኛ እና አስረኛ ክፍልን የተማርኩት ኮከበ ፅባሕ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ነበር:: 11ኛ ግን በችግር ምክንያት አቋረጥኩ:: አክስቴ ነዋሪነቷ አቃቂ በመሆኑ ወስዳ አስተማረችኝ:: አቃቂ ብዙ ያሳለፍኩባት፣ ያየሁባት ነች:: እዚህ እንድማር ያደረገችኝ አክስቴን አለመሰናበቴን አስታወስኩኝ:: ምን ያደርጋል ወርጄ ወደኋላ ሄጄ አልሰና በታት የማይሆን ነው:: ግን መቼ አገኛት ይሆን? በውስጤ ተሰናበትኳት::

አቃቂ ፍተሻውን ስናልፍ «ቻው..ቻው..አዲስ አበባ..» እያልኩ በውስጤ ስንብቴን ፈጸምኩ:: ጋራ ላይ ያለው ቱሉ ዲምቱ ጊዮርጊስን ቀና ብዬ አየሁት:: ወደ ጊቢው መግቢያ በሩ ጋር ያለው የአባቴ ቀብር ላይ የተቀለለውን ሀውልት ለማየት ሞከርኩ:: ሌላ ቀብርና ቅጠል ዙሪያውን ስለበዛብኝ ልለየው አልቻልኩም:: አውቶቡሱን የሚዘውረው ሰው ስንብቴን አሳወቀ ይባስ አፈጠነው:: ግን ከምር ልሰናበተው ፈልጌ ይሆን? ለምን ማየት እንደፈለኩ አላወኩም:: ስደት ሲጀምሩት እንደዚህ ያደርግ ይሆን? ከዚህ በኋላ ለምን ያህል ደቂቃ በሃሳብ እንደዋለልኩም ሆነ ምን እንዳሰብኩ እንኳን አሁን ያኔም አላውቀው::

«ያ-አላህ! እስቶፉሩላህ ለአዚም..ከእንዲህ አይነት አደጋ ጠብቀን» የሚለው አጠገቤ የተቀመጡት ሴትዮ ንግግር ከሀሳቤ መለሰኝ:: ግራና ቀኜን ማተርኩ የተፈጠረውን ለማየት:: አብረውኝ የተሳፈሩት ሰዎች ሁሉ በሚያዩበት አቅጣጫ አየሁ:: አይኔ እነሱ ያዩትን አየ:: ለምን ይቅርብኝ? አመድ ላይ የምትንከባለል አህያ መስሎ አራት እግሩን ወደ ሰማይ የሰቀለ መኪና አየሁ:: ሰዎች ከበው ያንቧችራሉ፣ ያዳምቃሉ:: ጋቢናው ጭርምትምት ከማለቱ አንጻር ሹፌሩ ተረፈ? የሚል ጥያቄ ነው ሁሉም የሚያቀርበው:: በእርግጥም በዚህ ሁኔታ ተርፏል ለማለት የሚከብድ መሰለኝ::

ከፍተኛ አደጋ ነው::

እስከዛሬ ከአቃቂ እስከ ደብረ ዘይት ባለው መንገድ ብቻ ስንት የመኪና አደጋ አይቻለሁ? አምስት? አስር?..አንጃ! ብቻ ብዙ እንደሆነ ይሰማኛል:: አራት እግራቸውን ወደ ላይ ሰቅለው ያየኋቸው ግን ከዚህ ጋር ሁለት ናቸው::

ጉዞው ቀጥሏል:: ደብረዘይት ከተማን እንደ አህያ ጋማ ለሁለት ከፍሎ የሚያልፈውን መንገድ ይዘን እየተንዝን ነው፡፡ የእኔም ሀሳብ እና የስንብት

እይታ ቀጥሏል:: ጁስ ቤት? ወደ ሰዓሊ ለማ ጉያ ቤት መታጠፊያውን አየሁት:: ..ሁሉን ወደ ኋላ እየጣልን እማማ እርጎ ቤት ደረስን:: አጠገቡ ያሉ ዘመዶቼን አሰብኩኝ:: ወንድማማቾቹ መላኩ፣ ጥበቡ..ነፍሱን ይማረውና አሰበ ፀጉሩን እንደ አለማየሁ እሸቴ ከፍሎ የሚያበጥረው ስታይሉ ሁሉም ታወሱኝ:: መቶ አለቃ አሰበ..የአየር ወለድ አሰልጣኝ ነበር:: ወታደራዊ አልባሳቱን ለብሶ ልጅ ሆኜ ሳየው ወታደር መሆን እመኝ ነበር::

የገዛሁትን ጫት ጥቅል ያልፈታሁት የአውቶቡሱ ካሴት ማጫወቻ የመዝሙር ካሴት ስለጎረሰ ነው:: የዘማሪ ታዲዮስ «ሁሉ ለበጎ ነው» የሚል መንፈሳዊ ዜማ ይንቆረቆራል:: የእኔስ መሰደድ ለበጎ ነው? እንጃ!!.. የምቅመው አልፎ አልፎ ቢሆንም ለምን እንደሆነ አላውቅም ስቅም መዝሙር መስማት አልወድም:: ቀድሞ ከተከፈተም እስኪዘጋ ድረስ..:: በተረጋጋ መንፈስ ነው መዝሙር ማዳመጥ የምፈልገው:: አሁን ደግሞ እንደማይወለድ ሽል ውስጡ የሚተራመሰው ሀሳብ ስሜቴን ጥሩ እንዲሆን አላረገውም::

*(በሚሊዮን የሚቆጠር ወገኔ በየአቅጣጫው ለስደት ሲኳትን የእኔ አይነት ድብልቅልቅ ያለ ስሜት ይዞ ይሆን የሚጓዘው? በእርግጥ ፍርሃት..ፍርሃት ማለቱ እንኳን የማይቀር ነው::)*

«..ለምንድን ነው የሚከፋኝ?..ለምን ይሆን ሆድ የባሰኝ? አንተ ብርታት ስጠኝ:: በእርግጥ ስደት...ያውም ወደማያውቁት ሀገር መጓዝ... ድንበር ጥሶ፣ ባህር ተሻግሮ ወደ ባዕድ ሀገር መሰደድ ያሳስባል:: ያስፈራልም:: ግን ያለኝ አማራጭ ይሄው ነውና አረገዋለሁ:: እንዳረገውም ጌታዬ ብርታት እና ፅናት ስጠኝ? አይዞህ ግሩሜ በርታ በል፣ አይዞህ ብሶት ቢሰማህም፣ ብቸኝነት ቢውጥህም ሀያሉ እግዚአብሔር ከአንተ ጋር ነው::» ድብልቅልቅ ያለ ስሜት ይዤ ፈጣሪዬን እየለመንኩ ራሴንም እያበረታታሁ ውሉ ጠፍቶብኝ ናዝሬት መናኸሪያ ደረስን:: ከመኪና ወርጄ ወጣ እንዳልኩ ያገኘሁት ሆቴል ዘው..የምን ምርጫ ነው? መቀናጣት ስደት ላይ የለም:: ስደት ከእዚህ ይጀምራል:: ምሳ በላሁና ወደ ሐረር የሚሄድ መኪና ፍለጋ ጀመርኩ:: ቀጥታ የሚሄድ መኪና በማጣቱ አሰበ ተፈሪ ድረስ በሚኒባስ መሄድ ግድ ሆነብኝ::

ተሳፈርኩ::

ሚኒባስ ውስጥ ስገባ አንዲት ልጅ አጠገብ ለሁለት ሰው የሚሆን ቦታ አለ:: ለተወሰነ ሰዓት ጉዞ ጊዜያዊ የወንበር ጎረቤቷ ሆኜ ተሰየምኩ:: ገብቼ ቁጭ:: ሌላ ሴትዮ መጥተው አጠገቤ ቁጭ:: ወፈር ያሉ በሀምሳዎቹ ማገባደጃ ላይ ያሉ:: ፈጣን ተግባቢ ናቸው:: ገና ከመቀመጣቸው «..ልጄ ሰው ሲበላ በሀገራችን እንብላ ባህላችን ነው:: እንብላ ጎጂ ባህል ነው የምትሉት አባባል ራሱ ጎጂ አባባል ነው:: እንብላም አትልም?» አባባላቸው





ተመቸኝ:: ምሳ እንደበላሁ ጫቴን ነክሼ ነበር:: ጭኔ ላይ ያስቀመጥኩትን የጫት ላስቲክ ወደፊት ገፋ አድርጌ በምልክት እንዲወስዱ ነገርኳቸው:: ሁለቱን እንጨት ሳብ አድርገው ግራ እጃቸው ላይ መታ..መታ..አደረጉት:: ካራገፉ በኋላ መቀንጠስ ጀመሩ::

«..ሁሌ ከመቃማችን የተነሳ ሐረሮች ይቅማሉ ሳይሆን ይበላሉ ስለምትሉን ነው ኮ እንብላ አትልም ወይ ያልኩህ..» በአባባላቸው ተሳሳቅን::

«አይ ችግር የለም» አልኳቸው ምን ማለት እንዳለብኝ ሳላስበው::

«ደግሞስ..» አሉና ቀጠሉ «..ደግሞስ እኔ አፍ አውጥቼ ስለጠየኩህ ጋበዝከኝ፤ እሷንስ ምነው ዝም አልካት?..» አሉና በግራዬ በኩል ወደ ተቀመጠችው ልጅ አሳዩኝ:: ሁለት ሴቶች መሀል መቀመጤ ትዝ ያለኝ ያኔ ነው:: ሳንዱዊች አድርገውኝ የለ እንዴ?

«በጣም ይቅርታ መቃም ይቻላል:: ቃሚ...» ወደ ላስቲኩ አመለከትኳት

«አመሰግናለሁ እኔ ጫት አልቅምም»

«ለምን አትቅሚም? ጫቱ ያንሳል ብለሽ ነው? እኔም ይገርለሁ እኮ ለጨዋታ አልኩ እንጂ..» ከልባቸው በሆነ ቃና ተናግረው ከያዙበት ሊያወጡ ሲሉ እንደ መንገፍገፍ እያደረጋት

«እኔ አልቅምም:: ሃይማኖቴ አይፈቅድልኝም...» የሚል ምላሿን ሰሙ:: አዩዋት:: አስተያየታቸው «ምንድን ነው ሀይማኖትሽ?» የሚል ይመስላል:: ጠየቋትም::

«ፕሮቴስታንት ነኝ» አለች ይበልጥ ግልጽ ለማድረግ::

«መፍቀድማ ሁሉም ሀይማኖት አይፈቅድም» ልላት ነበር:: በእሷ እምነት ብቻ ሳይሆን ኦርቶዶክስም ሆነ እስልምና አለመፍቀዱን አውቃለሁ:: ግን ትንፍሽ አላልኩም:: ሆሆይ ደግሞ መከራከሪያ መንገድ ልክፈት? ማን ተዳረቅ አለኝ::

«....ቤንጤ ነሽ? ቤንጠ?» ሴትዮዋ ቃሉን ለጠሩት ፊታቸውን እንዴት እንዳደረጉት ላያቸው ይገርማል:: አንዱ ለሌላው እምነት ያለው ግንዛቤ አናሳ ሆኖ በጭፍን ጥላቻ መከናነቡ እስከመቼ ይቀጥል ይሆን?

«አዎ! ጴንጤ ነኝ» ረገጥ አደረገችው ንግግርዋን በእኮራበታለሁ አይነት ቃና::

«አወኩ ተይው!! ተይው ልጄ፣ እናንተ እኮ ሰው ፊት አትቅሙም.. አትጠጡም.. አታጨሱም:: ደህና ጨዋ ሰው ትመስላላችሁ::» የእኔ ሳቅ

አቋረጣቸው:: ሳቁ ተጋባባቸው መሰል ከት ብለው እየሳቁ «..እውነቴን እኮ ነው..»

«ምን ማለት ፈልገው ነው?» አቋርጣ ጠየቀቻቸው:: የተናደደች ትመስላለች::

በእርግጥም ተናዳለች::

«አየሽ እኔ የጅጅጋ ሰው ነኝ ቤንጤ..ቤንጤ ሲሉ ሰማሁ ምንድን ነው እሱ አልኩ እነሱ መሬምን አያምኑም፣ ጅብሪልን.. መላዒካን አያምኑም ይክዳሉ ብለው አሉኝ:: አላህ ሻኢ.ዶ */እግዚአብሄር ምስክሬ/* ነው ስቅጥጥ አለኝ:: እኛ ሙስሊም ብንሆንም ኢሳን የወለደች መሬምን.. ጅብሪልን ሁሉን መላኢካን እናውቃለን:: ደግሞ ምን አይነት እምነት መጣብን ብዬ ጥልት አደረኳችሁ:: ሳያቸው፣ ስለማ እንጠጣም፣ አንቅምም፣ አናጨስም ይላሉ:: እኔ ሆቴል አለኝ:: ስንቱ የማውቃቸው ክፍል ተከራይተው የሚያረጉትን አያለሁ:: ሲያጨሱ ብቻ አልገጠመኝም:: እነዚህ ሰዎች ከአላህ ነው ከሰው ነው የሚደበቁት እላለሁ::» በገራገርነት ያዩትን የሰሙትን ዘረገፉት:: የሚያ ጠፉ ሊኖር እንደሚችልና ሁሉ አንድ እንዳልሆነ በትዕግስት አስረዳቻቸው::

«እኔ እንኳን አልወዳቸውም፤ አልጠላቸውም:: */ይሄ ያኔ ብቻ ስይደለም ስሁንም ያለ ስቋሜ ነው::/* እንዲሰብኩኝ ግን አልፈልግም:: አልፈቅድም:: እኔም ልከራከራቸው አልወድም:: እንኳን ማርያም አታማልደንም ቀርቶ እግዚአብሄር አልፈጠረንም ቢሉ የራሳቸው እምነት የራሳቸው ነው:: እኔን ምን ያገባኛል?» ንግግሬን አላስጨረሰችኝም::

«ጂሰስ ክራይስ..» ስትል አቋረጠችኝ:: «እንዲህማ አይደለም:: አንተ የምትለው እኮ ወንድምህ ገደል ሲገባ እያየህ...» ከሀሳቤ ጋር ባልተገናኘ ክርክር ልትገጥመኝ መንገድ ነው የፈለገችው:: ቶሎ ማቆም አለብኝ::

«ዞረሽ..ዞረሽ..ክርክር ውስጥ ልትገቢ ነው:: በይ ተይው» አልኩ::

«እኔ ነኛ ሲያቀብጠኝ ጀምሬ... በሉ ተዉት:: ከፈለግሽ ቃሚ ካልፈለግሽ ግድ የለብሽም..» አዩዋት:: ተናደውባት ይሁን አድንቀዋት..አዝነውላት ይሁን፣ አዝነውባት ውሉ በማይታወቅ ሁኔታ አዩዋት:: ርዕስ ለመለወጥ የፈለጉ መሰለኝ:: አሰበ ተፈሪ ለምን እንደምሄድ ጠየቁኝ:: «..እኔ የጅጅጋ ሰው ነኝ» ያሉት ታወሰኝ:: የተወሰነም ቢሆን መረጃ ሊሰጡኝ ይችላሉ ብዬ አሠብኩ:: ጅጅጋንም አልፌ እንደምሄድ ነገርኳቸው:: «ለምን?» የሚለውን አስከትለው የምሄድበትን ለማወቅ ይጥራሉ ብዬ ያሰብኩት ስህተት ነው:: ጥያቄ አላቀረቡልኝም:: በዝምታ ተሸበበ::

እኔም ዝምታዬ ውስጥ ሸምቄ የናዝሬት ከተማን ለቀን ወጣን:: አሻግሬ ወደ ውጭ ማየት ጀመርኩ:: ቆንጥሩን፣ ጋራውን..እያየሁ በውስጤ «...ሀገሬ





ኢትዮጵያ ጋራሽ ሸንተረሩ..» የሚለውን ዜማ አስቤ ይበልጥ ስለተፈጥሮ፣ ስለሙቀቱ.. እያሰላሰልኩ ወለንጭቲ ደረስን:: መኪናው ስለቆመ ድንገት ከዛ በኋላ ሌላ ከተማ ላይ ካልቆመ ብዬ ውሀ እንዳያንሰን ተጨማሪ ገዛሁ:: ይህቺን ከተማ የማውቃት ወለንጭቲ ስትባል ነው:: «ቦሰት ወረዳ» የሚል ጽሁፍ በማየቴ ገረመኝ:: በዚህ በኩል ብዙ ጊዜ ተመላልሻለሁ:: አላየሁትም:: የመሰናበቻ በሚል አፍጥጬ ማየቴ መሰለኝ ዛሬም ያየሁት:: አለያም ጽሁፉ የተሰቀለው በቅርብ ነው ማለት ነው:: ወይስ ተሳስቻለሁ? ቦሰት ጋራውን አውቃለሁ:: ቦሰት የምትባለው ከወለንጭቲ ቀድማ የምትገኝ ትንሽ መንደር ነገር ነበረች:: ወይስ አሁን ለአውራጃው መጠሪያ ሆነ?

የምጠይቀው ሠው በማጣቴ በዝምታ ባልፈውም መገረሜ እንዳለ ነው:: የእኔ ልብ አለማለት ነው ወይስ ስሙ የተቀየረው አሁን ነው? መቼም የተሾሙ አስተዳደሮች.. ለህዝቡ እንታገላለን የሚሉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ሁሉ የብሄረሰብ ስምና የቦታ ስም መለዋወጥ እንደፋሽን አድርገውታል:: የበፊት ስሙ ያስደነብራቸዋል:: ታሪክ ጠላታቸው ነው:: ግብግብ የሚገጥሙት ከስም ጋር ነው:: ከታሪክ ጋር ነው:: ስም ለመቀየር ሲሉ ህዝቡን ይሄ ማለት ስድብ ነው እያሉ ይሰብኩታል:: ተቆረቆርንልህ ለማለት ይሆን? የስም ለውጥ የትግል አላማቸው ይሆን? እንጃ!!!

ይህ የስም ለውጥ በቀደመው የደርግ ስርዓት ጊዜም ነበር:: ትምህርት ቤት እንኳን ሳይቀር እቴጌ መነን የካቲት 12፣ ቀዳማዊ ሀ/ስላሴ ኮከበ ጽባሕ... በመሳሰሉት ተለውጠዋል:: አሁን ደግሞ አዋሳን ሀዋሳ፤ ጅጅጋን ጅግጅጋ ያሰኘ ለውጥ አለ:: የስም ለውጥ:: ይህ የስም ለውጥ ወረርሽኝ በሕንድም ተከስቷል:: የከተሞቻቸውን ስም ቦምቤይ ወደ ሞምባይ...ካልካታ ወደ ኮልኮታ.. ተለውጠዋል:: ስም ለውጥ የአለም ፖለቲከኞች ገጸ-በረከት ይሆን?

የእኛዎቹ ለየት የሚለው ሁሉን ስድብ ነው ማለታቸው ነው:: ግን..ግን ሁሉን ነቅፈን፣ ሁሉን ስድብ ነው ብለን እንዴት እንዘልቀዋለን? ቃላትን ተስማምተን እንደምንጠቀምበት አመለካከታችንን ከቀረፅንበት መጥፎውን ጥሩ፣ ጥሩውን መጥፎ ልናደርገው እንችላለን:: ቃላት እንዳሰበጣጠሩት ይሰበጣጠራል:: ጥሩ ብለው በጥሩ ከተረጎሙት ጥሩ ይሆናል:: በመጥፎም ካሉት እንደዛው:: ዋናው የእኛ ጭንቅላት ነው:: ስድብ ብሎ ካጸደቀው አዲዮስ..:: ስድብ አይደለም ካልንም እንደዛው:: የአንድን ብሄር መጠሪያ ስድብ ነው ብለው ስሙ እንዲቀየር ብዙ ትግል ይደረጋል:: ማንነቱን እንዲያጣ ስሙ እንዲቀይር ሳይሆን ኑሮው እንዲቀየር ቢሆን ያ-ትግል ጥሩ ነበር:: ስም መለወጥ ለእኔ ግን ሽንፈትን መቀበያ እንጂ ሽሽት ማሸነፊያ መንገድ አይደለም:: ማሸነፍ የማደርገው በዛው ስም ሆኜ ታግዬ በልጦ መገኘትን ነው:: ስም መቀየር ለህዝቡ ኑሮ ምን ይሆን ጥቅሙ? የዕለት ጉርስ ይሆናል?

ያለሁበት መኪና ጉዞውን ቀጥሏል:: የእኔም ሀሳብ በየቦታው መኳተኑን ተያይዞታል:: ለጥ ያለውን መንገድ «መጣሁልሆ..» እያለ ሰንጥቆት ወደፊት የሚጓዘውን ሚኒባስ ፍጥነት ፈርቶ ወደኋላ የሚወረወረውን ጥቁር ንጣፍ መለስ እያልኩ እያየሁ ነው:: መተሀራን አቋርጠን አለፍን:: ሀብሀብ፣ ከስል መንገድ ዳር የሚሸጡትን እያየሁ..አዋሽ ደረስን:: አዋሽ መንገዱን ካልሳምኩ ብሎ ያሞጠሞጠ ይመስላል:: መንገዱን ተጠግቷል:: ውሀው ሲያዩት ከያዘው ቦታ አንዛር ያስፈራል:: ፀጥ ለጥ ብሏል:: ፀጥ በፀጥታ...ንፋስ ከሚያንቃንቀው በስተቀር በጸጥታ የያዘውን ቦታ ይዞ በይዞታው ኮርቶ ተኝቷል:: ዝምታውም ያስፈራል - ግርማ ሞገስ አላብሶታል:: አንቀላፍቷል:: የጸሀይዋን ብርሀን ተቀብሎ ማራኪ የቀለማት ህብረት ፈጥሮ መልሶ ያንጸባርቃል:: ውበት አለው:: አዋሽ ጉልበተኛ ነው:: በል ያለው የጠገበ ቀን በማን አለብኝነት መንገዱ ላይ ወጥቶ ይንጎማለላል:: አካባቢውን ያውካል፤ ጉዞ ያስተጓጉላል:: ያሻውን ጠርጎ ይሄዳል:: ማን ሀይ ባይ አለው? አዋሽ የጠገበ ሞልቶ የተረፈ ጊዜ ጥጋቡን በልክ አያደርግም:: ጥጋቡ አይጣል ነው:: የአካባቢውን ነዋሪ ሁላ ያሸብራል:: ይበጠብጣል:: ቤት ንብረት፣ ህይወት...ጠራርጎ ይወስዳል:: የራበው የከሳ፣ አቅም ያጠረው ጊዜ መንገዱን ልሳም ብሎ ማሞጥሞጡ ይቀርና እጥር እፍር፣ ኩምትር፣ ስቅቅ፣ ስብስብ፣ ብሎ ይቀመጣል:: ያኔም ቢሆን የአካባቢውን ነዋሪ ይጎዳል:: ምን የአካባቢውን ብቻ የምርቱን ተጠቃሚ ሁሉ ይጎዳል:: እኔ ሳስበው አዋሽ ጥጋቡም፣ ረሃቡም መከራ ነው::

«አዋሽ ሲያሻው አጉራሽ
ሲያሻው ነካሽ..» ብለው ያስኬዳል::

እንዲህ..እንዲህ እያልኩ ሀሳቤን ስደረድር የባቡሩ ሀዲድና የመኪናው መንገድ የሚተላለፉበት ቦታ ደረስን:: ትንሽ ቤቶች አሉባት:: ከተማ መባል ትችል ይሆን? ምንም ብትሆን በፊት.. በፊት የታወቀች የፍተሻ ቦታ ናት ሲባል ሰምቻለሁ:: ኮንትሮባንዲስቶች ልባቸው የፍርሃት አዶከብሬውን የሚደልቅበት ነበረች:: ሳይቀናቸው ቀርቶ ሲነጠቁም በሀዘን የሚቆራመዱባት፣ በሀዘን..በእንባ የሚራጩባት፣ ባዶ እጃቸውን የሚቀሩባት.. ዋይታ የሚነግስባት፣ የፊናንስ ፖሊሱን የሚለማመጡባት፣ ይዞ ወይም ባዶ እጅ መግባት የሚወሰንባት ነች:: ቀንቷቸው ሲያሳልፉ በደስታ ጮቤ የሚረግጡባት፣ ብዙ የታየባት ቦታ ነች ሲባል ሰምቻለሁ:: እኛ ያለንባት ሚኒባስ ግን ቆም ብላ ስመ ፍተሻ ነካ..ነካ ተደርጋ አለፈች:: ፍተሻ ከተባለ ማለቱ ነው::

አለፍ እንዳልን ሁለት ታንኮች ተራርቀው አልበቅል እንዳለ ችግኝ እርሻ መሀል ተተክለዋል:: ታንክ ዘርተን ለማብቀል ሙከራ ላይ ያለን ያስመስለናል:: ከሁለት አመት በፊትም እዚሁ አይቻቸዋለሁ:: ሶማሊያ በወረራው ጊዜ እዚህ ድረስ መጥቶ ነበር እንዴ? የያኔ ወይስ የ1983 ዓ.ም. ቅሪቶች ናቸው? ሴትዮዋን ጠየኩኝ::





«እንጃ ልጄ፣ አስታዋሽ አጥተው እዚሁ ቆመው አያቸዋለሁ እንጂ የመቼ ቅሪቶች እንደሆኑ አላስታውስም::» ለስንት አመት ቆመው ይሆን? ስንት የሀገር አንጡራ ሀብት ፈሰባቸው ይሆን የተገዙት? ከዚህ በኋላስ ምን ይሆን መጨረሻቸው? ዝገትን ማስተናገድ ወይስ ሌላ እጣ ፋንታ አላቸው? ዝልግልጉን መንገድ ተያይዘነዋል:: እኔም ባየሁት ባላየሁት በሀሳብ ተወጥሬያለሁ:: አፌ ያላምጣል፣ ጥርሴ ያኝካል:: አእምሮዬ በሀሳብ ተወጥሯል:: ውስጤ ፍርሃት..ፍርሃት ብሎታል:: ስደትን እንኳን ከሀገር ውጭ ሀገር ውስጥ አለመሞከሬ ነው ጭንቀት የለቀቀብኝ::

ከርቀት አረንጓዴ ድሪያ የለበሰች የምትመስል ለም ቦታ አየን:: «አሰበ ተፈሪ» ደረስን ማለት ነው:: ከዚህ በፊት የመጣሁ ጊዜ ያየሁባት አረንጓዴነት አሁንም አለ:: ሁሌም አረንጓዴ ትሆን ይሆን? ወይስ በተመሳሳይ ወቅት ነው የመጣሁት? የተማሪ መለቀቂያ ሰዓት ስለሆነም ዘውትር ግርግር የማይለያት አሰበ ተፈሪ ሞቅ ደመቅ ብላለች:: ሐረር ገብተን ለማደር ስለተነጋገርን ቀጥታ በሌላ ሚኒባስ ወደ ሐረር ነው ያመራነው::

ተረተሩን አቀበቱን አቆራርጦ ጋራ ዞሮ ተጠማዞ ጉዞ:: ጉዞ ጉዞን እየወለደ ሂደቱ ቀጥሎ ቦረዳ ደረስን:: ግራና ቀኝ ጋራው ላይ ባሉት የጫት እርሻዎች ነው ሁሌም የማውቀው:: ቀጥሎ ሂርና ደረስን:: ሂርና በተራራ የተከበበች ከተማ ናት:: ወደ ድሬደዋና ሐረር ስወርድ ሁሌም የሚታወሰኝ የገበየሁ አየለ «ጣምራ ጦር» መጽሐፍ ነው:: በ1960ቹ መገባደጃ ላይ በዚያድባሬ የተደረገው ወረራን ቁልጭ አርጎ የሚያሳይ ምርጥ መጽሀፍ:: ትረካውን በልጅነት ቢሆንም የሰማሁት የማይረሳ ትዝታውን ውስጤ ተክሎ አልፏል:: በተለይ በሪሁን የተባለው ገጸ-ባህሪ ፈጽሞ ልረሳው በማልችለው ሁኔታ ውስጤ ቀርቷል:: ከሴትዮዋ ጋር ብናወራም አሻግሬ ማዶ..ማዶውን ማየቴን አልተውኩም:: የማየው ሁሉ ማርኮኛል:: ውበት ነዋ:: ውበት ማየት ማድነቅ ማን ይጠላል? ያውም የተፈጥሮ ውበት::

ወደ ድሬደዋ ከተማ መገንጠያ ደንገጎ ላይ ስንደርስ ሐረር አንሄድም ብለው አራት ሰዎችን አውርደውን ለሁላችንም አምስት..አምስት ብር መለሱልን:: በጣም ብናደድም «ምን ማድረግ ነው?» ብለው ሴትዮዋ ሲበሰጫጩ ላለማባባስ ዝምታን ጊዜያዊ ዘመዴ አደረኩ:: «ዝም አይነቅዝም..» ይባል የለ? ብርዱ ደግሞ አውቆ ይመስል አየለ:: ከብዙ ጥበቃ በኋላ ብቅ ያሉት ትናንሽ ፋሚሊ ፔጆ መኪናዎች «አወዳይ..አወዳይ» ይላሉ:: ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ሆኗል:: እዛው አካባቢ ለማደር አሰብኩ::

«አሄሄ..እዚሁ ማደራችን ነው?» ከአፋቸው ከመውጣቱ ከድሬደዋ በኩል እየከነፈ የመጣው ሚኒባስ «አወዳይ...ሐረር» አለ:: ካለው ሰው ጋር ተጋፍተን ገባን:: አንዱን በአንዱ ላይ ደራርበ ጫነን:: ጨለማ ስለሆነ በቅጡ

ባይታየኝም ሐረር ስንደርስ በየበረንዳው የተቃመው የጫት ገረባ ተከምሮ ያስገርማል፡፡ ገና በየበረንዳው ተቀምጠው የሚቅሙትን ያየ «ሐረርን ጨለማ ከቃሚዎቿ ሊያላቅቃት አይችልም፡፡ ቁጥራቸውን ይቀንሰው ይሆናል እንጂ» ቢል ስህተት አይደለም፡፡ ሐረር ቀን ብቻ ሳይሆን ምሽትም ግርግር የነገሰባት ውብ ነች፡፡





# - 2 -

# ሐረርን ማለፍ

እየተሰደድን እስከመቼ
ተንከራተትን ወገኖቼ
እስከመቼ ነው እስከመቼ
ሀገር እያለን በሰው ሀገር
ውሻ ሆነን የምንኖር?

ከመኪና የወረድንበት አቅራቢያ አንድ ሆቴል መኝታ ተከራየን፡፡ መንገድ ካገናኘን ሴትዮ ጋር ጎን ለጎን ነው የያዝነው መኝታ፡፡ «እራት ነገር ፈልገን እንብላ» ብለውኝ ከያዝነው ክፍል ወጣን፡፡ ደጋግመው «አንተን የሚበላልጡ ልጆች አሉኝ» ስላሉኝ «እናትህ ነኝ አትፍራ» የሚሉ መሰለኝ፡፡ እንደ እናቴም አየኋቸው፡፡ እራታችንን አጣጥመን እንደጨረስን «እናንተ ወጣቶች ከቃማችሁ በኋላ ጨብሲ ብላችሁ የመጠጥ ጠርሙስ ታንቃላችሁ፡፡ እኛ ሻይ በወተት፣ ቃህዋ ለሰውነት እንዲሆነን እንጠጣለን፡፡ ድንገት መጠጣት ከፈለግህ ብዬ ነው፡፡» ነፃ መሆናቸው ደስ አለኝ፡፡

«መጠጥ እንኳን አልጠጣም፡፡»

«ለምን?»

«ያመኛል አልወድም»

«አይ!!..ሴት ልጆቼ ሁሉ አግብተዋል እንጂ እድርልህ ነበር፡፡ ዘንድሮ ደግሞ የማይጠጣ ወንድ መች ይገኝና ሁሉ ጨላጭ ነው፡፡ እንዲህ አይነት አማች አይገኝም፡፡ አንተ ግን እንዴት አትጠጣም?» በመገረም ይሁን ዋሸሁ ብለው መስሏቸው ትኩር ብለው ያዩኛል፡፡ እንደማትሪክ ተፈታኝ ነው የሚያጠኑኝ፡፡

«ለምን እንደሆነ አላውቅም ስጠጣ ያመኛል:: ስለሚያመኝ በተፈጥሮ ጠላ እንኳን ጠጥቼ አላውቅም:: ይሄ ነገር ለብዙ ሰው ይገርማል:: ማስቱ እንኳን..» አቋረጡኝ::

«አግብተሀል እንዴ? ሴት ልጆቼን ድሬ ጨረስኩ ብዬ የምቆጨው?» «አግብተሀል እንዴ? ሴት ልጆቼን ድሬ ጨረስኩ ብዬ የምቆጨው?» በቀልድ ቢሆንም ለጥያቄያቸው መልስ መስጠት እንዳለብኝ ተሰማኝ:: ግን የምለው ግራ ገባኝ::

«አግብቼ ነበር:: አንድ ልጅም አለኝ»

«ምነው አግብቼ ነበር አልክ ፈት ነህ እንዴ?»

«አዎ! በቃኝ ብላ ወደ ቤተሰቦችዋ ሄደች::» ሁኔታው ከፊቱ ድቅን አለብኝ:: «አራት ወር ሞላት» ለራሴ ያሰብኩ መሰለኝ ለካ ቃል አውጥቻለሁ::

«አይ ትንሽ ጊዜ ነው» አሉኝ ለእሳቸው ያወራሁ መሰሏቸው:: «ታረቅ ልጄ፤ ልጅ ያለው ሰው ደግሞ ተለያይቶ መቅረት የለበትም:: ለልጅ ሲባል መቻቻል ነው::»

«ቢሆን ደስ ባለኝ ነበር:: እወዳታለሁ:: እየወደድኳት ነው የተለየችኝ:: አሁን ደግሞ ይባስ ራኳት..» ተስፋ የመቁረጥ ሁኔታ ድምጼ ውስጥ በጉልህ የተንጸባረቀ መሰለኝ:: በትክክልም ነበረበት::

«ከወደድካት ለምን ተለየሀት? መቼም ወንዶች አታርፉ..»

«እ..እ..እ..!!» አቋረጥኳቸው በስሜት:: እንደዚህ አይነት አባባል አይስማማኝም:: «መቼም ወንዶች ሲሉ በጅምላ ባይደፈጥጡን ጥሩ ነበር:: ደግሞ እንደዛም ከሆነ ሴቷስ ቢሆን መች ታርፍና? ወንዱ ብቻውን አይባልግ..ግን የእኔና የዚድ ጾብ በዚህ አይነት አይደለም:: ቤተሰብ በመካከላችን ገባ:: እኔ ስራዬም ትንሽ አስቸጋሪ ነው:: እነሱ ደግሞ ሀሳባቸው ሌላ ነው፤ ያለብኝን ችግር አልተረዱኝም:: ሁሉ ተደምሮ ትዳራችን በእግሩ ሊቆም አልቻለም:: ህፃኑ ልጄን ጠረኑን እንኳን ሳልጠግበው የልጅነት ጣዕሙን ሳላጣጥመው ጨዋታውን ሳላየው..ይዛው ሄደች:: እንደናፈኩት እኔም ትቼው እየራኩ መጣሁ ከዚህ...» በረጅሙ ትንፋሽ ምጌ ሳስወጣ ተንቆርዝዞ የነበረው እንባዬ ግድቡን ጥሶ ለጥፋት እንደሚንደረደር የወንዝ ውሃ ቁልቁል ተንኳለለ::

እንደ እናት አንገቴን እቅፍ አድርገው ደረታቸው ላይ ልጥፍ በማድረግ ፀጉሬን እያሻሹ ያባብሉኝ ጀመር:: እሳቸውም እንባቸውን በሻርፓቸው ጠራረጉ:: «ቤተሰብ እንዴት መካከላችሁ ገብቶ ትዳር ያፈርሳል? ከወደደችህ ትዳሯን ከፈለገች እነሱ ያሏትን ሰምታ ለምን ጥላህ ሄደች? ሌላ ችግር





ቢኖር ነው::» መልሱን ከእኔ አልጠበቁም:: እሳቸውና የ37 ዓመት ባለቤታቸው መካከል ቤተሰብ ምን ያደርግ እንደነበር ረጅሙን የትዳር ህይወታቸውን ማንካ እያነሱ መከሩኝ፣ ዘከሩኝ:: ዋጋ የለውም:: ሁሉንም ችለው የሚያሳልፉት ለልጆቻቸው ሲሉ መሆኑን አወሩኝ:: አሁን ባላቸው በህይወት የሉም:: በሞት ከተለዩዋቸው 5 ዓመት ሆኗቸዋል:: ብዙ መክረው ትዳሬን መልሼ እንድይዝ፣ ጎጆዬን እንዳቃና ለመኑኝ:: ልመናቸው አንጀቴን በላው::

«እንዲህ አይነት ጥሩ ሰው አለ?» በውስጤ ነው ያልኩት:: የሐረር ሰው እንዴት ልበ-ቀና ነው? ያውም መንገድ ላይ ተዋውቆ እንዲህ የሚሆን ያለ አልመሰለኝም:: ስራቸው፣ ድርጊታቸው ሁሉ የእናትነት ነው:: ነገርኳቸው:: መልሶ ጎጆ የማቃናቱ ነገር እንደማይሆን፣ ሀገር ለቅቄ እየጠፋሁ መሆኑን በግልጽ ነገርኳቸው::

«ቤተሰብ የገባበት ምክንያት ምንድን ነው? ከመነሻው ችግር ነበር ማለት ነው?» ሲሉ ጠየቁኝ:: ጥያቄያቸው ከበደኝ:: ግራ ገባኝ:: ልንገራቸው አልንገራቸው ስል አመነታሁ:: «ምነው ዝምታ ዋጠህ?» ሲሉ አከሉልኝ::

«አይ ታሪኩ ብዙ ነው:: ከመነሻው ውስብስብም ነው» አልኩ እንደዘበት ላለማውራት ፈልጌ:: ግን ፈጣን አስተሳሰባቸውና መልሳቸው ገረመኝ::

«ውስብስብ ያልከው በእንግሊዘኛ ነው የምታወራልኝ? መቼም አማርኛ ከሆነ ይገባኛል:: ቢረዝም እንቅልፌ መጣ አላልኩም ምን አስጨነቀህ?» ጠዋት መንገደኛ መሆናችንን ረስተውታል መሰለኝ:: እሳቸው መኖሪያቸው ጅጅጋ ድረስ ሲሆን እኔ መጨረሻው የት እንደሆነ የማላውቀው ቦታ እንጓዛለን:: መተኛት እንዳለብን ውስጤ አምኗል:: ለነገሩ እንቅልፍ አልመጣብኝም:: እሳቸውም ከመስማት ፍላጎት ጋር ፍጥጥ ብለዋል:: ወይ ዕዳ..!!! በቃ!!! ካልነገርኳቸው እንደማይለቁኝ አውቄያለሁ:: የውሸት ታሪክ ፈጥሬ ልነግራቸው አልፈለኩም:: እናት ይዋሻል እንዴ? ከእናት ይደበቃል? እንደ እናቴ አይቻቸዋለሁ:: እሳቸውም እንደ ልጃቸው አይተው ሆድ ብሶኝ ሳለቅስ ጸጉሬን እያሻሹ አባብለውኛል:: እኔም ደረታቸው ላይ ተለጥፌ ጠረናቸውን ምጌ በእናትነት አጣጥሜያለሁ:: በአንድ ቀን ይህን አይነት ስሜት ስለጫሩብኝ:: በተፈጠሮ ጥሩ ሰው ሆነው ጥሩነት ዘርተውብኛል:: ውስጤን ከፍቼ ላሳያቸው ሁሉን ልነግራቸው ፈለኩ:: ሊጎዱኝ እንደማያስቡ አመንኩ:: ምን አድርገው ይጎዱኛል? ምንም:: እግዚአብሄር ያውቃል::

ባልነግራቸውስ? ቅር ይላቸዋል:: ቅር ከሚላቸው..ብነግራቸውስ? ምን የረባ ታሪክ አለኝ? ተያየን፣ ተዋወቅን፣ ተፋቀርን..ተጋባን በቃ! መንገር ይጠበቅብኛል:: ግራ ተጋባሁ በመንገርና ባለመንገር መካከል ሆኜ ጀመርኩ::

‹‹እኔና ዘለቃሽ ትውውቃችን ከህጻንነት ጀምሮ ያደኩበት ጊቢ ውስጥ ነው። የቤተሰቦቿ ኑሮ ጫንጮ የሚባል ቦታ ነው። ከአዲስ አበባ አርባ ኪሎ ሜትር በጎጃም መስመር ወጣ ብላ የምትገኝ አነስተኛ ከተማ ናት። አያቷ ነፍሳቸውን ይማረውና አንድ ጊቢ ውስጥ ነበር የምንኖረው። የወሎ ሰው ናቸው። ጣይቱ አሊ ይባላሉ..» አቤት ፍጥነታቸው.. ወዲያው

«ከሙስሊም ነው የተጋባሽው? ክርስቲያን ሆነህ?» ንግግሬን አቋርጠው ጠየቁኝ።

«ምን ይደረግ ፍቅር ነው» የሚል ምላሽ ሰጥቼ ወደ ንግግሬ አመራሁ። «..እና አንዳንድ ነገራቸው ደስ ይለኛል። አብሶ እህቴን ሲጠሯት ከእኛ ቤት የማይስቅ የለም። ሰፈር የምትጠራበት ስሟ ሚሚ ነው። በት/ቤት የምትጠራው ፅዮን ተብላ ነው። «..ሚሚ ጺዮን..» ይሏታል ሁለቱንም ደርበው። ያኔ እንስቃለን። በመሀል ታመሙና ሞቱ። ጊቢ ውስጥ የምንኖረው ሁሉ የቀበሌ ቤት ውስጥ ነው። ከዛ የልጅ ልጆቻቸው 3 ሆነው ቤቱን ለቀበሌ ላለመመለስ ይኖሩበት ጀመር። ከዘለቃሽ ጋር ለመጀመሪያ ጊዜ የተያየነው..የለቅሶው ዕለት ነው። ..የትውውቃችን ሁኔታ በሀሳቤ ታየኝ። ጊቢያችን ታወሰኝ። በዚህ ሰዓት እናቴ ምን አይነት ስሜት ውስጥ ትሆን? ስል አሰብኩኝ። ነገሮች ሁሉ እንዲህ እንደተምታቱብኝ እስከመቼ.. ፍርሃት ፍርሃት እንዳለኝ የት ድረስ እጓዛለሁ? ከአሁኑ ናፍቆት መሸበብ ከጀመረኝ መጨረሻዬስ ምን ይሆን? ያስፈራል። ለመረጋጋት ፈለኩ እና ለሽንት ተነስቼ ወጣሁ። ፊቴን ተጣጥቤ ተመለስኩ። ገና ከመቀመጤ..

‹‹እሺ!..ቀጥልልኝ..›› አሉ።

«..አንድ ወንድሟና እህቷ አብረዋት ይኖራሉ። እነሱን ለማስተዳደር እሷ ታላቅ ነችና ተሯሩጣ ትሰራለች። በወጣትነቷ ሀላፊነት ተሰምቷት እሷ ታላቅ ነችና ተሯሩጣ ትሰራለች። በወጣትነቷ ሀላፊነት ተሰምቷት ይህን በማድረጓ አደንኳት። ስለህይወት ውጣ ውረዷ ስትነግረኝ አባቷ አቶ ጉዲሳ አውራጃ አስተዳደር ሆነው ሲሰሩ ከእሳቸው ጋር ያልዞረችበት ክፍለ ሀገር የለም። ወለጋ ደንቢ ዶሎ እያለች ታመው ለህክምና ወደ አዲስ አበባ ይዛቸው መጣች። ያልታደለች ከአውቶቡስ ተራ ወደ 4 ኪሎ/ያኔ *ስያትዋ በሀይወት ነበሩ/* በኮንትራት ታክሲ ይዛቸው ስትመጣ እንደደገፈቻቸው ትከሻዋ ላይ ራሳቸውን ዘንበል እንዳደረጉ ይህችን አለም ተሰናበቱ። በዚህን ጊዜ ያ-ረዳት የሌለው ቤት ሀላፊነት በእሷ ላይ መውደቁን አመነች። ለዛ እንደሆነ ቀን ከሌት የምትሰራው ነገረችኝ። ውስጤ ገባች። እኔም የኑሮ ውጣ ውረዱን ከልጅነት ጀምሮ ቀምሼዋለሁና የሷ እንግልት በቅጡ ተሰማኝ። ዘለቃሽንም በዚህ ምክንያት ቀረብኳት። መቀራረባችን ጠንክረና ወደ ፍቅር ተቀየረ። አልፎ ተርፎ ለረጅም ጊዜ ተጠናንተን ለመጋባት በቃን።»

«ለረጅም ጊዜ ምን ያህል?» አቋርጠውኝ ጠየቁ።

«ፍቅር ከጀመርን ለዘጠኝ ወር ያህል ምንም አናውቅም።»





«ገዳም ነበር ያላችሁት?» ዳግም አቋረጡኝ። አባባላቸው አሳቀኝ።

«እስክንጠናና ነው።» አልጣማቸውም። አባባሉ የጤነኛ አልመሰል አላቸው መሰል አስተያየታቸው ተለየ። «ምንድን ነው የምትጠናኑት? ማዕድን ፍለጋ ነው የያዛችሁት? ወይስ እዚህ እኛ ጋ ኡጋዴን የሚፈለገውን ነዳጅ ስትፈልጉ ነው? ዘጠኝ ወር አንድ ልጅ ተረግዞ የሚወለድበት መሆኑን ረስታችኋል? ይህን ያህል መጠናናት ምንድን ነው? ፍቅር ስንጨርስ ነው የተጋባነው አትሉም?» የሚሉ መሰለኝ በውስጣቸው።

«በእኛ ጊዜ ቤተሰብ ነው የሚመርጠው። አሁን ነፃ ስትሆኑ ጣጣችሁ በዛ።» በዚህ ዙሪያ ብዙ መከራከር አልፈለኩም። ሌላ ታሪኬንም አወጋኋቸው። እያወራኋቸው እንቅልፍ አይኔን ልክደን አልክደን ሲታገለኝ በል ተኛ ብለው አሰናበቱኝ። ከእሳቸው ተለይቼ ወደ መኝታዬ ከሄድኩ በኋላ ሀሳቤ በየአቅጣጫው ሲኳትን ስገላበጥ እንቅልፌ የት እንደገባ ግራ ገባኝ። አስታውሳለሁ እናቴን፣ ልጄን፣ በትንሽ ፀብ የተለየኂት ሚስቴን፣ ወደፊት በስደት ስለሚገጥመኝ... ስለምሄድበት የማላውቀው ሀገር ሳወጣ ሳወርድ ሊነጋጋ «አላህ ወ አክበር» አለ። ከዚህ በኋላ ብተኛ ጥሩ አይደለም። ምናልባት አንድ ሰዓት የሞላ ላልተኛ እችላለሁ። ወረቀት አውጥቼ ልጽፍ ፈለኩ። ፍላጎት ብቻውን ምን ሊያመጣ? በምን ምክንያት እንደሆነ ሳላውቅ ጭንቅንቅ አለኝ። ሲነጋጋ ግን ተሸነፍኩና ተኛሁ።

አንድ ሰዓት የሚሞላ ሳልተኛ ሰማይ የአህያ ሆድ ሲመስል በሚባልበት ሰዓት «ተነስ» ብለውኝ ስንወጣ የማውቃት..ሐረር አልመስልህ አለችኝ። ራሴን ወቀረኝ የሚሉት አይነት ይደስቀኛል። አይኔን እያሻሸሁ ከደንገዝጋዛው ብርሃን ጋር ተጋፈጥኩ። ለወትሮው ሐረርን እወዳት ነበር። አሁን ሳልቆይባትና ዞር..ዞር..ሳልልባት ላልፍ በመሆኑ ተናደድኩኝ። በጠዋት መሆኑ ይሁን ቅዝቃዜው ውበትዋን ነፍጓታል። ጥርሷ አልቆ በድዷ እንደምትስቅ አሮጊት ፈገግታዋ ወይቧል። አይናፋር መስላለች። ከአየሩ ቅዝቃዜ ጋር የሰዉ መሸፋፈን ሐረርን ጭር አድርጓታል። መናኸሪያ ውስጥ ገብተን ወደ ጅጅጋ የሚሄደውን መኪና መፈለግ ጀመርን። አግኝተን ስንገባ በብርድ ጥርሱ የማይንቀጫቀጭ ከሌታውን ያላቆመ፣ አንገት ልብስ ያላደረገ የለም። መናኸሪያው ጊቢ ውስጥ ግንብ ተጠግታ ከተሰራችው «ካፍቴሪያ» የሚለው ስም የሚበዛባት ሻይ መኮመሪያ በግፊያ ሻይ ይቸበቸባል። ልቤ ፈለገ። እሳቸውን ጥሎ መውረድ ከበደኝ።

ጉዞ ጀመርን። ከከተማ ስንወጣ ፍተሻው ብጥርጥር ያለ ነው። ከሐረር ከተማ አልፌ ስለማላውቅና አዲስ ስለሆነብኝ አፍጥጬ ነው የማየው። በሶማሊያ ወረራ የተዋጉበትን ታሪካዊ ጋራዎች..በስም ያወኳትን ባቢሌ..ከዛም ባሻገር የመኖሪያ ዳስ በየጫካው እያየሁ ጅጅጋ ከቀኑ ስድስት

ሰዓት አካባቢ ደረስን:: በጉዞዬ አብረውኝ የነበሩት «ወ/ሮ..» መናኸሪያ ከመድረሳቸው በፊት ልጄ እንውረድ ቤቱን ላሳይህ ቢሉኝም ጉዞዬን መቀጠል ፈልጌ እምቢኝ አልኳቸው:: ሌላው ቀርቶ ጅጅጋ እንዳለች የማውቀው ዘመዴን እንኳን ማግኘት አላሰብኩም:: ቤቷን አላውቀውም:: ግን አዲስ አባ ደውዬ አድራሻ ተቀብዬ ማግኘት ስችል ጸጥ ብዬ ማለፍ ነው የፈለኩት:: ጊዜ መሻማት ነው አቅዴ:: ጠልጠል ያረደኳት ቦርሳዬን አይተው ይሁን ለአካባቢው ጸጉረ ልውጥ በመሆኔ ምድረ ደላላ አላሳልፍ አለኝ:: እንደ ጉንዳን ሰራዊት ከበውኝ ‹‹እ..እ....አረብ ሀገር ነህ? አስተማማኝ በሆነው በእከለ...» እያሉ አዋከቡኝ:: ሌሎቹን ከበው ሲያዋክቧቸው «አዎ! ..አረብ ሀገር ነው» ሲሏቸው ወደ አንድ ቦታ ይወስዷቸዋል::

«ወደ አርትሼክ ነህ?..ወደ ሶማሊያ ከሆንክ ወደብ አድርሰን ጀልባ እናሳፍርሀለን:: ና አረብ ሀገር ነው የፈለከው እዛው የሚያደርስህ ሰው አለ:: በማግኘት ልተባበርህ?» በአሰልቺና ተደጋጋሚ ጥያቄ አጣደፉኝ:: የሁሉንም እርዳታ እንደማልፈልግ ነገሬ ግርግሩን ለማብረድ ከመናኸሪያው ወጣሁ:: አልተው እየተከተለ «እኔ...ልርዳህ» ያለ አንድ ችኮ ቢጤ ተወኝ ብለው አለኝ:: «ምን ትረዳኛለህ? አይን የለኝም ትመራኛለህ? ቸገረኝ አልኩ? የምረዳ አይደለሁም:: ከዚህ በኋላ እንዳትከተለኝ..» ብዬ አፈጠጥኩበት:: የሚገባው አይነት አይደለም:: ዞር እንዲልልኝ ስልክ ቤት ፍለጋ ጀመርኩ:: አሁንም ይከተለኛል:: ፖሊስ ከፊት ለፊት ሲመጣ «እንዳላሲዝህ አለበለዛ ከአጠገቤ ሂድ» አልኩት:: ለጊዜው ዞር አለ:: ወደ አዲስ አበባ የሚደወልበት ሱቅ ገብቼ ቤተሰብ ጋ ደውዬ የዘመዴን ሆቴል ስም ማን እንደሚባል ጠየኩ:: መልሰህ ደውል የሚል መልስ ተሰጥቶኝ ስልኩ ተዘጋ:: ፖሊሱ ከኋላዬ ነካ...ነካ አድርጎ «ና ወዲህ» ሲለኝ የሰራሁት ነገር ባለመኖሩ «ምን ፈለክ?» አልኩት:: መርበትበት እንደሌለብኝ አመንኩ:: ደፋር ለመምሰል:: በእውነቱ ግን ልቤ በጣም ፈርቷል:: ተያዝኩ ነገሮች ሁሉ አከተመላቸው--

«ወደ አረብ ሀገር ልትሄድ ደላላ ስታናግር ነበር ተብሏል ስለዚህ አሁን በቁጥጥር ስር ነህ?» አለኝ::

«ድንቄም በቁጥጥር ስር ወገናቸውን ለማስቃየት በድለላ ስራ ተሰማርተው የሚዘርፉትን መቼ ተቆጣጠራችሁ? አብራችሁ እየዘረፋችሁ» አልኩ በልቤ:: በአፌ ግን ምን አቀበጠኝና..? «እረ! አክስቴ ጋ ነው የመጣሁት» አልኩት::

‹‹ማነች አክስትህ?››

‹‹ጸሀይ ትባላለች:: የሆቴሉ ስም ጠፍቶኝ ነው አዲሳባ የደወልኩት::››

‹‹አይመስልም ይሄ ልጅ አይቶሀል..›› ብዙ ባስረዳውም ማን ሰምቶኝ?

«እሺ ደግሜ ልደውልና የት እንደመጣሁ ታውቃለህ..» አንድ አይነት ቋንቋ እያወራን መግባባት አቃተን:: ልጁና ፖሊሱ ግን ያግባባቸው ቋንቋ እንዳለ ገመትኩ::





በእርግጥም ነበር:: ወደ ፖሊስ መምሪያው ወሰዱኝ::

«ወይኔ!!..እዚሁ ተያዝኩ:: አለቀልኝ ከፊተሹኝ መታወቂያዬን ያገኙታል በቃ!..» ስል ተጨነኩኝ:: እነሱ ደግሞ የሚፈልጉት ሌላ ነበር:: ለሚጠይቁኝ ሁሉ አግባብ ያለው መልስ ሰጠሁ:: ደላላውና ፖሊሱ ጥቅም ያስተሳሰራቸው ስለሆኑ ሰሚ አላገኘሁም:: ቅያሪ ልብስ የያዝኩባት ትንሽዬ ቦርሳ በክዳኗ በኩል ኪስ ነገር አላት:: ዚፕዋም ጭምር ሙሉ ለሙሉ ጥቁር ስለሆነ በአጋጣሚ ኪሱን አላወቁትም:: ውስጡ ከኢትዮጵያ ነፃ ፕሬስ ጋዜጠኞች ማህበር መታወቂያ ጀምሮ የተለያዩ መረጃዎች እና ለጉዞ እንዲሆነኝ የያዝኩት ብር ሁሉ አለ:: ብርብር ሲያረጉ በልቤ ፈጣሪዬን እማጸን ነበር:: ምንም አላገኙም:: ጋረደልኝ::

መቶ አለቃ ይሁን ም/መቶ አለቃ ማዕረጉን አሁን የማላስታውሰው ወንደሰን የተባለ ለሞያው የተሰለፈ ፖሊስ ጋ ሲያቀርቡኝ.. «እነሱ እንደሚሉት ከሆነ ወደ አረብ ሀገር ልትሄድ ደላላ ስታፈላልግ ነበር?» አለኝ በመርማሪ አይኑ ውስጤን እያጠናው::

«ወንድሜ አንተ ትረዳኛለህ ብዬ አስባለሁ:: እሱ እኔን ሲሰማ ፈፅሞ አልፈለገም:: ከመቶ ብር ያነሰ ነው ኪሴ ያገኘው ይቺን ብር ይዤ አረብ ሀገር ለመሄድ እነሳለሁ? የማስብስ ይመስልሀል? እንዴት ብዬ?» ጥያቄውን በጥያቄ መለስኩለት ውስጤ በፍርሃት እየተናጠ:: ላብ ግንባሬ ላይ ችፍ ማለት ጀምሯል:: ለምን አልፈራ?

«ታዲያ ለምን መጣህ?»

«ይቅርታ መቶ አለቃ እንደ ኢትዮጵያዊነቴ ወደፈለገኝ ቦታ ብሔድ ወንጀል አልመሰለኝም ነበር:: ወንጀል ነው እንዴ? ከዚህ በፊት በተለያዩ ክልሎች ዞሬያለሁ ወንጀል ሆኖ ያስጠየቀኝ ቦታ አላጋጠመኝም:: ጅጅጋ መምጣቴ ጥፋት ነው?» አውጥቼ አልተናገርኩትም እንጂ በውስጤ «ፓስፖርትና ቪዛ ያስፈልግ ነበር እንዴ?» ብያለሁ::

«እሺ..ዘመዴ ጋ ነው የመጣሁት ብለሀል:: ማን ጋ ነው የመጣኸው? እንዴት ሆኖ አድራሻቸውን ሳታውቅ መጣህ?» አጠያየቁ ራሱ ፖሊሳዊ ስርዓት አለው:: ሀይል አልተጠቀመም::

«ጸሀይ የምትባል ዘመድ አለችኝ:: ግን የሆቴሏ ስም ጠፍቶኝ ለማጣራት አዲስ አበባ ስደውል ነው የያዙኝ:: ልጅቷ ታማ እኛ ጋ ስለሆነች ስሙን ጠይቀን እንነግርሀለን መልሰህ ደውል ብለውኝ ነበር እባክህ ስልክ ተባበረኝና አንድ ደቂቃ ልደውል?» ደንገጥ አለ::

«ታማ እናንተ ጋር ያለችው? ማን ትባላለች?»

«ገነት»

«ወንድሚስ?»

«ዳዊት»

«የንጉሴ ልጆች?..»

«እ..እ..እ..ትክክል..!!!» ስላወቀልኝ ውስጤ በደስታ ተሞላ::

«ፍሬህይወት ሆቴል?»

«አዎ! አስታወስከኝ የጠፋኝ የሆቴሉ ስም ነበር:: ያውም ፍሬህይወት ነፍሷን ይማርና ሞታለች..» ይበልጥ አብራራሁለት::

«..እነሱንማ አውቃቸዋለሁ::» የስልኩን እጀታ ሳያነሳ ማይክራፎኑን ከፍቶ ቁጥሮችን ነካካ:: ሲጠራ ለሁላችንም ይሰማል:: ተነሳ:: ዘመዴ ጸሀይ ነበረች ያነሳችው::

«ሀሎ!!» አለች:: ድምጿን ስሰማ ደስ አለኝ::

«ሰላም ወ/ሮ ጸሀይ..መቶ አለቃ ወንደሰን ነኝ ከፖሊስ መምሪያ:: ግሩም የሚባል አዲስ አበባ ያለ ዘመድ አሎት?»

«አዎ ምነው?» የደነገጠች መሰለኝ:: ጸሀይ በተፈጥሮ ድንጉጥ እና ለሰው አዛኝ ናት:: ሰው ሲቸገር ከማየት ራሷ መቸገርን ትመርጣለች::

«እዚህ ፖሊስ መምሪያ ነው ያለው ኑ ውሰዱት» እንዳይደነግጡ ሁኔታውን አስረዳቸው:: አንትዬ */እንተነህ ነው ስሙ/* በብስክሌት ሲበር መጣ:: ለካ ብዙም ሩቅ አልነበረም::





# - 3 -

# ከጅጅጋ እስከ ጠረፍ

እውነት ቀብሮ እውነት ማጣት
መንገድ ከፍቶ መንገድ መዝጋት
ጥሩ ትቶ መጥፎ ማንሳት
ህሊናን ረስቶ ሆድን ማስፋት

ፀሀይ ስታየኝ ደነገጠች:: የዋህ አይኖቿ እንባ ቀረዘዙ:: «እንዴት መጣህ? ለምን ቀድመህ አልደወልክልኝም?»

«አጋጣሚ ነው» አልኩ:: ብዙም ጥያቄ ሳታበዛ ውሀ ይዘጋጅለት ብላ ተጣጠበኩኝ:: የተዘጋጀውን ምሳ ቀማምስን:: «ቃጨሮ[2] ይምጣ ወይስ..» አለችኝ እና ፍቃዴን ሳትጠብቅ ላከች:: መቼም ጫት የእነሱ ግብዣ ነው:: እምቢ ብል ቅር ይላታል:: በዝምታ..ዝም ማለትን መረጥኩ:: አርትሼክ ጉብቼ አድራለሁ ያልኩት ቀረና ጅጅጋ ማደሬ ቁርጥ ሆነ:: ቤቱ ሞቅ..ሞቅ ብሎ ሲቃም አንድ ጎረቤቷ የሆኑ ሴትዮ መጡ:: ምን መጡ? መጡልኝ ብል ይቀለኛል:: እሳቸው ከብዙ ስቃዮች መዳኛ መንገድ ሆነውኛል::

«እንግዳ አለብኝ ትንሽ ችግር ገጥሞት ስራ ስለፈታ ከሀገር ለመውጣት ብሎ...» ፀሀይ የነገርኳትን ነገረቻቸው:: በፊት ቅር ብሎኝ ነበር:: ምስጢሬን አወጣች ብዬ:: ለነገሩ ዋሽቼ ስራ ስለፈታሁ ነው ነበር ያልኳት:: ለሴትዮዋ መንገሯን በኋላ ጥቅሙን ሳይ ቅሬታዬን አነሳሁ:: ጠቅመውኛል:: «እ..!እ..!

[2] ሐረሮች ቃጨሮ የሚሉት በአጭር በአጭሩ የተቀነጣጠሰ ጫት ነው::

በአርትሼክ እንዳትሞክረው:: አሁን..አሁን ችግር ነው:: ቡርኦ ጫካ ውስጥ እያሰሯቸው.. እየዘረፏቸው..» አሉና ጣታቸውን አፋቸው ላይ ጭነው ትንሽ እንደማሰብ አሉና «በአርትሼክ ሳይሆን የሚያዋጣው በውቻሌ በኩል ነው» አሉኝ:: አልገባኝም:: ከዚህ በፊት ስሙን ሰምቼው አላውቅም:: ስህተት መሰለኝ:: ምክንያቱም..እኔ የማውቀው በምኒልክ የውጫሌ ስምምነት የተደረገበትን ቦታ እንጂ ሌላ ያለ አልመሰለኝም:: «ውጫሌ ወይስ ውቻሌ?»

«ውቻሌ ማለት የሶማሊያ ድንበር ናት:: ያው ሰዉ ለምዶበት ውቻሌ ይላል እንጂ ቶጎቻሌ ነው ትክክለኛ ስሙ:: ከዚህ ቅርብ ነው:: በዛ በኩል ብትሄድ ይሻላል» እንግዳዋ ሴትዮ ሁሉን ነገር ዘርዝረው አስረዱኝ:: ቀጠሉና «ገና ከአውቶቡስ እንደ ወረድክ ብሔራዊ ሆቴል የሚል ታገኛለህ:: ቀጥታ እዛ ግባና መኝታ ያዝ ከዛ ቀስ ብለህ ደላላ አፈላልግ:: ከያዙህ ሶማሌዎቹ እዛ ግባና መኝታ ያዝ ... መኪና ፈታተው ስለሚሸጡ የመኪና መቀያየሪያ ልገዛ ነው ጅጅጋ ነኝ ቀበሌ....በላቸው::» ሁሉን መረጃ ሰጡኝ::

በማግስቱ ከጠዋቱ 12:30 ላይ መናኸሪያ ወስዳ ውቻሌ..ውቻሌ.. በሚለው መለስተኛ አውቶቡስ ተሳፈርኩ:: ለመጀመሪያ ጊዜ ያየኋትን ጅጅጋ ለመጨረሻ ጊዜም ተሰናበትኳት:: «ተመልሼ አይሽ ይሆን? በእውነት ሀገሬ በድጋሚ እመለስ ይሆን? ከስንት አመት በኋላ? ልጄ አድጎ፣ እናቴ አርጅታ፣ እህትና ወንድሜ አግብተው፣ ወልደው ከስንት አመት በኋላ እመለስ ይሆን? ብቻ ፈጣሪ መልሶ ለሀገሬ ያብቃኝ...» በሀሳብ ነጎድኩ:: እዚህ አውቶቡስ ላይ አማርኛ ተናጋሪ መኖሩንም ተጠራጠርኩ:: ሁሉም ጮክ ብለው ያወራሉ:: እንዴት እንደሚደማመጡ ግራ ገባኝ:: ከጅጅጋ ከተማ ስንወጣ ፍተሻ አለ:: ልቤ በፍርሃት ሊፈነዳ ደርሶ ያለምንም ችግር አለፍኩ::

ጉዞ እንደቀጠልን በሶማሊያ ወረራ ጊዜ አደጋ ደርሶበት የቆመ ታንክ አየሁት - አፈሙዙን ወደ ጅጅጋ ከተማው እንዳነጣጠረ ቆሟል:: «ታሪካዊ ቅሪት ነኝ» የሚል ይመስላል:: ይሄኔ ከተማውን ለመምታት ሲዝሰግስ ይሆናል ያስቀሩት:: የራሴን ግምት ሰጠሁ:: ለጥ ያለው ሜዳ ላይ በየቦታው የተሰማሩትን ከብቶች፣ የዘላኖቹን ዳስ፣ እርሻ እያየሁ በዝምታ ተሰጉሜ ወደፊት..:: እነሱ ያወራሉ፣ እኔ አላወራም:: ላውራስ ብል ከማን ጋር?... በምን ቋንቋ አወራለሁ? መፈጠሬንም መኖሬንም ያሰቡ..ያወቁ አልመሰለኝም:: የአንድ ሀገር ሰዎች በቋንቋ የማንግባባ - ይገርማል:: በልዩነት ባለመግባባት ተቻችሎ መኖር ድንቅ ነገር፣ ድንቅ ውበት ነው:: የሀገሬ ልዩ ውበቷ ብሔር ብሔረሰቦቿ ናቸው:: ልቤ ደጋግሞ ያሰመረበት ሀሳብ:: በሶማሊያ ጦርነት ጊዜ አደጋ ደርሶባቸው በየቦታው የቆሙ ታንኮች ዝገት ወርሷቸው ይታያሉ:: የተቃጠሉበት ጥቁረት አልብሷቸው «..ታሪክ ይፍረደን አዎ!!!..ስንት ገንዘብ እንዳልወጣብን ስንት እንዳልሰራን ዛሬ ተጥለናል:: ለሌላ ጥቅም ለማዋል አስታውሶ የሚያነሳን በማጣታችን ከ30





ዓመት በላይ ቆመናል» የሚሉ መሰለኝ:: ወደ አስር የሚጠጉ በየጥሻው ቆጥሬያለሁ::

በየጫካው አንገታቸውን አስግገው ከየዛፉ ላይ ቅጠል እየቀነጣጠሱ የሚበሉትን ግመሎች ማየት አስደሰተኝ:: ስለቁመታቸው፣ ስለፊታቸው፣ የእግር ርዝመታቸው፣ የሸሆናቸውን ስፋት..እያሰብኩ «የበረሀ መኪናዎች» መሆናቸውን አድንቄ ተፈጥሮን፣ ሜዳ ጋራውን እያየሁ ውቻሌ (ቶጎ ውጫሌ) ደረስኩ::

እንደ ጅጅጋ የደላሎች ወከባ የሌለበት ቦታ በመሆኑ ተደሰትኩ:: ልክ እንደተባልኩት ብሔራዊ ሆቴል የሚለውን ፈልጌ አልጋ ያዝኩና ቦርሳዬን አስቀመጥኩ:: ቁርስ ለመቀማመስ ፈለኩ:: ብርሀኑ ሆቴል የሚል የተጻፈባት በቆርቆሮ የተሰራች ስመ-ሆቴል አየሁ:: ገባሁ:: ቡና ይጠጣሉ:: ፍርፍር አዘዝኩና ቡና ደረብኩ:: ፍርፍር ሳዝ ለመጨረሻ ጊዜ እንጀራ እንደምበላ ነው ያሰብኩት:: እንጀራ የእኛ ብቻ ስለሆነ ከኢትዮጵያ ውጭ ላገኝ እንደማልችል ገመቼ ነበር:: እኔ ደግሞ ሆዴ ባላገር ነው:: ያለ እንጀራ እንዴት ነው የምሆነው? ብዬ እየቆዘምኩ...

«ከሆቴሉ» ወጥቼ አካባቢውን ቃኘሁ:: ወደ ገበያው ወረድኩ:: ሕዝቡ የሁለት ሀገር ሕዝብ አይመስልም:: ይገበያያል:: አብሮ ይበላል:: አብሮ ይቅማል:: ገበያው ሶማሊያ ድንበር ላይ ቢሆንም ትንሽ አልፎ አይቼ ተመለስኩኝ:: ተመልሼ ብርሀኑ ሆቴል በረንዳ ላይ ተቀመጥኩ:: አንድ ቁመቱ ረዘም ያለ ወጣት መጣ:: ቀለል አለኝ:: ገና ከመቀመጡ «ከዚህ ሀርጌሳ የሚሄድ መኪና አገኛለሁ?» ስለው፣

«ኧረ ዝም በል» ብሎ አስደነገጠኝ:: ዞር ስል አራት ሰዎች ከኋላዬ ቡና ይጠጣሉ:: በምልክት እያሳየኝ «ሚግሬሽኖች ናቸው» አለኝ ከሹክሹክታ ባልበለጠ ድምጽ:: ትንሽ ቆይቶ ሲወጡ «ቆይ አንድ ጥሩ ደላላ አለ:: እኔ ደላላ ሳልሆን የከባድ መኪና ረዳት ነኝ:: ከእሱ ጋር ላገናኝህ» ብሎኝ ተነስቶ ሄደ:: ውስጤ ግን ተጠራጠረ:: ፖሊስ ይዞ የሚመጣ መሰለኝ:: እባብ ያየ በልጥ በረየ ይሉ የለ?

ትንሽ ቆየና አንድ አጭር ልጅ ይዞ መጣ:: የአካባቢው ተወላጅ አለመሆኑ ያስታውቃል:: እሱም እዚሁ ለዚሁ ስደተኛ ነው ማለት ነው? መታደል ነው ስል በትንሹ ቀናሁበት:: ከሀገሩ ያልወጣ ስደተኛ::

«ለታክሲው የኢትዮጵያ 150 ብር ትከፍላለህ ለእኔ የድለላ 50 ብር ትሰጠኛለህ?» አለ ደላላው::

«ችግር የለም» የእኔ መልስ ነው:: በሰዓቱ ጎዞዬን ነበር የማስበው::

«ጠብቀኝ» ብሎ ሄደ:: ወደ ፍተሻው ተጠጋሁ:: ውሀው የተጠጣ ባዶ ላስቲክ.. ጠርሙስ.. በትላልቅ ማዳበሪያ (ከረጢት) እየተሞላ ሲጫን አየሁ:: ይሄ ሁሉ ጠርሙስና ላስቲክ አንዴ ጥቅም ከሰጠ በኋላ የሚጣል በመሆኑ ሜዳውን ሞልቶታል:: የአዲስ አበባ «ቁራሌው.. ቆርቆሮ ያሌው..» ባይ ፀሀይ ሜዳውን እየቆጋው በጀርባው ጆንያ ተሸክሞ ጉሮሮው እስኪሰነጠቅ እየጮኸ ከሚዞር እዚህ በየሜዳው በነፃ የሚገኝ መሆኑን ማን በነገረው» የሚል ሀሳብ መጣብኝ:: አጭሩ ልጅ በቱፉንቱፍ ፊቱ ላይ ከወዲያ ወዲህ የሚዋከቡት ቅልብልብ አይኖቹ ታማኝ አያስመስሉትም:: መቆየቱ አጠራጠረኝ:: ትንሽ ቆይቶ አንድ የሶማሊያ መቶ አለቃ አስከትሎ መጣ:: ጸዳ ያለ እንግሊዘኛ ያወራል:: በምችላት ተንተባትቤ ተግባባን::

«ሻንጣህን..ሌላም ያለህን እቃ ካለህ አምጣ እኔ እይዘዋለሁ አንተ ከእሱ ጋር ከኋላዬ ተከተሉኝ» አለኝ:: አውጥቼ ሰጠሁት:: እንደራሱ እቃ ያዘውና እኛ ከኋላ እየተከተልነው የፍተሻ ቦታውን አለፍን:: ድልድዩን ስናቋርጥ መሀል የሚሆነው ቦታ ላይ ቆምኩ:: አብሮኝ ያለው ደላላ ግራ ገባው ሀሳቤንም የቀየርኩ መሰለው:: መቼም የድለላዋ ሀምሳ ብር እንዳትቀርበት ነው እንጂ አዝኖልኝ አይደለም::

«ምነው? ምን ሆንክ?» አለኝ:: አስብ የነበረው ግን «የትላንትናው ግሩም አከተመ:: ዛሬ ሌላ ግሩም ነኝ:: ከትላንትናው ግሩም ውስጥ የበቀልኩኝ አዲስ ስደተኛው ግሩም ሆንኩ:: አዲስ ታሪክ አዲስ ምዕራፍ..» የሚለውን ነበር:: ይህ ነበር ውስጤ ለውስጤ ያበሰረው::

ከባለታክሲው ጋር አገናኙኝ:: የድለላውን 50 ብር ተቀብለው የሶማሊያው መቶ አለቃ «ፍተሻ ቦታ ላይ ገንዘብ እየሰጠ ስለሚያሳልፍህ ነው ያስወደደው:: በተረፈ አንድ ችግር ቢገጥምህ መንገድ ላይ ቢያስወርድህ፣ ቢዘርፉህ፣ ቢመታህ ለሁሉ ነገር ደውልልኝ» ብሎ ሞባይል ስልክ ቁጥሩን ጽፎ ሰጠኝ:: ሞባይል በዛን ሰአት እኛ ጋ ክ/ሀገር ከተሞች ላይ ስራ ተብሎ ለጉድ ይወራል:: መንግስት አልባዋ ሶማሊያ ውስጥ የትኛውም ቦታ ተንቀሳቃሽ ስልክ መስራቱ ገረመኝ::

በፋሚሊ ክሪሲዳ (ማርክ ቱ) መኪና ነው የሚያጓጉዙት:: ከሹፌሩ አጠገብ 2 ከኋላው 4 እቃ መጫኛው ጋር እንደተገኘ ይጭናሉ:: 4 ሰው የሚጫንበት ጋር ገባሁ:: አንድ..አንድ ሲል ሞላ:: አሁን የቀረው ጋቢና /ሹፌሩ/ ጋር ያለችው አንድ ሴት በመሆኗ ተደራቢ ብቻ ነው:: ቆየና ተገኘ:: ሴቷ ግን አጠገቤ አይቀመጥም ብላ ረበሸች:: የመቀመጫውን እጥፍ ትከፍያለሽ ሲላት መሰለኝ እኔን ዞር ብላ አየችኝ:: ኢትዮጵያዊነቴን ጠይቀውኝ..በሹፌሩና በእሷ መካከል እንድቀመጥ አርገው በእኔ ቦታ አዲሱ ተሳፋሪ ገብቶ ጉዞ ተጀመረ:: ለምን እንደዛ እንዳደረጉ ገረመኝ:: እንቆቅልሽ ሆነብኝ:: ይህን ያረጉበት ሁኔታ የገባኝ የመን ከገባሁ በኋላ ነው:: ወንዶቹ





ሆን ብለው ስለሚተሻሹዋቸውና እምነታቸው ደግሞ ያን ስለማይፈቅድ ነው:: ሀበሻ ሆን ብሎ እንደማይተሻሽ ስለሚያውቁ መሰለኝ አጠገቧ ያስቀመጡኝ:: ግን ፈርቻለሁ::

ጉዞው ሲጀመር አጠገቤ ያለችውን ሴት ተሳፋሪን ጨምሮ ሁሉም «ቢስሚላሂ..» ብለው ፀሎት ማድረግ ጀመሩ:: አስደሰቱኝ:: እኔም «በስመ አብ..» አልኩ በሆዴ:: አስከትዬም «ጌታዬ አንተው ጠብቀኝ:: በባእድ ሀገር ያውም ህግና መንግስት በሌለበት ሀገር ነው ያለሁት ተከተለኝ» አልኩኝ:: መንገዱ አሸዋማ ቢሆንም ገጭ-ገርገጭ በሌለበት ሁኔታ በፍጥነት እየከነፍን ነው:: አቧራው ተጉለለ እያለ ሽቅብ ይወጣል:: «ኦሪያሄ አቲጋ ሀበሽ ባታሀዮ?..» አጠገቤ ያለችው ሶማሌ የጠየቀችኝ ነው::

«እ..እ..» አልኳትና ስትደግመው ለመጻፍ ወረቀት አወጣሁ::

ምን ምላሽ እንደምሰጣት ግራ ገባኝ:: አይኔን ባቁለጨልጭም አማርኛ አውቆ የሚያስተረጉምልኝ አላገኘሁም:: ግራ እንደገባኝ አወቀች:: «ካን ዩ ስፒክ እንግሊሽ?» በተሰባበረ እንግሊዘኛ ጠየቀችኝ:: «የስ» ነበር መልሴ:: «አንተ ሀበሻ ነህ?» ነበር ቀጣይ ጥያቄዋ:: አስከትላም «እኔ ሀበሻ ያውቃል ትንሽ..ትንሽ» አለች በአማርኛ::

«እንዴት ቻልሽ?»

«አዲስ አበባ ኖሪያለሁ» በእንግሊዘኛ

«ምን ያህል ጊዜ?»

«አራት ወር»

«የት አካባቢ?»

«ሳሪስ»

ስለ አዲስ አበባ ማማር..ስለሕዝቡ ጥሩነት እሷም እኔም እየሰባበርን ስናወራ አንድ ትንሽ «ጊቢሌ» የምትባል የገጠር ከተማ ቢጤ ደረስን:: የሚገርመው እዚህ ከተማ ውስጥ የተወሰኑ ኢትዮጵያዊያን ስራ ይሰራሉ:: አንድ ካፍቴሪያ ነገር ውስጥ ሻይ ለመጠጣት ሲገቡ እኔም ተከትዬ ገባሁ:: ሻይ እየጠጣን ጽዳት የሚሰራ አንድ ኢትዮጵያዊ አገኘሁ:: «ሰላም» አልኩት በአማርኛ::

«ኮ..አካሚሬ?»

«ነጉማ ፊያዳ?»

«ኤሴዲምታ?»

«የመን»

«ብያኬቱ ኤሳ?» ጥያቄው ገረመኝ:: በማውቃት ኦሮሚኛ እያናገርኩት አገርህ የት ነው ማለቱ እንዴት አያስገርመኝ? ቀይ አይደለሁ ፈረንጅ አልመስል ምን ማለቱ ነው ብዬ «ኢትዮጵያ» አልኩት:: ሌላ ምን መልስ ይኖረኛል?

«መጋላ?»

«ኤ...» ነው መልሱ

«መቃን መጋላ?» መልስ አልጠበቀም «አንተ ኦሮሞ ነህ ሀበሻ?» አለኝ በአማርኛ:: ኦሮሚኛ አለመቻሌ ገብቶታል:: ሁሉ ነገሩ አዲስ ሆነብኝ:: ያወራልኝ አማርኛ አልመስልህ አለኝ:: በአንድ ቋንቋ እያወራን መግባባት የቻልን አልመሰለኝም:: ደግነቱ ገቢ ልንቀጥል ሆነና ወጣሁ:: ውስጤ ግን ጥያቄውን ማብሰልሰሉን ቀጥሏል:: ኦሮሞ ሀበሻ አይደለም? ሀበሻ ማለት ምን ማለት ነው? ሀበሻ የሚባለውስ ክልል ከየት እስከ የት ነው? «ኢትዮጵያዊ አይደለንም:: ለመሆን እንደራደራለን» የሚል የአቶ ሌንጮ ለታን ቃለ-ምልልስ ሳሌም መጽሔት ላይ ያነበብኩት ትውስ አለኝ:: ምን አይነት መርዝ እንደረጩ አሰብኩ:: ይሄ መጥፎ መርዝ መቼ ይሆን የሚመክነው?

ሐርጌሳ ልንገባ አስር ኪሎ ሜትር እንደሚቀረን ነገረችኝ:: ቀጣዩን መንገዴን እንዴት እንደምሄድ ሳስብ «ከሀርጌሳ በኋላ ወዴት ነህ?» አለችኝ::

«ወደ ቦሳሶ ነኝ» ገና ተናግሬ ሳልጨርስ ሹፌሩ የሆነ ነገር ተናገረ:: ተርጉማ ስትነግረኝ «ወደ ቦሳሶ የሚወስድ መኪና እኔ አገናኝዋለሁ» ነበር ያለው:: ደስ አለኝ:: የሚገርመው እሷም ወደ እዛው ናት:: ያገናኘን ነገሪው ያለው:: ደስ አለኝ:: የሚገርመው እሷም ወደ እዛው ናት:: ያገናኘን ነገሪው





# - 4 -

# ሐርጌሳ

በገደላገደል፣ በዋሻ፣ ተራራ
አዛም አንድ ወድቋል፣ወዲያም አንዷ
የህፃን ለቅሶ ሰማሁ ስትሞት እናቷ
ሲደፋ አባቷ
እናት ታስቅሳለች በወላድ አንጀቷ

አባትም ተከዘ በደነ አከላቱ
ልጅ ወጥቶ ቀርቶበት፣ሲቀዘቅዝ ቤቱ
አምላክ በቃ በለን ይሄንን መከራ
ወገን ለወገኑ አርገው እንዲራራ
(ፀሀይ በየነ)

ሐርጌሳ ውር..ውር..የሚሉ ሰዎች..መኪናዎች ያጨናነቋት ወከባ የነገሳባት ከተማ መሆኗን ለመረዳት ጊዜ አልፈጀብኝም:: ምግቡ አቧራ ፈርቶ አልተደበቀም:: ልባስ አላስፈለገውም:: ሲዘረዝር አደባባይ እንደተወዘፈው ብር ራቁቱን አደባባይ ይሸጣል:: አደባባይ ይበላል:: ስጋው ሊሸጥ መሬት የተነጠፈ ላስቲክ ላይ ቢመደብም የሚታየው ክላዩ የሰፈሩት ዝንቦችን በቅጠል ነገር ሻጩ ‹‹እሽ..›› ብሎ ሲያስነሳቸው ብቻ ነው:: ወተቱ በትልቅ እቃ ተቀምጦ ቀዳ እየተደረገ ይሸጣል:: የሚገርም ለየት ያለ ከተማ ሆነብኝ:: ቀኝ መሪ ያላቸው ክሪሲዳ ፋሚሊ *(ማርክ ቱ)* መኪናዎች ሌሎችም ከተማዋን አጨናንቀዋታል::

ያለ ቀረጥ ስለሚገባ ሁሉም በየአቅሙ ባለመኪና እንደሆነ ነገረችኝ:: ሶማሊያዊያኑ መሀል አስፋልት ላይ ክብ..ክብ ሰርተው ቆመው ያወራሉ:: መኪናውም ተጋፍቶ ያልፋል:: ቦሳሶ ለሚወስደን ሹፌር ተደውሎለት ስለነበር የሆነ ቦታ ተቀጣጥረዋል:: ራጁ የሚባል አማርኛ አቀላጥፎ የሚናገር ልጅ አመጡና ወደ አንድ ምግብ ቤት ምሳ ልንበላ ገባን:: ራጁ አማርኛ ሲናገር ኮልተፍ የሚል ባፋጭ የህፃን አንደበት ያለው ልጅ ነው::

ቶሎ መግባባት የሚችል አይነት ሳይሆን አይቀርም:: ከቅጥነቱ የተነሳ እንደ ምላጭ በጎን በኩል አይታይም ማለት ይቻላል:: ፊት ለፊትም ቢሆን ብዙ የሚታይ አካል ያለው አይመስልም:: ልብሱ ላዩ ላይ እንደባንዲራ ይውለበለባል ቅጥነቱ ያስፈራል:: በዛ ላይ ርዝመቱ ያሳጣዋል:: በጥድፊያ የተሞላ ውክብ..ውክብ የሚል አይነት ነው:: እንደነገረኝ ከሆነ መኪና በማጠብ ይተዳደራል::

«አይዞህ እኔ የሐረር ልጅ ነኝ ጥሩ እንድትግባቡ እረዳሀለሁ::» ደስ አለኝ::

«እሺ! በጣም አመሰግናለሁ» አልኩ በባዕድ ሀገር የሚረዳ ወገን ሲገኝ ይጠላል? ከዛኛው ይሄ የተሻለ ይሆናል ስል ገመትኩ:: በእርግጥም ስለብሄር ያነሳልኝ ነገር የለም:: የትራንስፖርት ዋጋውንም የለውም ብሎ ተከራክሮ ከ350 ወደ 330 የኢትዮጵያ ብር አስደረገልኝ:: ሁሉም ምሳ ለመብላት የሚፈልጉትን ያዙ ጀመር:: ምን እንደማዝ ግራ ተጋብቼ ቁልጭ ቁልጭ ስል..

«ፌዴሬሽን ልዘዝልህ? የተሻለው ምግባቸው ስለሆነ ነው::»

«አንተ ደስ ያለህን እዘዝልኝ» ፌዴሬሽን ሲባል የማውቀው ሌላ ቢሆንም እዚህ በምግብ መልክ ሳገኘው ለማወቅ አጓጓኝ:: ሩዝ፣ ፓስታ፣ ስጋ በስሱ ተከትፎ የተጠበሰ፣ አሳ ጥብስ፣ በእርጎ ተለውሶ፣ ስልስ ተደርጎበት...ከዳቦ ጋር ቀረበልኝ:: ማንኪያ ስጠብቅ በእጅ መብላት የግድ መሆኑን ማንኪያ በቤቱም አለመኖሩን ነገረኝ:: ለምደውታልና ሁሉም አቀላጥፈው ይበላሉ:: እንዴት ልቻልበት? ገና ከጅምሩ እጄ ቦካ:: የሸሚዜ እጀታ ተለውሶ ምግቡን ሲመስል ትንሽ ቀረው:: «ወይ ፌዴሬሽን!!.. የሩጫ ፌዴሬሽን ይሆን? ቀፎኝ በልቼ ከታች ከላይ ሊያሯሩጠኝ ካልሆነ..» ፈራሁት:: እርጎ በተለይ እንዲህ ንጽህና በጎደለው ሁኔታ ተለዋውሶ እንዴት እሺ ብሎ ሊገባ? ነካ ነካ አድርጌ መመገቤን አቆምኩ::

«ጉድ ፈላ» ያልኩት ሂሳቡ ሲነገረኝ ነው:: ራሴን ይዤ ሁሉ ብጮህ ደስ ባለኝ:: 12500 ሂሳብ ቢጠየቅ ማንንም ያስደነግጣል:: ምንዛሪውን ላላወቀው:: መደንገጤን ያየው ራጁ «የኢትዮጵያ 50 ብር ካለህ ስጠው መልሱን ይሰጥሀል» አለኝ:: 43000 ሽልንግ ተመለሰልኝ:: ለዝርዝር በየመንገዱ የተከመረውን ገንዘብ ሳስታውስ የብራቸው መውደቅ ትዝ አለኝና «ይሄኔ አታሎኝ ሁሉ ይሆናል ይህን ብቻ የመለሰልኝ» ስል አሰብኩ:: ግምቴ ትክክል ነበር ሶስት ሺህ አታሎኝ ራጁ ተቀብሎ ለራሱ ወሰደው::

ወደ ቦሳሶ የሚወስደን ሹፌር ወዲያው ብሩን አምጡ ብሎ ተቀበለን:: ታክሲ ውስጥ አስገብቶ ከተማዋን ትንሽ ካዞረን በኋላ «ሙባረክ» የሚባል ትልቅ ሆቴል ውስጥ አልጋ ያዘልን:: በጠዋት ለመሄድ ቀጠሮ ሰጥቶን





ተለየን:: ወዲያው ወጣ አልኩና ከተማዋን እንዳልጠፋ ምልክት እያደረኩ ትንሽ ዞርኳት:: ስመለስ ጫት ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ ጠየኩ:: ውድ ከመሆኑ የተነሳ የከተማው ውድ እቃ ቢባል አያንሰውም::

ሐርጌሳ ሰውና መኪና እየተጋፋ የሚሄዱበት፣ ሁሉ ድምጹን ከፍ አድርጎ የሚያወራበት፣ ዘመናዊ ህንጻዎች ብዙም የማይታዩባት ከተማ ነች:: የቤቶቹ አሰራር ሙሉ በሙሉ በድንጋይ የተገነቡ ከመሆናቸውም በተጨማሪ ቀደምትነት የተላበሱ ናቸው፤ ለዓይንም ማራኪ አይደሉም:: ሶማሊያውያኑ የትራፊክ ህግ ያላቸው አይመስሉም:: 2 እና ከዛ በላይ ሆነው መሀል መንገድ ላይ ቆመው ያወራሉ:: መኪና አይፈሩም:: ድንገት መኪናው ይፈራቸው ይሆን?

«ሄሄ..ያ-አሪያ አሪያ ሀበሺ» አንዱ መንገደኛ ሱማሌ አናገረኝ:: ምን ምላሽ ልስጠው? ሠላም የማለት ያህል ምልክት ሰጠሁት:: ቀጠለ «ኦረሞ ኩቱ» በእጁ ጭምር ጠራኝ:: ደስ አለኝ ግን ኦሮሚኛ ባለመቻሌ ዝም ብዬ ከማፍጠጥ ውጭ መልስ የለኝም:: «ና..እንጂ!» አማርኛ መቻሉን ሳውቅ ይበልጥ ደስ አለኝ:: «አ..አማርኛ ትችላለህ?» አሁን ትንሽም ቢሆን መግባባት እንችላለን ወደእሱ ሄድኩ::

«ቲኒሽ..ቲኒሽ ይችላል:: ኦረሞ ይችላል::»

«ኢትዮጵያዊ ነህ?» ቢሆንም ባይሆንም ምንም አያገባኝም:: ዋናው ተነጋግሮ መግባባታችን ላይ ነው::

«አይደለሁም::»

«ታዲያ እንዴት ቻልክ?» የሀገሬን ቋንቋ ሁለቱን በመቻሉ ደስ ብሎኛል:: እኔ እንኳን አንዱን ነው የምችለው:: ሀገሩ ያልሆነው ሁለት ሲችል ብቀና፣ ባፍር፣ ብደሰት የቱ ነው የሚያምረው?

«ቢዙ ሀበሻ..ኦረሞ ጋደኞች አሉ::» ኢትዮጵያዊያን ወገኖቼ ተሰደው እዚህም መኖራቸውን ባውቅም ከእሱ ስሰማው እንደ አዲስ ገረመኝ:: ሀገራችን ከሶማሊያ ሳትሻል ቀርታ ነው እዚህ መኖር የመረጡት? ወይስ ሌላ ችግር አለ? ሰላም ማጣት? እዚህስ ሰላም አለ? አጠያያቂ ነው..ብዙ አሰብኩ::

«አንቱ ኦረሞ ወላ ሀበሻ?» አሁን የበለጠው አስገራሚ ልክፍት ተከተለ:: «ጊቢሌ» የምትባለው ከተማ ላይ ያጋጠመኝ የኦሮሞ ብሔር ተወላጅ ትዝ አለኝ::

«ኦሮሞም ሀበሻም አንድ ነው»

«ሚን ይላል አኒቱ? ኦረሞ ቂኝ ጊዛት ነጣ ይወጣል::» ከእኛ አልፎ ሌሎችን የመረዘ ወረርሽኝ::

«ኦሮሞ ሀበሻ ካልሆነ..ኦሮሞ ኢትዮጵያዊ ካልሆነ፣ ቅኝ ግዛት የተያዘ ከሆነ እኔ ከሁለት ብሔር የተወለድኩት ምን ልሆን ነው? የቅኝ ገዢ እና የቅኝ ተገዢ ልጅ ልሆን?..» ውስጤ እነሱ ያሰቡትን ዕውን ቢሆንስ ብሎ ማንነት ፍለጋ የጠነሰሰው ፌዘኛ ጥያቄ ነው:: ጥሩ ኢትዮጵያዊነቴን ግን ያለጥርጥር ያምናል:: ደሜ ሳይለወጥ ኢትዮጵያዊ ደም ይገኘ የዜግነት ለውጥ ናፋቂ አይደለሁም:: ልሆንም አልፈልግም::

«አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ?»

«ጠይቅ ያወቀ ይነግራል»

«ኦሮሞ ሀበሻ አለመሆኑን በምን አወክ?»

«እነሱ ነገሩ..ሁሉ ነገሩ በቃ ሰማሁ»

«ሠላም ሁን...» መንገዴን ቀጠልኩ:: ሌላ ምን ይባላል? የማወራው ሁሉ ጠፋኝ:: ምን ብዬ ልከራከረው? ተነግሮታል:: የተነገረውን አምኗል:: እነሱም ተነገራቸው አመኑ፣ አወሩ:: እግሬ ጉዞውን ቀጥሏል:: አእምሮዬ ግን በነገረኝ ወረርሽኝ ዙሪያ ያጠነጥናል::

የሌባው ብዛት አይጣል ነው:: ጸጉረ ልውጥ በመሆኔ መሰለኝ ለማጃጃል ያረጉት ሙከራ ሁሉ ገረመኝ:: ለነገሩ ሀገራቸው አይደለም በስደት ሀገራችን መጥተው እንኳን በስርቆት ስንቱን ድባቅ መተውታዋል? ሀርጌሳ ዛሬ እንደቀልድ ዞር..ዞር..ልበልባት እንጂ በዚያድባሬ ጦርነት ጊዜ ለስንቱ ወገኔ የስቃይ አረንቋ ሆና ነበር:: ስንቱ ተደበደበ፣ ተቀጠቀጠ፣ ተወገረባት፣ አካሉን አጣባት፣ ስንቱ በእስር በስቃይ ተንገላቶ ሞተ?..11 አመት በምርኮ ታስረው የተለቀቁት የሰጡት ቃል ታወሰኝ:: ግን ከትውስታ ያለፈ ነገር የለኝም::

አንዷት ቀይ ቆንጆዬ ልጅ ሁለት ህጻናት ይዛ ወደ እኔ መጣች:: ህፃናቱ ጠቆር ይላሉ:: ሰላም ብላኝ ሳንቲም እንድሰጣት ጠየቀችኝ:: ለምን እንደምትለምን፣ ልጆቹ የእሷ መሆናቸውን፣ ሀርጌሳ ስንት አመት እንደሆናት ብዙ ጥያቄዎች እያከታተልኩ ጠየኳት:: ከወሎ የመጣች የራያ ልጅ እንደሆነች ነገረችኝ:: ልጆቹ የእሷ ናቸው::

አንድ ሶማሊያዊ አግብታ ሁለት ከወለደችለት በኋላ ጥሏት እንደጠፋ አወራችኝ:: ኑሮዋን የምትገፋው ተባራሪ ስራ ሰርታ ነው:: ስታጣም ለምና እንደምትኖር እንባ እየተናነቃት ያወራችኝ አሁን ድረስ በአይነ ህሊናዬ ተስሎ ይታየኛል:: ያልፍልኛል ተብሎ ስደት ተገብቶ ልጅ ወልዶ በሰው ሀገር በልመና መተዳደር ህሊና ያቆስላል::

እኔ በተጓዝኩበት መስመር ሶማሊያ ውስጥም ሆነ የመን በዛ ያሉ ሴቶችን ታዝቤያለሁ:: ከሀገር ባል ማጣት ያስደዳቸው ይመስል ያገኙትን





ዜጋ ያገባሉ:: አብዛኛዎቹ አግብተው ሲጠቀሙ ሳይሆን ሰርተው ማብላትና ትርፋቸው ልጅ የሆነ በርካታዎች ሰነዓ ከገባሁ በኋላም አጋጥመውኛል:: አባት አልባ ልጅ የያዙትም ቁጥር ቀላል አይደለም:: የተሰደዱበትን አላማ መርሳት የአብዛኛው ስደተኛ ችግር ሆኖ ነው ያየሁት::

ሱማሊያ ውስጥ..ያውም ከራስ ያልተሻለ ከእጅ ወደ አፍ መባል የማይችል አሳዛኝ ኑሮ ከሚኖር ሰው ላይ መለመን?...ያሳፈራል:: ውስጤ ቢያነባም..ውስጤ ቢቆስልም ምንም ማድረግ አልችልም:: ሀሳቤ በቀጥታ ወደ አዲስ አበባ ነጉዶ..ሚስቴ ልጄን ይዛ ስትለምን ታየኝ:: ሰቀጠጠኝ:: አይኔ የእንባ ቋሳ አዘለ:: ከዚህ በላይ የምሰማበትም ሆነ የማይበት አቅም የለኝም:: ኪሴ ስገባ ያገኘሁትን የሶማሊያ ሽልንጎች አራግፌ ሰጠኋት:: ጨመር አድርጌ መስጠት ብፈልግም ገና መድረሻዬን ያላወኩ በመሰደድ ላይ ያለሁ ትኩስ ስደተኛ ነኝ:: ፍሬሽ ስደተኛ ልበለው? እና ሳንቲሟ አሳሳችኝ:: የእኔንም የወደፊት ዕጣ ፋንታዬን በማሰብ አልቅስ..አልቅስ አለኝ:: አሁን አሁን ሳስበው በዛ ሰሞን ብቸኛ አማራጩ ማልቀስ ነበር እንዴ? በትልቁም በትንሹም አልቅስ አልቅስ.. ይለኝ ነበር::

በቀጥታ ወደ ሙባረክ ሆቴል ሄጄ መኝታ ክፍሌ ገባሁ:: ገና 12 ሰዓት ቢሆንም መኝታዬ ላይ ወጥቼ መገላበጥ ሆነ ስራዬ:: መውጣት ፈራሁ:: ወደ ፊት የሚጠብቀኝን ባላውቅም ከዚህ የባሰ ነገር እንደማይ አስቤ ፈራሁ:: ፍርሃቴን ላስለቅቅ ይሆን? ወንበር ላይ የተቀመጠልኝን ሳሙና እና ፎጣ አንስቼ ታጠብኩ:: ጭራሽ እንቅልፌ ጠፋ:: እስከመቼ እንደዚህ እንቀጥላለን በሚል በአንድ ሌሊት ታምር ፈጥሬ የማድር ይመስል ስብሰከሰክ አደርኩ::

በማግስቱ ጠዋት የመኝታ ክፍሌ በር ተንኳኳ:: «ና ሹፌሩ መጥቷል» አለችኝ:: ሂሳብ ስለከፈልነው በዛው ቢጠፋስ ብዬ ነበር:: በእምነት መምጣቱ አስደሰተኝ:: ጫኔንና ሌሎች ተሳፋሪዎች ፍለጋ ከተማውን በተለያየ አቅጣጫ ለአንድ ሰዓት አዞረን:: 7 ሰው ሲሞላለት እሁድ 3:40 ደቂቃ ላይ ጉዞ ተጀመረ::

# - 5 -

# ጉዞ ወደ በሳሶ

ቢዛቅ ቢገለገል እሱ እንደሁ ጥቃ ነው
ቢመኙም ቢያልሙም ተስፋ ቢስ መሆን ነው
ቢሻገሩ ባህር እጅግ የከፋ ነው
የስደት ማቀሚያ ልንሙ ምንድን ነው

(ስም የሌለው ከፌስቡክ የተወሰደ)

«ቢስሚላሂ...» ተብሎ የተጀመረው መንገድ በርበራ መግቢያ ፍተሻ ላይ አደረሰን:: ብዙ መኪና አልነበረም:: ፈታሹ ወደ እኛ መኪና ሲመጣ «ምንም ቢናገርህ መልስ እንዳትሰጠው» አለችኝ:: ዝቅ ብሎ እንዳየ ብዙ ነገር ማለት ጀመረ:: ከሚናገረው ነገር ውስጥ የሰማሁት ቢኖር «ሀበሻ..ሀበሺ...» የሚለውን ተደጋጋሚ ቃል ብቻ ነው:: በሩን ከፈት አድርጋ ወረደችና አውቶማቲክ ላይ ተደርጎ እሩምታ ተኩስ እንደተለቀቀ ክላሽ ያለማቋረጥ «ጠጠረረረ!!..» አለች:: እንዴት ሊደማመጡ ይችላሉ? ግራ ገባኝ:: ለእሱ የመናገሪያ ፋታም አልሰጠችውም:: እሱም ፋታ ሳይሰጥ ያወራል:: በኋላ የሆነ ነገር ተናገረ::

ተመልሳ ገብታ ሹፌሩን እንዲነዳ ነገረችው:: የኬላውን ገመድ ፈቶ ለቀቅ አደረገው ፖሊሱ:: አግድም የነበረው ብረት ሽቅብ ቆመ:: በድንጋጤ ቆሞ የነበረ ልቤ የፍተሻውን ቦታ ሲያልፍ ተረጋጋ:: ሁሉም በሳቅ እውካኩ:: የነበረኝን ፍርሃት አውቀው መስሎኝ ተሸማቀኩ:: ወይ ቋንቋ አለማወቅ! የበይ ተመልካች ሆኜ አይኔ ተቁለጨለጨ:: ዝም ብዬ አልስቅ ፍርሃቴን አውቀው የውስጤን ተረድተው በእኔ የሚስቁ መስሎኛል:: ባላወኩት ብስቅ ማግጠጥ ይሆንብኛል:: ለነገሩ ልሳቅስ ቢባል በስደት ስንት አስቃቂ ነገር እያዩ እውነተኛ ሳቅ ከየት ይመጣል? ውስጥ በሀዘን አሮ በፈተና ተቃጥሎ.. ልሳቅስ ቢሉ ይሳቃል? አለመሳቁ ሁሉ ሳይገርማቸው አልቀረም:: እነሱስ ሰላም ባይኖራትም፣ ቢከፋም ቢለማም ሀገራቸው ላይ ሆነው ነው:: እኔ





የሰው ሀገር ሰው፣ የስደት ማረፊያዬን መጠለያ..መውደቂያዬን ያላወኩ ምን ደልቶኝ ልሳቅ? ብስቅም ማግጠጥ ነው የሚሆነው::

«ምንድን ነው እንዲህ ያሳቃችሁ?» አልኳት ሣቋን ስትገታ::

«መስማትና መናገር የማይችል ደንቆሮ ነው:: አባቴ ጅጅጋ የወለደው ወንድሜ ስለሆነ እሱን ላመጣ ነው የመጣሁት...አልኩት» አለችኝ:: በአባባሏ መሳቅ ያለብኝን ያህል ስቄ አም!..ስቄ ልበለው እንጂ እሷን ደስ እንዲላት ብቻ አገጠጥኩና «ቴንኪው» አልኳት:: በሆዴ የተባረክሽ የሚለውን ጨምሬ::

«እንደዚህ እያልኩ አደርስሀለሁ::»

«በጣም ነው የማመሰግነው»

«ኢትዮጵያ ስራ የለም? አረብ ሀገር ምን ትሰራለህ? በተለይ የመን ችግር ነው:: ለወንድ ስራ የለም::»

«ስራ ፈልጌ አይደለም የምሄደው»

«ትዳር ፈልገህ ነው ታድያ?» ፈጣን መልሷ ገረመኝ::

«አይደለም»

«ዘመድ ጥየቃ በባህር?» በአሽሙር ቃና::

«አይደለም»

«ወደ ሳዑዲ ልትሻገር?»

«አይደለም»

በግልምጫ ጫማ ጥፊ ቀረደደችኝ:: አገለማመጧ ድባቅ ይመታል:: ግልምጫ ያምርባታል የሚባል ከሆነ እሷን ያለጥርጥር ያምርባታል:: እኔ በውስጤ ልንገራት አልንገራት እየተሟገትኩ ነው::

«ታድያ ለምንድን ነው የምትሄደው? ሀበሻዊ ጥቁር ቱሪስት ነህ በባህር?» የአሽሙር በትሯ እንደተናደደች ይገልጻል:: ላለሳልሳት ይገባል::

«...ሀገሬ መኖር ስላልቻልኩ ነው» አልኳት::

«እንዴት? ወንጀል ሰርተህ ነው?»

«የግል ፕሬስ ጋዜጠኛ ነኝ» አንዳንድ ነገር እየጠየኩ የምጽፍበትን ወረቀት አየች::

«አኒቴ መሰለሊ ነው ያለህ አንተ ሰሊላል? በኋላ ጦር ይልካል::» የወየበ ፈገግታ ቸርኳት:: አሁን በተሰባበረ አማርኛ የነገረችኝ እንግሊዘኛውን ባልረዳት እንዲገባኝ ፈልጋ ሙሰለኝ::

«ኦ ኦ ኦ . . .ነገር እንዳይመጣ» እያለ ውስጤ «እውነት ጋዜጠኛ ነኝ» አልኳት::

«አልመሰለም»

«እንዴት?»

«በቃ! አሊመስለም»

«መታወቂያዬን ላሳይሽ?»

«አዎ!» አሳየኋት:: እውነትም ስላይ ብላ እንዳታሲዘኝ ፈርቻት ጭምር ነው ያሳየኋት:: በሀዘኔታ ራሷን ነቀነቀች «ኢረዳሀሎ» ስትል ድጋሚ ቃል ገባችልኝ:: ለሌላ ሰው እንዳልናገር አስጠነቀቀችኝ:: ጉዞው እንደቀጠለ ነው:: የደሴን ጠመዝማዛ መንገድ የሚያስንቅ ጥምዝምዝ ያለ ብቻ ሳይሆን ከላይ ሆኖ ቁልቁል የሚያፈጥ መንገድ ከተራራው ላይ ያለሀሳብ ተኝቶ አየን:: በቁንጥ የተሰራ የልጃገረድ ሹርባ ይመስላል:: የመኪናው ፍጥነት ተገታና ጠመዝማዛውን መንገድ ተያያዘው:: ተራራውን ወጥቶ እንደጨረሰ ስመ ከተማ *(የገጠር ከተማ)* የሆነች መንገዷ ዳርና ዳር ትንሽ ቤቶች ያሉባት ቦታ አገኘን::

ሼክ ትባላለች:: የጫት ኤርፖርት እንዳላት ነገረችኝ:: አየር ማረፊያውን ግን አላየንም:: ጥግ ላይ መኪናው ቆመና ምሳ ብሉ ተባለ:: ገና ስወርድ «የሀገር ልጅ» የሚል ድምጽ ሠምቼ ዞር አልኩ:: ቀይ ሰልካካ ደስ የሚል ልጅ አየሁ:: የሚያምር ተክለ ሰውነት ያለው ነው:: ፈግጓል:: አጠር ያለች ሸርጥ ቢጤ አድርጓል:: ስራው ምን እንደሆነ ለመለየት አያስቸግርም:: መጥረጊያና ቆሻሻ ማፈሻ ይዟል:: ተጠጋሁት::

«ሰላም ወንድሜ? እዚህ ምን ትሰራለህ?»

«መሀመድ አልዬ እባላለሁ:: ፅዳት እየሰራሁ ኑሮዬን እገፋለሁ::» የወሎ ልጅ መሆኑን በአነጋገር ዘየው አወኩ:: በኑሮው ደስተኛ አለመሆኑን ንግግሩ ፍንትው አርጎ ያሳያል:: እንዴትስ ደስተኛ ሊሆን ይችላል? ነኝ ቢልም አይታመንም:: ጥውልግ ያለ ተስፋ ይታይበታል::

«ምሳ እንብላ ምን የተሻለ ነገር አላቿው? ጥሩ የምትለውን እዘዝልኝ» አልኩት:: እንደ ሐርጌሳው ፌዴሬሽን ተብሎ የተጨማለቀ ነገር እንደመጣልኝ እንዳይሆን ስግቻለሁ::

«ደግ» አለና መጥረጊያውን አስደግፎ ወደ ውስጥ ገባ:: መረቅ፣ ሩዝ እና ሰላጣ ከአሳ ጥብስ.. ከለስላሳ መጠጥ ጋር ይዞ መጣ:: እየበላን ያወራኝ ነገር ተስፋ ያስቆርጣል:: ለ4 ዓመት በዚህች ከተማ ቆይቷል:: ከሆቴሉ ፊት ለፊት ያለች ዳስ አሳይቶኝ መኖሪያው እንደሆነች ነገረኝ:: የሚለብሰው





እንኳን የለውም:: ምን አይነት አስጠሊታ ህይወት እንደሚኖር ሳስብ ግራ ገባኝ:: የሚከፈለው ወደ ኢትዮጵያ ብር ሲመነዘር ከመቶ ጥንጥዬ ቢዘል ነው::

አገሩን ለቆ የተሰደደ መናጢ ደሀ ስደተኛ ከምግብ፣ ከልብስና መጠለያ ሌላ ምን ይፈልጋል? በቃ!! የተሰደደው በሀገሩ መኖር አልችል ብሎ አይደል? ችግሩ የሚበላው ማጣቱ..መጠለያ..አልባሳት..ማጣቱ..ብቻ ነው እንዴ? ሁሉ ነገር ከዚህ የበለጠ አስከፊ ህይወት ሆኖበት ይሆን? ወይስ ግንዛቤ ማጣት? እንባዬ መጣ:: ስሜቴን ሁሉ ተቀብሎ በማልቀስ የሚያስተናግደው አይኔ እንባ ቶሎ..ቶሎ.. ማፍለቁን ተያይዞታል:: ይህን ያህል ተሰደን ከራስ ባልተሻለ ሀገር በፍርፋሪ ተቀጥረን መኖር..ረሀባችን የቱን ያህል ከፍቷል? ውስጥ የሚያቆስል ሁኔታ ነው የገጠመኝ:: ከሐርጌሳዋ የሁለት ልጆች እናት ገጠመኝ ጋር ተደምሮ ውስጤ በሀዘን ተቃጠለ:: ጉዞ ብንቀጥልም ህሊናዬ ቡቱቶ ለብሶ ጠማማ ዳስ ውስጥ እያደረ ጉልበቱን ለሆዱ ባደረገ ወንድሜ ዙሪያ እያጠነጠነ ነው:: መጀመሪያ ሲመጣ ሰዎቹ ላደረጉለት ውለታ ይሉኝታ ይዞትም እንደተቀመጠ ነግሮኛል::

«ቡሩኦ» የምትባል ከተማ ደረስን:: ጫት ካልገዛችሁ ጉዞ አይቻልም የተባለ ይመስል ሁሉም ገዙ-ሴቷም ጭምር:: ከህግጋቱ ወጥቼ እንዳልቀጣ እኔም ለመመሳሰል ባስብም ውስጤ «ሌላ ቀን የማታደርገውን ምነው አበዛህ?» የሚል ወቀሳ ብጤ ለነዘረብኝ:: ከዚህ በኋላ የሶማሌላንድ ሳንቲም ብዙ ጥቅም ስለማይሰጥ በፑንትላንድ ሽልንግ ቀየርነው:: ጉዞ..ጉዞ..እየወለደ አሰልቺነቱ በሙቀት የታጀበ ሆኖ በላብ እየታጠብን ቀጠልን:: ለሽንት ውረዱ ተባለና ወርደን በየቦታው ተበታተንን:: እንደገና ጉዞው ቀጠለ:: ገረዊ የምትባል ከተማ ደረስን:: *(ድንገት ከከተማነት ከዳፉት ብዬ ነው እንጂ ቤቶቹን ብንቆጥራቸው ከ200 አይበልጡም::)* ገረዊ ቡርኦ ላይ ጦርነት ተነስቶ ሸሽተው ለረጅም ዓመት እንደመጠለያ የተቀመጡበት በUNHCR የተቆረቆረች ከተማ እንደሆነች ነገረችኝ::

ቀጥሎ ያገኘናት «ላስአኖት» የምትባል ከተማ ናት:: ይህች ከተማ የሶማሌላንድ ጠረፍ /ቦርደር/ ነች:: ገንዘቡም የመኪና ታርጋውም ከዚህች ከተማ አልፎ አይሰራም:: ሹፌሩ መፍቻ እና የመኪና ታርጋ ይዞ ወረደና ቀየረ:: እስከዛ የመጣንበት የሱማሌላንድ ታርጋ ሲሆን የቀየረው የፑንትላንድ ነው::

ከልካዮ ከሚባለው ከተማ በኋላ ሞቃዲሾና ቦሳሶ የፑንትላንድ ገንዘብ እንደማይሰራ የመኪናውም ታርጋ ድጋሚ እንደሚቀየር ስታወራኝ ገረመኝ:: ከልካዮ የሚባለው ቦታም ሆነ ሞቃዲሾ እንደማንደርስ ነግራ «ገረዊ» ላይ መገንጠያ መንገዱን አሳዩቿኝ:: «ቦሳሶ» ፑንትላንድ ውስጥ መሆንዋን

ስታስረዳኝ የጂኦግራፊ ተማሪ የሆንኩ ቢመስለኝም ትንተናዋን ወደድኩት:: ታርጌት ያረኳት ቦሳሶ ከገረዊ 500 ኪ.ሜትር ትርቃለች:: በመካከላቸውም «ቃርዳ» የምትባል ከተማ አለች:: ገረዊ ለፑንትላንድ ርዕሰ መዲና ነች:: እሁድ ጠዋት ከሐርጌሳ የተነሳን ስንሄድ ውለን አድረን ሰኞ ከጠዋቱ 1:30 ላይ ቦሳሶ ገባን::





# - 6 -

# ቆይታ በቦሳሶ

ደረቱን አልደቃ እንደሰው  
ፊቱንም አልነጥ ላቀስለው  
ወንድ አያለቅስም ብለው  
አርሬ እንድሞት አድርገው  
አሁን እንዴት ላንባ  
ሲከሩኝ ሆዴ ሲባባ

ቦሳሶ እንደጠበኳት አይነት ከተማ ሆና አላገኘኋትም:: የሶማሊያ እርስ በእርስ ጦርነት አሻራውን ጥሎ የማይረሳ ትዝታውን ተክሎ ካለፈባቸው ከተማዎቻቸው አንዷ ናት:: የፈራረሱ የቤት ቅሪቶች በየቦታው ይታያሉ:: ጣራው..ግማሽ ግድግዳው የተቦደሰ ቤት በሩቅም በቅርብም አይን ይስባል::

አዲስ አበባ በጋሽ አበራ ሞላ የተጀመረው ፕሮጀክት በህዝቡ ውስጥ ሰርጾ ከገባ በኋላ ንጽህናዋ እጅጉን የተሻሻለ ሆኗል:: ከሶማሊያዊያኖቹ ከተማዎች አንጻር ስትታይ ግን ድሮም ንጹህ ነች ያሰኛል:: በየቦታው የወዳደቀው ላስቲክ፣ የሚጠጣ ነገር የሚታሸግባቸው ቆርቆሮዎችና ፌስታል ላስቲኮች ለከተማዋ ንጽህና ጉድለት የመጀመሪያ አስተዋጽኦ አድራጊዎች ሆነው ታዩኝ:: ቦሳሶ እንደገባን አንድ ሆቴል ጋ የወረደችው የመንገድ ጓደኛዬ «አሳዝነሽኛል ከባሌ ጋር መጥቼ እጠይቅሀለሁ» ካለችኝ በኋላ ለሹፌሩ ደግሞ «እባክህ..ሀበሻዎች ያሉበት ሰፈር አውርደው» አለችው:: እውነትም ከከተማዋ ዳር ወደ ባህሩ ተጠግቶ ያለው ቦታ የሀበሻዎች ማረፊያ ሆኗል::

ሹፌሩ እዛ ባሉት ስደተኞች ዘንድ «ጋሽ» የሚለውን መጠሪያ የተጎናፀፈው «አቶ ሰለሞን» የሚባል ሰው ንግድ ቤት በር ላይ አወረደኝ::

ስሙን ያወኩት በኋላ ነው:: ጠልጠል ያረኳትን ቦርሳ እንደያዝኩ ዞር..ዞር ብዬ ሳይ አንዱ

«እንኳን ደህና መጣህ» አለኝ::

«እንኳን ደህና ቆየኸኝ::»

«ገና መምጣትህ ነው?» ከመኪና ስወርድ እያየ

«አዎ!»

«ከዚህ በፊት መጥተህ ታውቃለህ?» አጠያየቁ አናደደኝ:: ፎርም የሚያስሞላኝ መሰለኝ:: «ደጋግመው የሚመጡ አሉ ማለት ነው?» በውስጤ አሰብኩ::

«አይ!»

«እኔም መጀመሪያዬ ነው:: ቦርሳህን ጋሽ ሰለሞን ጋ አስቀምጠው::»

«ጋሽ ሰለሞን ማነው?»

«እንዴት አታውቀውም?»

«የሶማሊያ ፕሬዘዳንት ነው ጠቅላይ ሚኒስትር ሁሉ ሰው የሚያውቀው? ቢሆን እንኳን ላላውቀው እችላለሁ:: አዲስ ነኝ እያልኩህ የምትጠይቀኝ ጥያቄዎች ነዋሪ ነኝ ያልኩህ ያስመስላል:: ይልቅ ማረፍ እፈልጋለሁ:: ቦታ የለም እንዴ?» አልኩት:: እሱ የእኔን ንግግር ከምንም አልቆጠረው..

«የእዚህ ሆቴል ባለቤት እኮ ነው ጋሽ ሰለሞን..» ሳቀ አመለጠኝ:: «ካ..ካ..ካ..ካ» አስነካሁት:: አየኋት:: በላስቲክና በሸንበቆ ሜዳ ላይ የተሰራች ዳስ ቢጤ ነች:: ሣቄን ከምንም ሣይቆጥረው ቀጠለ::

«ቅዳሜ ማታ የሚነሳ ዶኒክ[3] አለ:: ሰለሞን ነው የሚጭነው በዛው ትነግረዋለህ?» መልሴን ሳይጠብቅ ቦርሳዬን ተቀብሎኝ ገባ:: ተከተልኩት::

አጭር፣ በቅጥነቱ ላይ የረጅም ጊዜ ጉስቁልና የጎዳው..ደስተኛ ለመምሰል የሚጥር በከሳ ፊቱ ላይ ማድያት የደረበ..ቆዳው ተሸብሽቦ የትግሬ ጥርጥር የሚባለውን ቀሚስ የመሰለ፣ ፀጉሩ ገባ..ገባ..ያለ የሚለውን አልፎ መሀል የደረሰ ሰው «ሰለሞን» ብሎ ጨበጠኝ:: ‹‹ነፍስ ይማር›› ልል ነበር ስሜን በመንገር ፋንታ:: ከሙት መንፈስ ጋር የማወራ ነው የመሰለኝ:: ከቢጫነት ዘሎ ጥቁረትን ባስተናገደ ጥርሱ ፈገግታ መገበኝ:: እኔም ስሜን

[3] ዶኒክ የሚሉት ጀልባውን ነው





ነገርኩት:: ቤቷ ውስጥ ያሉትን በርካታ ኢትዮጵያዊያን ግራ በተጋባ ስሜት ማጤን ጀመርኩ:: በትግርኛ አናገረኝ:: በአማርኛ መለስኩለት::

«ቶሎ መሄድ ከፈለክ ቅዳሜ ማታ የሚነሱ ጀልባዎች አሉ» ነበር ያለኝ:: «..ቶሎ መሄድ ከፈለክ..» ማለቱ እንደገረመኝ ገብቶት ይሁን ዝም ብሎ «ድንገት ገንዘብ ተዘርፈህ ከሆነ እስኪላክልህ መቆየት ከፈለክ ብዬ ነው» የሚል ማስተካከያ አከለበት::

ለስለስ ያለ የርሃብ ስሜት ሲቆነጥጠኝ ይሰማኛል:: መጀመሪያ ያናገረኝ ልጅ ጅብሪል ይባላል:: ወደ እሱ ጠጋ ብዬ ቁርስ ነገር እንደምፈልግ ነገርኩት:: «አንድ ሙሉ» አለና አዘዘ:: በየቦታው የምግቦቹ ስሞች አስገርሞኛል:: ሁለት ጥንግርግር ያለ እንጀራ የሚል ስም የተሰጠው ስስ ቂጣ ቢባል የሚያስኬድ ነገር በትሪ ቀረበ:: የሆነ..«ወጥ» የሚለውን ስሙን ብቻ የያዘ ከውሀ የቀጠነ ፈሳሽ ከላይ ደፋችበት ልበል ጨመረችበት? እንኳን ሊበሉት ሲያዩት ያስጠላል:: የመብላት ፍላጎቴን ዘጋው:: ወጥ ተብዬው ሮጠ...

እንጀራ ሶማሊያ ውስጥ አገኛለሁ፣ አያለሁ ብዬ ፈጽሞ አላሰብኩም:: ለአይን የማይስብ ቢሆንም አገኘሁ:: በስደት አለም መጠየፉ ዋጋ የለውም ብዬ «ልመደው ልመደው ሆዴ...» የሚለውን ዜማ በውስጤ አቀንቅኜ መጉረስ ጀመርኩ:: አልዋጥልህ ብሎኝ አፌ ውስጥ ይንቀዋለላል:: እንደምንም ታግዬ ትንሽ ቀማምሼ ተውኩት:: ጅብሪል ግን የተላመደው ይመስላል:: እዛች ቤት ሻይ..ቡና..ቂጣ ይሸጣል:: ብዙ ቁጭ ስል እንቅልፍ ተፈታተነኝ:: እንጎላጀጀኝ:: ስንጓዝ ነው ያደርነው:: ወጣ እንድንል ጠይቄው ወጣን - ጅብሪል ቦሳሶ 3 ወር ከ15 ቀን ቆይቷል::

«ከዚህ የተሻለ ቁርስ ያለበት ቦታ የለም?»

«አለ ከፈለክ ላሳይህ» ትንሽ ሄደን አንድ ቦታ ይዞኝ ገባ:: ጥሩ ፉል አበላኝ:: ውድም ጋሽ ሰለሞን ቤት ከቀማመስኩት ጋራ ፉሉን ጨርሰን መብላት አልቻልንም:: ተነስተን ሂሳብ ልንከፍል ስንል አንድ ጥቁርቁር ያለ የተጎሰቋቆለ ልጅ መጥቶ ትተነው የተነሳነውን ቁጭ ብሎ መብላት ጀመረ:: አበላሉ እህል ካየ ሰንበት ያለ ይመስላል:: የሆነ መጥፎ ስሜት ተሰማኝ ተመልሼ ተቀመጥኩ:: ሰውነቱ ሁሉ ይንቀጠቀጣል:: ጅብሪል ግራ የገባው መሰለኝ:: ደጋግሞ እንሂድ እያለ ይወተውተኛል:: የእኛን ንግግር ከምንም ሳይቆጥረው በልቶ ሲጨርስ ትንፋሹን በረጅሙ ለቀቀው:: አሁን ቀና ብሎ አየን::

«ሰላም ነህ?» ጠየኩት

«እህህህ!!!» ሲል በረጅሙ ተንፍሶ በአዎንታ ራሱን ነቀነቀ::

«ገና መግባቱ መሰለኝ» ጅብሪል ብዙ አይቶ የተላመደ መሆኑ ያስታውቃል:: «ጫካ ካሰሯቸው ጋር ነህ?» ጥያቄውን ጨመረለት:: አሁን ጆሮዬ ነቃ:: ምላሹንም መስማት ናፈቀኝ:: ልጁ ግን «አዎ!» የሚለውን ለመግለጽ ራሱን እነቃነቀ:: መናገር የፈለገ አልመሰለኝም:: የምናገረው ሁሉ ጠፋኝ::

«ማናቸው አሳሪዎቹ? ለምንድን ነው የሚያስሩት? ፖሊሶች ናቸው?» ለሁለቱም ያቀረብኩት ጥያቄ ነው:: ሁለቱም መልስ ስላልሰጡኝ ጥያቄውን ደገምኩት

«ቡርኦ የሚባል ቦታ ላይ ጫካ ውስጥ ከጅጅጋ ያመጡትን ተቀብሎ የሚያስተናግድ ሼህ አብዶ አሊ የሚባል ሰው አለ:: ወታደሮች አሉት:: እነሱ ጫካ ውስጥ አስረው ይዘርፋሉ፣ ያንገላታሉ..ብቻ ተወው» አለና ጅብሪል ተከዘ:: የሆነ የከፋው ነገር እንዳለ አወኩ:: ይበልጥ ለማወቅ ጓጓሁ::

«ማታ ከገቡት ጋር ነህ ወይስ አሁን መምጣትህ ነው?» ጅብሪል ጠየቀ:: ልጁ ግን ጠቋሚ ጣቱን ወደታች ቀስሮ አሁን መግባቱን በምልክት ለማሳየት ሞከረ:: የማይናገረው አሞት ይሆን? ወይስ አማርኛ መስማት ብቻ ነው የሚችለው? ግራ ገባኝ::

«ሻይ መጠጣት ትፈልጋለህ?» ጅብሪል 1000 ሽልንግ ከኪሱ እያወጣ አስተናጋጁን ጠርቶ አዘዘለት:: አሁንም አዎንታውን ራሱን በመነቅነቅ ገልፆ እንባ ያቀረረ አይኑን እያቁለጨለጨ ሆዱን ያሻሽ ጀመረ:: «አልጠገበ ይሆን?» የኔ ሃሳብ ነው:: ሀሳቤ ስህተት ነበር:: ቁርጠት እንደያዘው በምልክት ነገረኝ:: እስካሁን ችግሩን ሳናውቅ ነው የጨቀጨቅነው:: የምናደርገው ጠፋን:: ማንን ምን እናማክር? እኔ ቁርጠት ለያዘው ሰው ምን መደረግ እንዳለበት የማውቀው ነገር የለም:: ይንደፋደፍ ጀመር:: አይኑ አቅርሮት የነበረውን እንባ ዘረገፈው::

ሻዩን ያመጣው አስተናጋጅ አናገረኝ:: በምን ቋንቋ ሰምቼ ምላሽ ልስጠው? በምን ቋንቋ ድረስልን ልበለው? በምልክት ለማስረዳት ስሞክር ጣቴን ሳወሳስብ ዳንቴን የሚሰራ ሰው መሠልኩ:: ጅብሪል ደግፎ ከያዘበት ቀና ብሎ በሶማሊኛ የሆነ ቃል ተናገረ:: «ከኪሴ ሁለት ሺህ ስጠው» አለኝና ኪሱን ሰጠኝ እኔ ስላልዘረዘርኩ አውጥቼ ሰጠሁት:: ሱማሌው ተንደርድሮ ሱቅ ገባና ኪኒን ይዞ ወጣ:: ኪኒን ሁሉ በየሱቁ መኖሩ ገረመኝ:: ኪኒኑን ሲያውጠው ቆይቶ ህመሙ ለቀቀው:: ውስጤ የነበረውን ስሜት ያኔ አይደለም አሁንም አላውቀውም:: የተምታታ ስሜት ነው ያለኝ:: እርግጠኛ የምሆነው ግን የደስታ ስሜት የተሰማኝ ህመሙ መለስ ያለለት ሠዓት ነው::

«ወይኔ አርፌ እርሻዬን...» ብሎ በእንጥልጥል ተወው:: ገበሬ የነበረ መሆኑ ያስታውቃል:: ከአርሲ እንደመጣ እህል ከበላ 3 ቀኑ መሆኑን ነገረን::





«ለምን አልበላኽም? የት ነው ያሰሯችሁ? ስንት ናችሁ?...» ጥያቄ ደረደርኩ:: አቧራው ከፀጉሩ ጀምሮ ወርሶት የነተበ ጃንያ አስመስሎታል:: ጉንጩ ጠፍቷል:: ሙግግ ብሎ የፊቱ አጥንት የልጃገረድ ጡት መስሎ ወደፊት ተወድሯል:: አይኑ ጉድጉድ ቢልም ጎላ ብሎ ቁልጭ.. ቁልጭልጭ ይላል:: አሳዘነኝ የሚለው ቃል ከሚገልጸው በላይ ውስጤ ገባ:: እንኳን እኔን ወገኑን ሶማሊያዊያኑም አዘኑለት:: 3 ሺህ የሚከፈልበትን ገላ መታጠቢያ በነፃ ፈቀዱለት:: ጅብሪል ከልቡ ቀና እና ጥሩ ልጅ ነው:: ቶሎ ምላጭ ገዝቶ ፀጉሩን ላጨው::

«የሚለብሰው ልብስ ካለህ ስጠው እኔ ስሰጥ..ስስጥ ጨርሻለሁ» ጅብሪል አነጋገሩ የልመና አይደለም:: ካለህ ግዴታ ነው ለወገን የሚል ቅላፄ ያለው መሰለኝ:: ተነስቼ ትንሿን ቦርሳዬን ያስቀመጥኩበት ጋሽ ሰለሞን ዘንድ ሄድኩ:: ለካ ገና መግባታቸው ነው:: በየመንገዱ፣ በየጥጉ ተዝለፍልፈው፣ ተኝተው ያየሁት በጣም በርካታ ናቸው:: ሁሉም ከሰል መስለዋል:: ቶሎ አልኩና ከያዝኩት መቀየሪያ ልብስ ውስጥ አንድ ሸሚዝና ሱሪ ይገፍለት ሄድኩ:: ታጥቦ ወጣ:: «ጣሂር» ነው ስሙ:: ጋሽ ሰለሞን ቤት ልበለው ሆቴል ቁጭ ብለን ያወራኝ ጀመር::

«ከእኛ አካባቢ አንድ አብሮ አደጋችን በዚህ አድርጎ ሳዑዲ ገባ:: በአመቱ የላከው ብር የቤተሰቦቹን ቤት ሳሩን በቆርቆሮ ለወጠ:: ከብት ገዛ:: ደብዳቤ ሲጽፍ ሥራው ከብት ጥበቃ እንደሆነ፣ ጥሩም ክፍያ እንደ ሚከፈለው ሲጽፍ፤ እኔም ስራው እንደማያቅተኝ አሰብኩና የነበሩኝ የእርቢ ከብቶች በሙሉ ሸጬ መንገዱን ጠያይቄ መጣሁ::»

«ስራ የለህም ነበር?»

«እርሳለሁ፣ ከብት አረባለሁ::»

«ጫካ ውስጥ ለምን አሰሯችሁ?» ለማወቅ በጣም ጓጓሁ:: ወረቀት አውጥቼ የሚለኝን ሙሉ ለሙሉ ብጽፈው ፈለኩ:: ግን ጋዜጠኛነቴን ያውቃሉ አለያም ሌላ ስራ የምሰራ መስሏቸው ያሲዙኛል ብዬ ፈራሁ::

«ጅጅጋ እንደደረስኩ ደላሎቹ ሲያዋክቡኝ..አመንኳቸው እጅ ሰጠሁ:: አፋቸው አቀለጠኝ:: ጀልባውን ጭምር እናሳፍርሀለን ሲሉ እውነት መሰለኝ:: በ400 ብር ሁሉን ጨረስኩ ብዬ ተስማማሁ:: አንድ ፍየሎች ያሉበት ጊቢ ወስደው አስገቡኝ:: ቀድመው የተቀመጡ 3 ልጆች ነበሩ እስር የጀመረው ከዛ ነው:: መውጣት መግባት አይቻልም ተባለ 1 ጠባቂ ልጅ ተመደበልን ለሽንት እንኳን ካልተፈቀደ በቀር ጊቢው ውስጥ መንቀሳቀስ ክልክል ሆነ:: ለ3 ቀን በዚህ ሁኔታ ስቆይ ያየሁት ጭቆና ሀገሬ ላይ ያለሁ አልመስል አለኝ:: ሌሎችም ተጨምረው 9 ሆንን:: ትልቅ የተዘጋጀ ድስት አለ:: ሩዝ በውሃ ቀቅለን እንበላበታለን:: ቁርስና እራት መደበኛ ዳቦና ሻይ

አለን:: በሶስተኛው ቀን ሌሎች 11 ልጆች ተጨመሩ:: ወዲያው ፍየል የተጫነበት መኪና መጣና እኛም እንደ ፍየል ተጫንን::

መጀመሪያ ወደ ጊቢ ሲያስገቡን በሳሶ ድረስ መሄጃ 200 ብር የጀልባ 200 ብር ብለው 400 ብር ይቀበላሉ:: ትኬት ነገርም አምጥተው ይሰጣሉ:: አርትሼክ ፍተሻ ላይ ስንደርስ «ለማሳለፊያ 50 ብር ለእያንዳንዳችሁ እንክፍላለንና አምጡ» አሉ:: ስናንገራግር «ያለበለዚያ የከፈላችሁት 400 ብር ይቀልጣል ያስወርዷችኋል እኛ ሀላፊነት የለብንም» ብለው አስፈራርተው ተቀበሉን:: እነሱ ግን ፍተሻ ጋ ሊደርሱ ቀርቶ የት እንዳለ ሣናየው ጫካ ጫካውን አቆራርጠው ፁርአ ያለ ሃሳብ ደረስን::

የቡርአን ከተማ በርቀት እያየን ወደ አንድ ጫካ ተንዝን::

አብዶ አሊ ከሚባል አንድ ሰው ቤት አረፍን:: ጊቢ አለው:: ከእኛ ቀድመው የመጡ 240 ሰዎችም ነበሩ በማግስቱ አብዶ አሊ ተብየው መሳሪያ በታጠቁ በርካታ ጎረምሶች ታጅቦ መጣና ከፊታችን ቆሞ «ዛሬ እረፍት አድርጋችሁ...» ብሎ ለንግግር ከንፈሩን ሲያንቃንቅ የሁላችንም ጆሮ ቆመ::

ንግግሩን ቀጠለ:: በአስተርጓሚ «ዛሬ እረፍት አድርጋችሁ ነገ ወደ ማታ ጉዞ ትጀምራላችሁ:: ከዛ በፊት ጀልባ የምትሳፈሩበትንና ከዚህ ቦሳሶ የምትደርሱበት እያንዳንዳችሁ 400..400 ብር መክፈል አለባችሁ::»

ሁላችንንም የሆነ ስሜት እንደተሰማን ለማወቅ ጊዜ አልፈጀብኝም በ400 ብር ያልቃል የተባለው ጉዞ ገና ከጅምሩ 800 ደርሷል:: ጉድ አልኩኝ በሆዴ:: ጅጅጋ እንደከፈልን እንዳንናገር የሚከተለውን ነገር ፈርተን ሁላችንም ዝም አልን» አለና ጣሂር በሀሳቡ የሆነ ነገር የታወሰው ይመስል ፊቱን ቅጭም አርጎ ብስጭት አለ:: አፈጠጠብኝ::

«ምን ሆነህ ነው እንዲህ የምትበሳጨው?» ስለው «..ምን አይነት ጅላጅል ጥያቄ ነው የምትጠይቀኝ?..» በሚል አስተያየት ገላመጠኝ::

«አይገባህም? ይሄ አውሬነት ነው:: የእሱ አጋፋሪዎቹም */ገሻ ጻገሬዎቹ/* ሆነ ሚስቱ ኢትዮጵያውያን ናቸው:: ዋናው ተከታዩ የአርሲ ልጅ መሆኑን ሳውቅ ይበልጥ ተናደድኩ:: አስብ በወገኑ ላይ የሚፈጽመው ግፍ አይጣል ነው:: ከሁሉ የከፋው ከወሎ የመጡ ባልና ሚስት ነበሩ:: ሴቷን ሊደፍራት ሲል ባል አይሆንም ሚስቴ ናት በማለቱ ደብድበውት እጁ ተሰብሮ...» ተከዘ:: በቁጭት ጥፍሩን እየበላ ቀጠለ...የሚናገረው ለእኔ እንጂ ያስገረመው ለጅብሪል የታከተው አይነት ታሪክ ይመስላል::

«ወንድ ሆነህ ወንድ የማትሆንበት ቦታ ስደት ነው..» */እዚህ ጋር ትልቅ ስባባል ነው እኔም የታዘብኩት ይህንን ነው::/* እየደበደቡ ፈትሸው ያለንን አራግፈው ለ15 ቀን ጫካ ውስጥ አቆዩን:: ሩዝ በበርሜል እየተቀቀለ ያለ





ዘይት ስንበላ ከረምን:: ታዲያ እሱም በሂሳብ ነው ከሌለህ የለህም አትበላም:: በዛ ላይ ዱላውን ተወው:: መረረን 12 ሆነን አንድ ላይ ተመካክረን በሌሊት ሲተኙ ጠብቀን ጠፋን:: ስናቆራርጥ...ስናቆራርጥ በስምንተኛ ቀናችን ቦሳሶ ደረስን:: */ረጅም ዝምታ/* ለምንድን ነው አሁን የምታስለፈልፈኝ?..ምን ሊረባኝ?» ተነስቶ ወጣ:: ከኪሴ ወረቀት አውጥቼ ልረሳ የምችለውን የቦታ እና የሰዎችን ስም ጫር..ጫር አደረኩኝ:: ለምሳ መብያ የሚሆን የተዘረዘረ የሶማሊያ ሽልንግ ስለሌለኝ ልዘረዝር ወጣሁ::

አይን አላይ አይል:: ጠቆር ያለች ሴት አንድ በእግሩ የሚሄድ ህፃን አንድ ደግሞ አዝላ ሌላ በሆዷ ይዛ አየሁ:: ተጠጋኋትና ሰላም ብያት ሳልፍ ስል ገርሞኝ

«እንዴት በዚህ ሁኔታ ለመንዝ አሰብሽ?» አልኳት::

«ምን አገባህ?»

«ያስቸግርሻል ብዬ ነው::»

«ያዝልኝ..አሳድግልኝ እርዳኝ ብዬሀለሁ? ምነው ፈተፈትክ የእኛ ሁማንራት (ሁማን ራይት ማለቷ ነው) የእኛ ቀይ መስቀል..» ላስረዳት ሞከርኩ:: ልትሰማኝ ፍቃደኛ አልሆነችም:: «ባክሽ ስድቡ ጥሞኛል ጨምሪልኝ..» ያልኳት ይመስል ኦርጅናል ኦርጅናሉን ብልግና ታከናንበኝ ጀመር:: ከእሷ ጋር መመላለሱ የሚያዋጣ ባለመሆኑ ቦታ መለወጥ አስቤ ወደታች ብወርድም አልተው አለችኝ:: ተከተለችኝ:: ባህሩ ዳር ሄጄ ተቀመጥኩ:: ዝምታዬ ምን መሰሏት እንደሆነ ባላውቅም የቻለችውን ያህል በኦሮሚኛም በአማርኛም ሰደበችኝ:: ከሰደበችኝ ውስጥ ሁለቱ «የደሀ ልጅ፣ መድረሻ ቢስ..» ያለችው ተስማማኝ:: ትክክል ነች:: የሁለት ደሀ ልጅ ነኝ:: የደሀዋ ሀገሬ እና የደሀዋ እናቴ ልጅ መሆኔን መች ዘነጋሁት??? መድረሻ ቢስ የሚለውም በዛ ወቅት ስድብ ሊባል የሚችልበት ሁኔታ የለም:: ስደት የወጣ ምን መድረሻ አለው? እኔማ ገና መድረሻዬንም ሆነ ማረፊያዬን ያላወኩ ተንዥ ስደተኛ በመሆኔ ልክ ነበረች::..እሷ ግን የሰደበችኝ ነው የመሰላት::

ከባህሩ ዳር ተነስቼ ወደ መዘርዘሪያው ቦታ የሚወስደውን መንገድ ተያያዝኩት:: እናቴ ላይ በፀሀይ ብርሃን የኤሌክትሪክ ሀይል ማመንጫው የተተከለብኝ እስኪመስለኝ ፀሀይዋ በረታችብኝ:: ያለ የሌለ ሀይሏን ተጠቅማ እናቴን መበርቀስ የፈለገች መሰለኝ:: መዘርዘሪያ ቦታው ጋር ስሄድ መቶ የኢትዮጵያ ብር ተቀብሎኝ ኪሱ ከከተተ በኋላ አጠገቡ ካለው ሌላ ዘርዛሪ ጋር እያወራ ይቆጥርና ለብቻው ያስቀምጣል:: ባለ 500...ባለ 1000 ለብቻ እያደረገ ይመድባል:: ብር የሚቆጥር ሳይሆን የጉሊት እቃ የሚመድብ

መሰለኝ:: ለምን ሰጥቶኝ እንደማይሸኘኝ ግራ ተጋባሁ:: የባሰ ወንበር ሰጥቶኝ «ተቀመጥ» አለኝ ሙትት ባለ አማርኛ:: ሐርጌሳ 50 ብር ሰጥቼው 12 ሺህ የበላሁበትን ቆርጦ 43 ሺህ ነው የሰጠኝ:: 3 ሺህ አጭበርብሮኝ ነበር:: በአጠቃላይ 58.000 ነው ዝርዝሩ:: የመቶው ደግሞ 116 ይሆናል ማለት ነው:: ስሌት ውስጥ ገብቻለሁ::

አንዲት ሴት አራት ልጅ ይዛ ስትለምን አየኋት:: ሁሉም የእሷ ልጆች አልመሰሉኝም:: በእድሜ የሚበላለጡ አይመስልም:: የገረመኝ ግን የራሴ ናቸው ስትለኝ ነው:: መጀመሪያ የምችል መስሏት ያወራችኝ በኦሮሚኛ ነበር:: ልጆቿ በጣም የተጎሳቆሉ ናቸው:: አንደኛው ልጅ ሰው ግጦ የጣለው የተጠበሰ አሳ ይዞ ይግጣል:: ቦሳሶ ውስጥ አሳ ጥብስ በየቦታው ሲሸጥ አይቻለሁ:: ልጁ ንፍጡ ወርዶ ከሚበላው አሳ ላይ እንደማባያ ተለጉዷል:: ዝንቦቹ ደግሞ የሚበላው አሳ ላይ ከበው ያምቧችራሉ:: አራቱም ልጆች ካለመታጠባቸው ላይ ጉስቁልናቸው ተደምሮ አሳዛኝ ሕይወት እንደሚኖሩ ያሳብቃል:: እጇን ዘረጋችልኝ:: ልጁ ታወሰኝና የሚበላው ሲያጣ፣ ሰው በልቶት የተረፈ ሲበላ በሀሳብ ታየኝ:: አማተብኩ:: ሰውየው የቆጠረውን በሙሉ ሰብስቦ በስስ ፌስታል ከቶ ጠቅልሎ ሠጠኝ:: ደነገጥኩ:: ተታሎ ነው? በምን ቋንቋ ልጠይቀው? «አንድ አሳ ጥብስ ስንት ነው?» ጠየኳት::

«4 ሺህ ነው» እንድትገዛላቸው ሰጠኋት:: ስደት ግን ስስታም ያደርጋል መሰለኝ:: ገንዘቡ ቢያንሰኝስ ብዬ ሳሳሁ:: ሳስቼ ሆድ የላትም የተባለ ይመስል ለእሷ መግዣ አልሰጠኋትም:: መጨረሻዬን ስለማላውቅ ይሆን ያሳሳኝ? እንጃ:: የእኔ ከሌላው የተለየ አይደለም:: ማንም መጀመሪያውን እንጂ መጨረሻውን አያውቅም::

የቀረኝን ገንዘብ ቆጠርኩት ከሰጠኋት ሌላ 186.000 ሽልንግ ነው:: በኋላ ልጆቹን ስጠይቅ ልክ ነው አሉኝ:: ከሐርጌሳው ይህ በጣም የረከሰ ነው:: ችግሩ ግን ግዢው ላይ ነው:: ለጅብሪል ሲጋራ ልገዛለት ወደ ሱቅ ጎራ አልኩ:: 500 ሽልንግ አውጥቼ ሲጋራ ጠየኩ:: ሱቅ ነጋሯ የአንድ ኢትዮጵያዊ ነበረችና «ይህማ ሊገዛ የሚችለው ሮዝማን አይደለም:: ሮያል ነው::» ጨመርኩና 1000 አደረኩለት:: አንድ ብቻ ሰጠኝ:: የሚያስቀው እኔ ፓኮ የሚገዛ መስሎኝ ነው የጠየኩት:: ሻይ ወይም ቡና ለመጠጣት 1000 ሽልንግ ያስፈልጋል::

አንድ ልጅ በሁለት ጓደኞቹ ተደግፎ ከወደ መታጠቢያ ቤቱ በኩል ሲመጣ አየሁት:: እግሩን ፈርከክ ስላደረገ ደብድበውት እንደሆነ ገባኝ:: የገባኝ ግን ልክ አይደለም:: ወይም አልገባኝም ነበር ማለት ነው:: ደብድበውት ብቻ ሳይሆን በኋላ ስለማ ተደፍሮም ነው:: ከደገፉት ልጆች አንደኛው አንተነህ የሚባል የአዲስ አበባ ልጅ ነበረና ተግባባን:: ታሪኩን ሲነግረኝ «...ወደ እዚህ ስንመጣ ያየነው መከራ ቀላል እንዳይመስልህ::





ቢሆንም ሶማሊያ ውስጥ ስንጓዝ ቀን..ተደብቀን እየተኛን ሌሊት ሌሊት እየተጓዝን ገረዊ የምትባለው ከተማን በርቀት እያየን ስናልፍ «ወገኖች.. ወገኖች..አአአ» የሚል ድምጽ ሰማን:: ተጠጋነው:: ለሶስት ደፍረውት መንገድ ዳር ጥለውት ሄደው አገኘነው:: ወንድ ልጅ ነው መቀመጫው አካባቢ በደም ተጨማልቋል:: ወንድ ልጅ በወንድ ልጅ ተደፈረ ማለቱ ራሱ ያሳፍረኛል:: ምን አይነት እርዳታ እንስጠው? ግራ ገባን ደግፈን ብናነሳውም መራመድ አልቻለም:: ጥለነው መሄድ የማይታሰብ ነው:: ስናዝለው እግሩ ግራና ቀኝ ሲከፈት ህመሙን አልቻለውም:: እግሩን መግጠምም አልቻለም:: ያመዋል:: ምን እናድርግ? አንዳችን አንድ እግሩን አንዳችን አንድ እግሩን አንድ ሰው ከጀርባው ይዘነው ተጓዝን:: በዛ ላይ ደብድበው ስለሆነ የደፈሩት ሰውነቱ ሁሉ ቁስልስል ብሏል:: ከመንገዱ ትንሽ ራቅ አድርገን ቀሪውን ሌሊት እዛው አሳለፍን:: ልናጥበው ብንፈልግ እንኳን ውሀ ከየት ይምጣ? በማግስቱ ሚኒና ለምነን «ላስ አኖት» የምትባለው ከተማ አደረሱን:: ህክምና ብንሄድም መፍትሄ ሊኖር አይችልም:: በቃ! ድንገት ያሳስሩን ይሆናል ብለን ስላሰብን ቁስል መጥረጊያ እና አምፒሲሊን ገዝተን ጠራረግንለት:: ኪኒኑንም አዋጥነው::

«ከጅጅጋ ፍየሎቹና ድንች ጭኖ የመጣ ሾፌር ትንሽ..ትንሽ..አማርኛ የሚችል አገኘንና የጠየቀንን ከፍለን ተጫንን:: ታዲያ ምን ያደርጋል ቦሳሶ ከመድረሳችን በፊት መኪናውን አስቁመው ውረዱ አሉን:: ምንም አይነት ገንዘብ የለንም ያለንን አሰባስበን ለባለመኪናው ሰጥተነዋል:: ሲፈትሹን ምንም የለንም:: ለምን ይፈልጉት ባናውቅም በዛ የበረሃ ሙቀት 9 ሰዓት ጀምረን ማታ ድረስ ጉድጓድ አስቆፈሩን::

«ከምሽቱ አራት ሰዓት በኋላ ከፈለጋችሁ ሂዱ አሉን:: የሚበላ ጠየቅናቸው:: በልተው የተረፋቸው ሰሀን ላይ ሳይከደን ተቀምጦ የዋለ ነበርና ብሉ አሉን:: ከነጋ ሻይና ዳቦ የበላን ነን:: ከቀማመስን በኋላ ያን የተደፈረ ልጅ እየተረዳዳን ደግፈን መንገድ ቀጠልን:: ስንጓተት 250 ኪሎ ሜትሩን 13 ቀንና ሌሊት ፈጅቶብን ቦሳሶ ደረስን:: አስብ እንዳናዝለው እግሩን ግራና ቀኝ ሲከፍተው ቁስሉ ያመዋል:: እግሩን መግጠምም አይችልም:: ተሰቃይቶ ...ተሰቃይቶ ደም እንባ እያለቀሰ ቦሳሶ ደረስን::

«ለ15 ቀናት ቦሳሶ ብንቆይም ምንም አይነት ህክምና ስላልተደረገለት ሳይድን ጀልባ አገኘን:: ቅዳሜ ልንሄድ ነው:: እንዴት እንደምንሆን አላውቅም...» አለኝ:: በእርግጥም ያ-ወቅት አልፎ ዛሬ እሱም (ተደፋሪው) የመን ሰነዓ ከተማ ነዋሪ ነው:: ሶማሊያ ውስጥ ያሳለፈውን ነገር ሲነግረኝ «..ወቅቱ በጣም ሙቀት በመሆኑ ቶሎ አልዳንኩም:: የባህሩ ውሀ ሲነካኝ ጨዋማ በመሆኑ በጣም ታመምኩ:: ጀልባው ላይ ካለው መተፋፈግ ጋር ፊንጢጣዬ እያዠቀ ህመሙ ራሴን አሳተኝ:: ሶማሊያዊያኑ እየጮህኩ

ስላስቸገርኳቸው አንስተው ወደ ባህር ሊከቱኝ ሞከሩ:: መታመሜን ነግረው ለምነዋቸው ሽሚዛቸውን አውልቀው ባህር ውስጥ ነክረው እሱ ላይ አስቀመጡኝ:: ውሀው ከመሞቁ እና ጀልባው ላይ ካለው ሙቀት ጋር ቶሎ.. ቶሎ ባህር ውስጥ ሽሚዛቸውን ለመንከር ተገደዱ:: ያም ቢሆን የባህሩ ውሀ ጨዋማ ነው:: ራሱን የቻለ ቃጠሎ ነበር የሆነብኝ:: ከብዙ ስቃይ በኋላ የየመንን መሬት ረገጥን...» ብሎኛል:: ሰነዓ ከመጣሁ ከሁለት ዓመት በኋላ ባገኘውም ታሪኩን እንድጠቀም ቢፈቅድልኝም ተጨማሪ ነገር ግን ሊነግረኝ ፍቃደኛ አልሆነም::

እወደ ሶማሊያው ቆይታ ስመለስ እኔ ጅብሪልና ጣሂር ምሳ ፓስታ እና አሳ በእርጎ ተለውሶ በልተን 54.000 ከፈልን:: ከኬንያ የሚገባ ሚሮን የተባለ ጫት ጅብሪል ገዛ፣ ፍላጎት ስለሌለኝ አልገዛሁም:: እሱ ሲቅም አብሬው ለመቀመጥ ሄድኩ:: ብዙ የሀበሻ ምግብ ቤቶች መኖሩን ያኔ ነው ያየሁት:: ውንክርክር ባለ የእንጨት ማገር ላይ በማዳበሪያ፣ በካርቶን እና በሳጠራ የተጋረደች ቤት «ኢትዮጵያ ሆቴል» የሚል በእጅ የተጻፈ ፅሁፍ ተለጥፎባት አየሁ:: በአይነ ህሊናዬ ሳጥን የመሰለ ቅርጽ እና ሽራማ ከለር ያለው ኢትዮጵያ ሆቴልን ሳልኩት::

«እነሰናይት ጋር እንሂድ? ወይስ እነ መላኩ ጋር?..»

«እኔ ምን አውቃለሁ? አንተው በምታውቅበት ውሰደኝ»

«እዛ ጨብሲም አለ::»

«እኔ ምንም አልፈልግም ብቻ ሰዓቱን ማሳለፍ ነው የምፈልገው» አልኩት

መንገድ ዳር የተሰራች ሳጠራ የለበሰች ቤት ወሰደኝ:: ወደ ውስጥ ስንዘልቅ «ውይ!..» የሚል ጩኸት ሰማሁ:: ሁሉንም ሰላም ብለን ልንቀመጥ ስንል አንደኛዋ አንገቷን ሰብራ ራሷን ጉልበቷ ውስጥ ወሸቃዋለች:: «ለምን? ምን ሆና ነው? የስደት ነገር..» አሰብኩ::

ጅብሪል «ሰኒ ፍቅር ምን ሆንሽ?» አላት::

ቀና አለች:: እኔም እንደ እርሷው መጮህ ነው የቀረኝ:: በቆምኩበት ደርቄ ቀረሁ:: ለካ አይታኝ ነው የጮኸችው:: አውቃታለሁ..ታውቀኛለች::

ሰናይት ቀይ የደስ ደስ ያላት ነች:: አሣሣቋ ደስ ይላል:: ከአፏ ብርሃን የምትተፋ ያስመስላታል:: ተነስታ ጥምጥም አለችብኝ:: እንባዋ ቁልቁል ተምዘግዝጎ ለመውረድ ጊዜ አልወሰደበትም:: ስስ ሽሚዜን አልፎ ትከሻዬ ላይ ሞቅ ያለ ፈሳሽ ጠብ አለብኝ:: «ምን ገጥሟት እዚህ ጣላት? ሳዑዲ አረቢያ ናት ሲባል ሰምቼ አልነበር? ምን አይነት ነገር ነው? እዚህ እየኖረች ነው ወይስ ለመሻገር ቀን እየጠበቀች? መዓት ጥያቄዎች ተግተለተሉብኝ:: መልስ ግን ስለሌለኝ--------አድርጌ አለፍኩት::





«ምን እግር ጣለህ?»

«አንቺን እዚህ የጣለ እግር ነዋ!»

«አትቀልድ!!!..ስራህስ? ሚስትህ..ልጅህስ?..» ሌላ ሳትቀባጥር እቅፍ አድርጌ በጆሮዋ «ዝም በይ ስለእሱ በኋላ እናወራለን» አልኳት::

«ቧ!!..ለልጅህ ጥለህ ለሚስትህ ጥለህ ትመጣለህ?» አለች ጓደኛዋ ጥፍጥ ባለ ኮልታፋ አማርኛ:: ምላሽ የለኝም:: ምን ማለትስ እችላለሁ?

«ግሩምዬ መቼ ነው የመጣኸው?»

«ዛሬ ጠዋት»

«ምንድን ነው ነገሩ? ኧረ እኔ አላምንም!!»

በእዚህም..በእዚያም ብላ ልታዋርደኝ ነው አለ ውስጤ..

«እመኝ ያመነና የተጠመቀ ይድናል» ቀልጄ ለማለፍ ሞከርኩኝ::

አጠገቤ ተቀመጠች:: ቤቷ እፍንፍን ያለች ጠባብ ነች:: በዛ አረንጓዴ ነገር ለማየት አይን ፍለጋ በሚንከራተትበትና በማይሳካለት ምድረ በዳ ሳር ተጎዝጉዞ አረንጓዴ የናፈቀው አይኔን አጠገበው:: ጭሱ እየተንቦለቦለ ከሰው ቁመት ስንዝር ከፍ ያለችውን ጣራ ተጋጭቶ እየተመለሰ ቤቷን አፍኗታል:: ዳሷ ውስጥ ያሉት ጠቅላላ ይቅማሉ - ሰናይትን ጨምሮ:: ሁለት ልጆች ጥግ ይዘው ካቲካላ ይጨልጣሉ:: 2 በሁለት በሆነችው በዚህች ዳስ ስር ይቃማል፣ ይጠጣል፣ ይጨሳል፣ ይዘሞታል:: ደስታ ውስጣቸው ሳይኖር ደስተኛ መስሎ ለመታየት መሞከር አርቴፊሻል ሳቅ፣ አርቴፊሻል ደስታ፣ ተሳቆ መኖር፣ ዳር ቆሞ ለሚመለከተው እንዴት ያስጠላል:: ሰናይትን እዚህ ማግኘቴ ገርሞኛል:: የጨርቆስ ልጅ ነች የምንተዋወቀው ራቅ ያለ ዝምድና ስላለን ነው:: ባለትዳርና የልጅ እናት ነች:: ሳዑዲ አረቢያ ሄደች ሲባል ባሏና ልጇስ ብዬ ነበር:: አጠገብ ለአጠገብ ተቀምጠን ማውራት ቀጠልን::

«ሳዑዲ አረቢያ መሆንሽን ነበር የማውቀው በምን ታምር እዚህ ተገኘ ሽ? ሳዑዲ ሶማሊያ ውስጥ ሆነ እንዴ ወይስ ሳላውቀው ሳዑዲ ገብቻለሁ?» እንደ ቀልድ ብጠይቃትም ውስጤ በማወቅ ጉጉት ተሞልቶ የነገር አንቴናውን ዘርግቷል።

‹‹ሰናይት..ሰናይት..ቢዝነስ አገኘሁልሽ። ያ-ጣጤው ሱማሌ ዛሬ አብሮሽ ማደር ይፈልጋል...›› እያለ አንድ ልጅ ገባ። ሴቶች አቃጥሮ በሚያገኘው ሳንቲም የሚኖር ወገኑን ሻጭ ነው። ደንግጬ ዞር ስል ሰናይት አፍራ በሻርፕዋ ፊቷን ሸፍናለች። መዝቀጧን በማወቄ..ጭንቷን ከትዳር ፊታ ለገበያ ማቅረቧን በመስማቴ፣ በዙሪያ በአዳር ተምና መሸቀጧ አሳፈራት ይሆን?

እንዴት ይሆን ደፍራ ቀና የምትለው? በጉጉት ጠበኳት:: ግን አልፈረድኩባትም::

ሰናይት ካቀረቀረችበት ቀና ማለት አሳፈራት:: ልጁ ደግሞ ደግሞ ሰናይት.. እያለ ቢያናግራትም ቀና አላለችም:: ቀስ ብዬ አቀፍኳት ‹‹...ይህ የህይወት ሂደት ነው መውደቅ መነሳት አለ:: ግን ለምን ሰኒ ልጅሽስ? ባልሽስ? እነሱን ጥለሽ ይህን አይነት ህይወት ይሻላል? ለምን ወደ ሀገር አትመለሽም?..›› ብዙ ብዙ ነገር አልኳት:: ልጁ አየኝ እና

‹‹እ...ቢዝነስ አግኝተሻል? በቃ አልማዝ ስሪ..›› እንደ ማፌር ብላ በእጇ ቆይ አይነት ምልክት ስትሰጠው ሰረቅ አድርጌ አየኋት:: ሰናይት ባህሩን ለመሻገሪያ ብቻ አማራጭ አጥታ እንደምትሰራ ነገረችኝ::

‹‹ሳዑዲ ናት የተባለውስ?›› አልኳት::

«ልክ ነው አዎ! ቀጥታ ሳውዲ አረቢያ ሄጄ ነበር:: ብዙ ነገር አለው መች እንደዚህ..» አመንትታ አቋረጠች::

«ለሳውዲ ፈተናማ ምኑ ይወራል ሽግር ነው» አለች አጠገቧ ያለችው ጓደኛዋ ስብርብር ባለ አማርኛ:: ትግሬ መሆኗ አነጋገሯ ያስታውቃል::

«ኦኬ!! ተይው አጋጣሚ ነው ብለን እንለፈው»

«ለአጋጣሚ አይደለም» ትግሬዋ አሁንም ጣልቃ ገባች:: አነጋገርዋ ተመችቶኛል

«ለፈ.ተና የተፈጠርኩ» ሰናይት ነች::

«ሁለና የተፈተንማ አደል?»

«ብታየው እንዴት ያስጠላል?» ሰናይት ነች::

«አንዳንዴ ህይወት እንዲህ ነች:: ያለ ነው ተዉት..» አሳዛኝ ነገር እንዳለና ተስፋ እንዳስቆረጣት ተረዳሁ:: አሳዘነችኝ:: ብሰማውስ ምን አደርጋለሁ ብዬ ነው ማጽናናት የጀመርኩት:: የራሴንም ብሶት ማስታመም አልቻልኩም:: እሷ..

«ሲያቀብጠኝ ኮንትራት ከሄድኩበት ቤት ጠፍቼ..» ብላ ጀመረች:: «ግሩምዬ ሙት አልልም ወድጄ አይደለም የጠፋሁት ምን ያደርጋል ተያዝኩና ተጠረዝኩኝ:: ባዶ እጄን እንዴት ወደ ቤት ልግባ? ዞሬ በዚህ ለመሄድ..» እንባ ተናነቃት.. ለቀቀችው:: ይውጣላት ብዬ ዝም አልኳት:: «በስደት አለም እንባ ማፍሰስ ቆሻሻ ውሃ የመድፋት ያህል ቀላል ነው::» ይህቺን ስደት አስተምሮኝ የጠቀስኳት ነች:: ተሰዶ ያነባ ያውቃታል ብዬ አስባለሁ:: እንብታ ሲወጣላት «ለምን ጠፋሽ?» አልኳት::

«ከኢትዮጵያ የወሰዱኝ ሰዎች ብዙ ቤተሰብ አላቸው:: እኔ እና እሷ የተገናኘነው አንድ ቦታ አብረን ስንሰራ ነው:: ዋናው ሰውዬ 4 ሚስቶች





አሉት:: ከእያንዳንዳቸው ከ 4 በላይ ወልዷል:: የእዛን ሁሉ አፈ ሰማይ ልብስ ማጠብ፣ መተኮስ፣ ቤት ማጽዳት..የበሉበትን ማጠብ አለ:: ምን ልንገርህ? ፈጽሞ ሰው አንመስላቸውም:: እረፍት ሊሰጡን አይፈልጉም:: ምግብ በጣም ችግር አለ:: ስድቡን..ቁጣውን..ዱላውን ካሰብከማ አይጣል ነው:: ያለው ጎረምሳ ህጻኑ ሁሉ ስሜት ማብረጃ፣ ውጥረት ማርገቢያ፣ ችሎታ መለኪያ፣ መለማመጃ ሊያረገን ይፈልጋል:: ሠውየው አራቱ ሚስቶቹ አልበቃ ብለውት እኛንም ይከጅላል::

«ለዚህ ቢበቃ ፅሩ ነበር:: ለጉንተላው ዱላው..እሳቸው አያርፉም::..» ሰናይትን አየት አድርጋ ንግግሯን ገታችው::

«እሳቸው ማናቸው?» አልኩ ስላልገባኝ::

«እነሱ....እሱ.. ለማለት ነው የምትጠቀመው» ሰናይት የቋንቋ ችግሩን አስረዳችኝ::

ጓደኛዋ አልማዝ ትባላለች:: አማርኛ ለማውራት በጣም ትጨነቃለች:: ብገላግላት ብዬ «እንድህር ደሊኺ ትግሪኛ ተዛረቢ ንዕሽተይ..ንዕሽተይ ይሰማኪኤ ምምላሱ'ዩ ዝከብደኒ» አልኳት:: ስጽፍ ነው ቀስ ብዬ ስለሆነ ያስተካከልኩት እንጂ ስናገረው ትብትብ ስላልኩ ያኔ ለእኔ ራሴም አስቆኝ ነበር:: እሷ አማርኛ ለማውራት እንደምታምጠው አምጬ አምጬ እያገጣጠምኩ በእኔ ቤት ‹‹ከፈለግሽ በትግርኛ ተናገሪ ትንሽ ትንሽ እሰማለሁ መመለሱ ነው የሚከብደኝ›› ማለቴ ነበር::

‹‹እዋይ! ንስኻ ትግራዋይ ዲኻ?»

«ኢትዮጵያዊ ኢዩ» ሰናይት ስናገር ሰምታ ስለማታውቅ ገርሟት ነበር::

«..አቤት!! የሴት ልጅ ፈተና..» ብላ አሁንም በእንጥልጥል ተወችው- ሰናይት:: ውስጤም የሰማሁትን «..አቤት የሴት ልጅ ፈተና..» ሲል ደገመልኝ:: ልታወራ የፈለገችው ነገር እንዳለ ጠረጠርኩኝ::

«ታዲያ በዚህ ሰበብ ጠፋችሁ?»

«አዎና!..» በማለት ጀመረች - ሰናይት:: «አዎና እረፍት የለንም:: ሰው አንመስላቸውም:: ያላገቡቱ መለማመጃ ሊያረጉን ይፈልጋሉ:: ስሜታቸውን ሊወጡብን ጥድፊያቸው መከራ ነው:: ያገቡትም አያርፉም:: ቀን በስራ ማታ ገላችንን በማርከስ፣ ጉልበታችን ደክሞ፣ ህሊናችን ደምቶ መኖር ስለችን:: ጠፋን:: ህጋዊ ሳይሆኑ መኖር ጥንቃቄ ይሻል:: ከባድ ነው:: ያዙኝ አልያዙን ብለን ተደብቀን መኖር ይሻላል ብለን ፓስፖርታችንን፣ የሰራንበትን፣ ልብሳችንን ጥለን ጠፋን::»

«ወዲያው ሹርጣ[4] ያዘን::» ጓደኛዋ ቀጠለች::

«ሹርጣ ምንድን ነው?» ጠየኩ::

«በአረቢኛ ፖሊስ ማለት ነው» አለችና ስናይት ቀጠለች:: «እስር ቤት ከርመን ወደ ሀገር ቤት ተላክን:: ከለበስነው ልብስ ውጭ መቶ ዶላር ይዘናል:: እኔ ደግሞ ባሌ ስራ ስለፈታ ነው መሰደድ ግድ ያለኝ:: አስብ 6 ወር ቆይተናል:: ቤተሰብ ጋ ባዶ እጅ መግባት አሳፈረን:: የእሷ ሩቅ ዘመድ ጋ መርካቶ ተክለሀይማኖት አካባቢ ስናርፍ አንድ ሰው አገኘን:: በባህር ይዞን እንደሚሄድ ነገረን:: ጅጅጋ ካደረሰን በኋላ ግን ጠፋብን:: ስንመጣ ያየነውን ስቃይ አትጠይቀን:: ሁሉም ያዩትን ስቃይ ቀምሰናል:: መንገድ ላይ የያዝነው ብር ስላለቀ መኪና እየለመንን..የደረሰብንን ሁላ በፀጋ እየተቀበልን ነው እዚህ የደረስነው::..»

በሴትነታቸው ብዙ ነገር እንደደረሰባቸው ገመትኩ:: ማውራት ያልፈለገችው ነገር እንዳለም ተረድቻለሁ:: «..ሁሉም ያዩትን ስቃይ አይተናል..» የሚለው አባባል የገለጸውን ያህል ገልጾልኛል::

እዛች እፍንፍን ያለች ቤት ውስጥ የመጠጡ ሽታ..ሺሻው፣ ሲጋራው..ጭሱ አቅለሸለሸኝ:: ወጥቼ ወደ ባህሩ ዳር መሄድ አማረኝ:: ግን እግሬ እርምጃውን እንዲገታ ያደረገ ሁኔታ ገጠመኝ:: ክንዱን በጩርቅ ጠቅልሎ ያሰረ ልጅና አንዲት ሴት ይጨቃጨቃሉ:: አራት ልጆች ቆመው ያዳምጣሉ::

«አንቺማ በምንም ታምር..ከዚህ በኋላ ሚስቴ ልትሆኚ አትችይም:: አይኔ እያየ ተኝቶሽ?» ሲል ወሬ ለማዳመቅ ከተሰበሰበው ሰው ጋር ተደባልቄ ስለነበር ሰማሁት:: ያ-የአርሲ ልጅ የነገረን መሆኑን ያወኩት ጉዳት የደረሰበት እጁን ላይ ነው:: ለምን እንደሆነ ባላውቅም በፍጥነት ወደ ጅብሪል ተመልሼ ጠራሁት:: ይዤው ስንደርስ የከበበው ሰው በርከት ብሏል::

ባልና ሚስቶቹ አሁንም ይጨቃጨቃሉ:: «..ከሌላ ሰው ጋር ግንኙነት አድርጋለች ከዚህ በኋላ ሚስቴ አይደለችም:: አትሆንምም» ይላል ባል::

«ተው እንጂ!.. ታውቃለህ ወድጄም አይደል ያደረኩት..» ትላለች ሚስት:: ሰዎች ከበውን ማስታረቅ አልመረጥኩም:: ከጅብሪል ጋር ተነጋገርንና ከግርግሩ ቦታ ገንጠል አርገን ይዘናቸው ሄድን::

«ቆይ እስኪ ወንድሜ የጭቅጭቃችሁ መነሻ ምንድን ነው?» ከስሩ መስማት ፈልጌ ነው:: ጫፍ ሰምቶ ማስታረቅ ይከብዳል::

---

[4] ለላማሌኛም ከሚለው ሌላ ሹርጣ የሚለው የሰማሁት የመጀመሪያ አረቢኛ ቃል ነው::





«የው እንግዲህ ተቀያችን ብዙ ሰዎች በየህ አርገው ሳዑዲ ዘልቀዋል:: ጥሪት ቋጥረዋል፣ ሴቷም ወንዱም ዘምነው ያማረ የፀዳ ለብሰው ያማረ ኖረዋል:: እኛም እንደዛው ለመሆን ተነጋግረን፣ ላንካካድ ቃል ተገባብተን ተነሳን:: እንዳው ደህና መተን መተን ጅጅጋ ስንደርስ መጋኛ የሆኑ ሰዎች፣ ወገናቸውን የሚበሉ ሰዎች ገጠሙን:: ቀን አጋልጠ ጣለን:: ስንት አሰቃይተው በቆሻሻ መኪና አቧራ ለብሰን ቡርኦ ድረስ መጣን:: ማነው የሚሉት እቴ ስሙ ጠፋኝ/ትንሽ እንደማሰብ ብሎ/ አብዶ አሊ የሚባል ወጠምሻ፣ መሳሪያ በያዙ ሰዎች ታጅቦ ለጉዞም ለጀልባም ድጋሚ ታልከፈ ላችሁ አታልፉም አለን:: የለንም ብለን ስንከችች ዱላው አይጣል ሆነ:: በኋላ ምን እንደነካው አላውቅም ስሬ ሽጉጥ ብላ ሲያያት «አንቺ ነይ..» ብሎ ተጣራ:: አልነሳም ብትል የእሱ ሰዎች መጥተው አንጠልጥለው ወሰዷት:: አላስወስድም ብል ቀጥቅጠው ይሄው እጄን ሰበሩኝ:: ታዲያ ከቃላችን ወጥታ ክዳኝ ከሥ ተኝታ ድጋሚ ተኔ...አኡዚቢላህ!!..» ሰቀጠጠው::

ክዳኝ ማለቱ ገረመኝ:: መካድ ማለትን እንዴት እንዳሰበው አላውቅም:: እሱ ባሰበው መንገድ ባይሆንም ይሄ ሰውዬ እንዲህ ካገኘው ጋር መተኛት ከለመደ የጤንነቱ ሁኔታ አስጊ ነው:: ይህ ከሆነ ሳትመረመር ከባሏ ጋር ትተኛ አልልም:: ይህ ለጤና ጥንቃቄ ያህል እንጂ ፍቺ የማይታሰብ ነው:: ወዳ ኡልተኛች

«ስማኝ» አልኩ ለማግባባት:: «ስማኝ..ቃሏን ማፍረሷ የቱ ጋ ነው? ወዳ ተኛች? አንተ ወንዱ ልታስጥላት አልቻልክም:: ደበደቡህ.. አቃተህ... እሷም ቢሆን እምቢ ብላ ባደረገችው ትግል እስካሁን ያልጠፋ ብልዝ ፊቷ ላይ አትርፋለች:: ከዚህ በላይ መሞት ነበረባት? አንተ በእሷ ቦታ ብትሆን ምን ታደርግ ነበር? ተደብድባ ከአቅሟ በላይ ሆኖ ለተፈጸመ ነገር ሚስቴ አይደለሽም ትላለህ? አንተ ከአቅምህ በላይ ሆኖ እንዳላስጣልካት ልብ በል እንጂ!!»

«ኧረ!..ግፍ ነው» ሲል ጅብሪል አቋረጠኝ:: ቆይ አንዴ የማለት አይነት ምልክት ሰጠሁትና ቀጠልኩኝ::

«..በእውነትም ግፍ ነው:: እሱ በጉልበት የፈጸመባት በደል አንሶ አንተም ትጨምርባታለህ? አንተ በፍቅር የተሰበረ ሞራሏን ልትጠግንላት ሲገባ ልትርቃት?.. አስብ እዚህ በሠው ሀገር ላይ ከአንተ የቀረበ ማን አላትና አይዞሽ ይበላት? ከአንተ የበለጠ ሊያጽናናት የሚችል ማን አለ? በዛ ላይ..» አንድ የእሱ ጓደኛ ሲሮጥ መጥቶ አቋረጠኝ::

«በማይባሩ መጀን..ሀሳብሁን ቀይር» አለው:: ተነስቶ አቀፋት::

እኛ ያልነውን ሰምቶ ይሁን የጓደኛውን ግዝት ተቀብሎ እርቁን የፈጸመው ባይገባኝም፣ መታረቃቸው ግን ደስ አለኝ:: ከዚህ በኋላ ጅብሪል ወደ ጫቱ ቦታ ሲሄድ እኔ ውስጤ ጥሩ ነገር አልሰማህ ስላለኝ ወደ ባህሩ ዳር መሄድን መረጥኩ::

ቦታው ቆሻሻ ነው:: ይፀዳዱበታል:: የሰዎች ፍግ..ኩስ ሜዳውን አድምቆት ኩበት፣ ሽለሽል፣ እንክልካይ..እየተባለ ያገሬ ሰው ከየሜዳው እንደሚለቅመው የሰዉ እንትን..ሞልቶታል:: ሽታ ቢኖረውም ወደዛ መሄድ ነው የመረጥኩት:: ስደት ላይ ምርጫ፣ ስደት ላይ ጥሩ ነገር መፈለግ የሚያዋጣ አልመሰለኝም:: ያውም በሶማሊያ ምድር ጥሩ ነገር ባላየሁበት.. ባልሰማሁበት ቦታ ማሰቡም ይከብዳል::

አንድ ድንጋይ ላይ ተቀመጥኩኝ:: የባልና ሚስት ፀብ ትዝ አለኝ:: «የወሎ ሼኾች በስማቸው የሚመጀኑባቸው» የሚል የካቲት መፅሔት ላይ ያነበብኩትን ጽሁፍ አስታወስኩ:: ሁሉም ነገር ተምታታብኝ:: በጣም ከፋኝ:: በአየሁት፣ በሰማሁት በሙሉ አልተደሰትኩም:: እንዲያው አንድ እንኳን ደስ የሚል ነገር የለውም::

ዳግም ሆድ ባሰኝ አልቅስ..አልቅስ አለኝ:: ግን አልቻልኩም:: ሁሉ ነገር ህልም ቢሆን ተመኘሁ:: ምኞቴ ምኞት ነበር:: እውን የማይሆን ድኩም ምኞት:: ውስጤን መጥፎ ከሚባል በላይ የመጨረሻ መጥፎ ስሜት ሰቅዞታል:: አልቅስ..አልቅስ ጩህ..ጩህ..የሚል ስሜት ይገዳደረኛል:: ብጮህ ወደድኩ ምን ሆንክ ብሎ የሚከበኝን ሰው ምን ምክንያት እሰጣለሁ? ማልቀሱ ሳያዋጣ አይቀርም ላስነካው ዳዳሁ:: ምናለ እንዲህ ሲከፋ..ሆድ ሲብስ እንባ አፍስሶ የውስጥ ረመጥን ቀዝቀዝ ማድረግ ቢቻል? ሴቶች እንዴት ታድለዋል? ነፃ ናቸው::

«ለምን ታለቅሳለህ ሴት ይመስል..ወንድ ልጅ አያለቅስም..አታልቅስ ወንድ አይደለህ?» በሚል ማህበረሰብ ውስጥ ሆነን የውስጥ ስሜት ማውጫ..መተንፈሻ የሆነውን እንባ ስንከለክል ነው ያደግነው:: ለእነሱ ግን ነፃ ነው የሚል የቅናት ሀሳብ ሽው አለብኝ:: «ወንድ ልጅ ሲከፋው አለያም ሆድ ሲብሰው ነው የሚያለቅሰው ለምን ታለቅሳለህ..» ያሉኝ ጅጅጋ ድረስ አብረውኝ የመጡት ሴትዮ ትዝ አሉኝ:: አሁን አሁን ቶሎ ቶሎ እንባዬ እየመጣ አስቸግሮኛል:: በትክክልም ሆድ እየባሰኝ..እየከፋኝም ነው:: ምን ደህና ነገር አየሁና ደስ ይበለኝ? ዘመድ ሲሞት ማልቀስ የሚያቅተኝን ያህል አልቅስ..አልቅስ ይለኛል:: ባየሁት ነገር ተከፍቻለሁ..:: ስለስደት ያለኝ ግምት ስህተት ሆኖ ነው ያገኘሁት:: ለካ ሁሉም እንደ እኔ የተሳሳተ ግንዛቤ ይዘው ነው ለዚህ ሁሉ ስቃይ የሚዳረጉት…ያየሁት የሰዎች ስቃይ ብቻ ሳይሆን ለእኔስ ወደፊት ምን ይገጥመኝ ይሆን የሚለውም ጭምር ውስጤ አስበ





አልቅስ..አልቅስ የሚል ስሜት የፈጠረብኝ:: በእርግጥ የማየው ነገር ሁሉ ቢያስለቅሰኝም አሁን በዚህች ደቂቃ ግን አልቻልኩም::

ባለቅስስ ይወጣልኝ ይሆን? እንጃ!!...ከባህሩ ዳር ተቀምጬ ንፋሱ ሽው እያለ ውስጤ ሀሴትን ሊፈጥርልኝ ቢጥርም ያየሁ..የሰማሁት ነገር ውስጤን አቁስሎት ምን ደስታ ይሰማኝ? ውስጤ ትርምስምስ ያለ ስሜት አለ:: ንፋሱ «ሿ..ሿ..ሿ..» እያለ አንከባሎ ያመጣው የሲጋራ ወረቀት አጠገቤ ደረሰ:: አየሁት ውስጤ የሚተራመሰውን ሀሳብ ፃፈው..ፃፈው አለኝ:: አነሳሁት.. እስክርቢቶዬን ከደረት ኪሴ ሳብ አረኩና የሲጋራ ወረቀቱ ላይ ተከልኩት:: ውስጤ አልቅስ..አልቅስ እያለኝ ሲተራመስ ያለመቻሌን ፃፍኩት!!

ዋ! እስማንባቴ
ከአይኔ እንባ እልቆ
ውስጤ እያነባ ከላይ ደርቆ
ዋ!!! እስማንባቴ
ሂ!!!...አድርጌ እስማሳየቴ
ተቃጥሎ ሲገም አካሌ
ዋ!!!...ማንባት አለመቻሌ
ማንባት ብችልማ አንብቼ
የውስጥ እሳቴን አጥፍቼ
እፎይ ባልኩ በእንባዬ
ከምታገል ተቃጥዬ
እንባ አዋጡልኝ ሙሾዬን ላውርደው
የተገዳሁትን እኔ ነኝ የማውቀው
ቅኔ ደርድሩልኝ ስንኙንም ቋጥሩ
እኔ እኔን ጠላሁት ውስጤ በማረሩ
ደረቴን አልደቃ እንደሰው
ፊቴንም አልነጭ ላቅለሰው
ወንድ አያለቅስም ብለው
አርሬ እንደሞት አድርገው
አሁን እንዴት ላንባ
ሲከፋኝ ሆዴ ሲባባ
ዋ!! ማንባት ብችልማ
ያሉትን ደበሉ ብልማ
ጥንድ..ጥንዱን አንዝቅዝቄ
ህቅ!!! ባልኩ ተንሰቅስቄ
ሀዘኔ በወጣ በታወቀ ለሰው
እምቁ ከማልመሰምሰው
እርዱኝ...እርዱኝ እባካችሁ
ትርፍ እንባ ያላችሁ
አልቅሱልኝ ለእኔ እሮ ሞተ ብላችሁ

ይሄም ሀሳቤን አልገለጸልኝም:: ወንድ ሆኖ በሶስት ወንድ የተደፈረው ልጅ በአይነ ህሊናዬ ድቅን አለ:: እያየ ሚስቱ የተደፈረችበት የወሎው ሲራጅ በሀሳብ ታየኝ:: የተሰበረ እጁ ታወሰኝ:: ምን አይነት ህክምና ሊያገኝ ይችላል? ገና ባህር ተሻግረን የመን? እስከዛ ችግር ቢገጥመውስ? ሌላ ሀሳብ ሚስቱ ብታረግዝስ? ኧረ..ማርገዝ ቀላል ነው የደፈራት ሰው በሽታ ቢኖርበትስ?..ዘገነነኝ::

«ምነው ብቻህን?» ጅብሪል ነው::

«ብቻዬን አይደለሁም:: እንዴት መጣህ? ጫትህን ጨረስክ?»

«ሁኔታህን ሳስበው ያመመህ ወይም የሰለቸህ ስለመሰለኝ አይቼህ ልመለስ ብዬ ነው»

በዚህ የስደት ቦታ የሚያስብልኝ አንድ ሰው ማግኘቱ ደስ አለኝ::

«ከባህሩ ጋር እየተጫወትክ ነው?» ዝምታዬን ለመስበር እንደጠየቀኝ ገባኝ

«ከሀሳቤ ጋር»

«ምን እያሰብክ ነው?»

«የሚታሰብ ይጠፋል ብለህ ነው? መቀመጥ ያቃተው የተደፈረው ልጅ... እርጉዟ ሴት..እጁን የተሰበረው ልጅ...» በመሀል አለመታከሙ ትዝ አለኝ:: «..ቆይ ኧረ!..እጁን የተሰበረውን ልጅ ምን እናድርገው? ህክምና ካላገኘ በኋላ አካሉን ቢያጣስ?..» ደነገጠ፣ ድንጋጤው ፊቱ ላይ በጉልህ ይነበባል::

«ታዲያ ምን እናድርገው?..ህክምና..» በእንጥልጥል ተወው:: ክንዴን ያዝ አርጎ ጎተተኝ:: «እኔ ጋር ብር አለ እናሳክመው» ብር አወጣ ሀኪም ፈልገን ይዘነው ሄድን:: ውስጤ እንደፈራው አይደለም::

ተመስገን!!!

ውሎው ውሎ ሳይሆን የሚያሳዝን ነገር በመስማትና በማየት አሳለፍኩት:: አሁን የአዳሩ ነገር ነው ውስጤን ያሳሰበው:: ጅብሪል ወደ ጋሽ ሰለሞን ምግብ ቤት ይዞኝ ሄደ:: ሜዳ ላይ ሁሉ ሸራ ላስቲክ..ማዳበሪያ.. የያዙትን ልብስ አቧራው ላይ እያነጠፉ ያገኙትን ትራስ እያደረጉ ሜዳው ላይ ተጋድመዋል:: ግማሹም ያነጠፈው ላይ ተቀምጦ፣ ታሪኩን፣ ትዝታውን፣ የቀየውን፣ የአድባሩን፣ የአውጋሩን..ግለ-ታሪኩን ያሳለፈውን ያወጋል:: ከዛ ቀድሞ በዚህ መንገድ ከመጣ ስለገጠመው..ይጠርቃል:: ተጠጋናቸውና ተቀመጥን::





«..ኢንዲያ..በጣም ጨካኝ ነች:: ካልሆነ መሀል ላይ የጫናችሁትን ገልብጣችሁ ኑ.. ትላለች:: የሐረር ሰው ነች..ባሏ ቦሳሶ ያለው ፖሊስ ጣቢያ አዛዥ ስለሆነ ነው እኮ እንዲህ እንደልቧ የምትሆነው..ጨካኝ ነች..ይሄን ግፏን አይቶ አውሬ ወለደች:: *(ይህ ወሬ በሰፊው ቢወራም የሕካል ጉዳት ያለበት ልጅ ስትወልድ ሰዉ ካለው ጥላቻ አንፃር አራት እግር ያለው አውሬ ወለደች ብሎ አወራባት..)* መሀመድ ደሬ[5] ገንዘብ ያግኝ እንጂ የፈለገ ችግር ቢገጥምህ አያዝንም:: ..ሁሉም የየራሱን ያወራል::

«ኢንዲያ ማነች?» አንዱን ጠየኩት::

«..የሐረር ሰው ነች:: በጣም አረመኔ ነች:: የራሷ ጀልባ አላት:: ሰው ከተጫነ በኋላ ችግር ቢከሰት፣ ጀልባው ቢበላሽ ገልብጧቸውና ኑ ትላቸዋለች:: በባህር የሚሄድ ስደተኛ ላይ ያልሰራችው ግፍ የለም..» የሚል ምላሽ ሰማሁ:: እያንዳንዱ የሚያወሩትን ታሪክ ለማዳመጥ ብሞክርም አልቻልኩም:: መደማመጥ ባልሰፈነበት ሁኔታ ነው የሚያወሩት:: «..ለ11 ጊዜ በባህር ተመላልሻለሁ» ያለው አንድ የወልዲያ ልጅ ትኩረቴን ሳበው:: «ለምንድን ነው ይህን ሁሉ ጊዜ የምትመላለሰው?» ትኩረቴን ብቻ ሳይሆን አቀማመጤንም ሳበውና መቀመጫዬንም ወደ እሱ አስጠጋሁ::

«በቃ! ስያዝ ስመለስ..ስያዝ ስመለስ አንዴም ገንዘብ አገኝሁና ቁም ነገር ልሰራ ብዬ ተመላለስኩ::» እንደቀልድ ማውራቱ ገረመኝ:: አስራ አንዴ የሚለውን ቃል በውስጤ ከ11 ጊዜ በላይ ሳልደጋግመው አልቀርም ተገርሜ:: ማሰቡም ይሰቀጥጣል::

«መጀመሪያ እንዴት መጣህ? በዚህ መንገድ መኖሩን በምን አወክ?»

«መጀመሪያ ስመጣማ ታላቅ ወንድሜን ተከትዬ ነው:: ታጋይ ነበር:: ከድል በኋላ በ1984ዓ.ም አካባቢ ሲቀነሱ ሰለሞን የሚባል የትግል ጓደኛው ሳዑዲ አረቢያ እንሂድ ብሎ ይዞት መጣ:: ያኔ ቤታችን ተለወጠ:: ቦታ ገዝቶ የሰራው ቤት እንዲህ የዋዛ አይደለም:: ለወልዲያ ልጆች አርአያ የሆነው እሱ ነው:: እኔም በ1990ዓ.ም. በዚህ በኩል መጣሁ::» አቋረጥኩት::

«መጀመሪያ ስትመጣ ችግር አልገጠመህም? መንገዱ እንደ አሁኑ ያስቸግር ነበር?» ጥያቄዬን ሲሰማ ፈገግ አለ::

«ችግሩ የጀመረኝ ከአዲስ አበባ ነው:: አሜሪካ ጊቢ ያሉ ማረፊያዎ-ችን ተጠቁሜ ስለነበር ወደዛ ሄድኩ:: ማረፊያዬን አዘገጃጀሁና ወጣ አልኩ:: ከዛ በፊት አዲስ አበባ ብመጣም አንድ ቀን ብቻ ስለሆነ ያረፍኩት አሁን ትንሽ ዞሬ ልይ ብዬ ነው አወጣጤ:: ሀብተጊዮርጊስ አካባቢ ስደርስ አንዱ

[5] ይሄ መሀመድ ደሬ የሚሉትም መላኩ የሚባለውን ኢትዮጵያዊ ምግብ ቤት አሸባሪዎች ሲያፈነዱበት ጉዳት ደርሶበት እግሩን ተቆርጦ ነው ያለው::

ከፊት ለፊቴ እየሄደ ጭብጥ የሚያክል ወርቅ ከመሬት አፈፍ አረገና አነሳ:: ሣየው ደነገጥኩ:: ወደ እኔ መጣና «ዝም በል ለማንም አትንገር» አለኝ::

«ኧረ!..ማንን አውቄ» አልኩት:: እኔና አንተ እንካፈላለን ሲለኝ «ያ-አላህ ተየሁ በወርቅ ገድ አልከኝ?» ብዬ ሳልጨርስ «ያዘውና ገገር ይገቼ ልምጣ ለሰው እንዳታሳይ..» ቀስ አርጎ አስጨበጠኝ:: እዚህ ጋር ጠብቀኝ ብሎ ወደ ብሎ የሆነ ቦታ አቆመኝ:: ሆቴል ነገር በር ላይ ነው ጠብቀኝ ብሎ ወደ ውስጥ የገባው «ሽጠን እንካፈላለን» ስላለኝ ምን ያህል ተሸጦ ምን ያህል እንደሚደርሰኝ አሰብኩ:: እርምጃውን ገታ እና ወደ እኔ ተመለሡ:: «እህ..! ይዘህ ብትጠፋስ? ይሄ እኮ ከ10.000 ብር በላይ የሚያወጣ ንብረት ነው የሆነ ነገር አስይዘኝ..» ደነገጥኩ:: የብሩ ብዛት አስደነገጠኝ::

«ኧረ ምንም የለኝ?»

«ስንት ይዘሃል?» ኪሴን ፈተሸ..ፈተሸ አድርጌ 500 ብር ሰጠሁት:: እሡ ዞር ሲልልኝ ለመሰወር አስቤ ነው የሰጠሁት:: ቤተሰቦቼ የአዲስ አበባ ሞጭላፋ እንዳይሞጨልፍህ ተጠንቀቅ ያሉኝ ታወሰኝ:: ምኑን ሞጭላፋ ናቸው እቴ ጭብጥ ወርቅ አግኝቶ የሚያካፍል ጅል ሁላ!! በዚህች 500 ሽኝቼ 10.000 ብር የሚያወጣ ወርቅ ይገፔ ልሰወር አሰብኩ..በእኔ ቤት ብልጥ ልሆን ነበር:: ለካ ነገሩ አርቴፍሻል ነበር:: ያኔ ዋቴ ተሰራሁ:: ከዛ የጀመረ እዚህ ድረስ ብስጭት እየጨመረ በፈተና በስቃይ ደረስኩ::

ጅጅጋ ያገኘኋቸው ሁለት የናዝሬት ልጆች መንገድ እናውቃለን ቋንቋ እንሞክራለን ስላሉኝ ከእነሱ ጋር ሆንኩኝ:: ሌሎችም ሁለት ልጆች አገኘን እና በጭነት መኪና ተጫንን፤ ብዙም አልሄድን አስወረዱን:: ያኔ ሶማሌዎቹ የእርስ በእርስ ጦርነት አላቸውም አይደል? መሳሪያ የያዙ ሲይዙን፣ ሲፈትሹን፣ የጉልበት ስራ ሲያሰሩን፣ ሲደበድቡን፣ ሲለቁን ሌሎች ሲይዙን..ብቻ ምን ያልሆነው አለ? ቡርኦ ሌላ አንድ ልጅ አገኘንና 6 ሆንን:: ቀን..ቀን ተደብቀን እየተኛን ሌሊት ሌሊት እየተጓዝን ገረዊ የምትባለው ከተማን በርቀት እያየን ስናልፍ ያዙን:: የከፋው ነገር ያኔ ነው የገጠመን:: ፈተሹን ክርስቲያን እና ሙስሊም ተለዩ ተባለ:: ተለየን:: ሁለት ልጆች ብቻ ናቸው ክርስቲያን ነን ብለው የቆሙት:: ሌሎቻችሁ ሙስሊም ከሆናችሁ አሽዱ እስኪ አሉን:: አሽድን የማያውቁትን ልጆች በአማርኛ አንዱ ልጅ እኔ ቀድሜ ስለምል ልብ በሉና ሰምታችሁ እናንተም ያንኑ ድገሙ:: እንድትሰሙኝ ረጋ ብዬ በቀስታ እላለሁ አለ::

«አሽዱ ላ-ኢለላ ማሀመደ...» ሁለቴ ደገመው:: በሶስተኛው ሁላችሁም እኔን እየተከተላችሁ በሉ አለንና ሁላችንም አልን:: እኔ እንኳን ሙስሊም ስለሆንኩ ቀድሞም አውቀዋለሁ:: ሌሎቹን ግን እንዲያመልጡ ረዳቸው:: ክርስቲያን ነን ያሉትን ሁለቱን ልጆች ደግሞ አይናችን እያየ





ሲገሉዋቸው ሲሉ ያው ልጅ ስለቁርዓን ስናስተምራቸው ስለነበር ሊሰልሙ ተስማምተናል ሼህ እስክናገኝ ነው እና ብትችሉ ሀጀር (ጽድቅ) ታገኛላችሁ ከምትገሏቸው ከሼክ አገናኙን አላቸው:: ሁላችንንም አሳድረውን አውለውን እነሱን አስልመው ለቀቁን:: ከመንገዱ ትንሽ ራቅንና ቀሪውን ሌሊት እዛው አሳለፍን:: ልጁ «ህይወታችሁን በዚህ ሁኔታ ካተረፍኩ እምነታችሁን እንደፈለጋችሁ..›› አላቸው:: በማግስቱ መኪና ለምነን «ቦሳሶ» የምትባለው ከተማ አደረሱን..»

ረጅም ትረካውን ተመስጬ ስሰማ ያለ እንቅልፍ ማደሬንም ረሳሁት:: ሁሉም አሰቃቂ የሆነና የሚገርም ታሪክ የሚያወሩት በጉዞ ስለገጠማቸው ነው:: ስሙ ማን እንደሆነ ያልተዋወኩት ተራኪዬም ስለባህሩ ጉዞ ሊያወራልኝ ወደደ:: ስለጉዞው ምንም የማውቀው ስለሌለ ይበልጥ ጆሮዬ ተከፈተ:: እንቅልፍ የት አባቱ!

«አንድ ጊዜ ደግሞ..» በማለት ጀመረ:: «..ትሳፈራላችሁ ብለው ከዚህ ከተማ ካወጡን በአራተኛው ቀን ወደ 10 ሰዓት ላይ ተጭነን ዶኒክዋ (ጀልባዋ) ጉዞ ጀመረች:: እፍግፍግ ብለን ነው የተጫነው:: ደክሞህ እግርህ ዝሎ ስትነሳ በዱላ «ቋ!» ያደርጉሃል:: ሙቀቱ ሙቀት እንዳይመስልህ:: ባህር ላይ ሲሆን ይብሳል መሰለኝ:: ከአራት ሰዓት ጉዞ በኋላ ጀልባዋ ተበላሸች:: ሁላችሁም በየሀይማኖታችሁ ጸሎት አድርጉ ተባለ:: ግማሹ «አቡነ አረጋይ አውጡኝ..ግማሹ ያ..አላህ ያ..አላህ..አላህ ወ አክበር..» ግማሹ ደግሞ «..እግዚአብሄር ሆይ..» ሲል አንዱ «ምነው የእናት የአባቴ ክራማ አጋልጠህ ትሰጠኝ?» አለ ሣኩኝ:: ሳቄን ግን ማፈን አልቻልኩም አመለጠኝ:: ሶማሌው አንስቶ ወደ ባህር ሊወረውረኝ ነበር:: ከዛ ተርፌ እኔም ወደ ጸሎቴ ተመለስኩ:: በተፈጥሮዬ እንደዛን ጊዜ ያለ ጸሎት አድርሼ አላውቅም:: ሶላት ሳላዛንፍ ብሰግድም የዛን ጊዜ ፈርቼ ስለነበር በጣም ፀለይኩ:: የዶኒኩ /የጀልባው/ ሞተር የተነሳው በእኔ ፀሎት ሁሉ መሰለኝ:: እንደምንም ተጎርጉሮ ሞተሩ ተነሳና ጉዞ ጀመርን:: ለ13 ሰዓት ከተጓዝን በኋላ ማዕበል ተነሳ:: ወደኋላ መመለስ አልቻልንም ወደፊት መሄድ አልቻልንም:: ጀልባው እንዴት ይንቀሳቀስ? በጣም አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ገባን:: አቅጣጫም ሳቱ:: ወደ የትም መሄድ አልቻሉም:: ሞተር አጠፉ:: ከዚህ በኋላ ማዕበሉ ወደሚገፋው አቅጣጫ ብቻ ነበር የሚሄደው:: ባህር ላይ ለ16 ቀን ለመቆየት ተገደድን:: ከሰላሳ ስድስት እስከ 40 ሰዓት ቢፈጅ ነው ተብሎ የተያዘ ስንቅ አለቀ:: ከረሀቡ ይልቅ የጎዳን ውሀ ጥሙ ነበር:: ርሀብም አረገፈን::

የሞተ የሞተውን ወደ ባህር እየጣልን ከ112 ውስጥ 39ኙ ባህሩ ሲበላቸው ሌሎቻችን በአስራ ስድስተኛው ቀን ትልቅ የአሜሪካን መርከብ ሲመጣ ዘራፊ መስለናቸው ለስለላ የላኩት ሄሊኮፕተር አቅጣጫ ጠፍቶን

እንደሆን ሲያውቅ ምግብ በገመድ ላኩልን። ማዕበሉ ሰክኖ ስለነበር አቅጣጫ እየመሩ ወደ ዳር አወጡን።..»

እውነት እውነት አልመሰል አለኝ። ለ16 ቀን ያለ ምግብ ያለ ውሀ..መቆየት እንዴት ተቻለ? ብዬ ሰነዓ ከተማ ከገባሁ በኋላ ብዙ መረጃ አሰባሰብኩ። ያገኘሁት መረጃ ከዚህ በከፋ መልኩ እንደነበር ነው። የተረፉት ሰዎች የሞቱትን ስጋ እየበሉ ህይወታቸውን እንዳተረፉ በተለያየ ጊዜ ያገኘኋቸው 3 ሰዎች የሰጡኝን ምስክርነት በቂ ነው። 2 ሰዎች ከተረፉት መካከል ብለው አንድ አይነት ስም ጠሩልኝና ያንን ሰው ፈልጌ አናገርኩኝ። ስሙን እንድጠቅስ ፍቃደኛ አልሆነም።

በእርግጥም በሰዓቱ የሞተ ጓደኞቻቸውን የበሉ አሉ። እኛ ግን..ሽንታችንን እየጠጣን ውሀ ጥሙን ለመቋቋም ችለናል ሲል ምግቡን አድበስብሶ አልፎታል። ከዚህ በተጓዳኝ ባህር የሚያቋርጡ ስደተኞችን የጫነ ጀልባ ሰምጦ ሁሉም ሲሞቱ አንድ ሰው ከ12 ቀን በኋላ ጅቡቲ ጠረፍ ላይ በህይወት ተገኘ። ዛሬ በሰነዓ ከተማ ሆቴል ከፍቶ አለ። ባህር ተፍቶት በህይወት አሳ አጥማጆች አግኝተውት እንካ ወገንህ ነው አስታመው ብለው የሰጡት ልጅ ነው ያወራኝ። አስታሞ ለዛሬ እሱነቱ ያበቃው ሰው ሰለሞን መርሻ ይባላል። በዛን ጊዜ ነዋሪነቱ ጅቡቲ ነበር። ባለታሪኩ ያን ወቅት ሳስታውስ ያመኛል አታንሳብኝ በሚል ልንነጋገር አልቻልንም። እውነታውን ግን አልካደም። ብዙ ብዙ ተረት..ተረት የሚመስሉ ነገሮች ይሰማሉ። አሰቃቂ..አሳዛኝ..ለማመን የሚከብዱ ታሪኮች ይደመጣሉ።

በሳሶ ያገኘሁት ተራኪዬ ለማመን የከበዱኝ ከማንም መረጃ ያላገኘሁላቸው ብዙ ነገሮች ሲያጫውተኝ ከሌሊቱ ዘጠኝ ሰዓት ሆነ። ከዚህ በኋላ የትም ሆቴል አልጋ ፍለጋ መሄድ እንደሌለብኝ ራሴን አሳምኜ ከእነሱ ተጠግቼ ተኛሁ። ከከተማዋ ጋር አንድ ላይ የተዋወኩት ጅብሪል ቀድሞ እንቅልፉን በከባዱ ተያይዞታል። በመሀል..በመሀል ለህልሙ ማጀቢያ/ሳውንድ ትራክ/ ማንኳረፍ በረጅሙ ይለቅብናል። እኔ ግን ሰውነቴን አጋደምኩት እንጂ አእምሮዬን ማሳረፍ አልቻልኩም። እንቅልፍ አጥቼ ስንዝ እንደ ማደሬና ያለ እረፍት ወዲያ ወዲህ ስል እንደመዋሌ ገና ጋደም ከማለቴ ጭልጥ አድርጎ ይወስደኛል ብዬ ነበር። በተገላቢጦሽ ቀን ስለገጠሙኝ ነገሮች በዓይኔ ውል እያሉ ያስቸግሩኝ ጀመር። አይኔን ሰብሮ ካልተጨፈንኩ ብሎ ያስቸገረኝ እንቅልፍ የት እንደገባ አጣሁት። ውሎዬን ሳስበው ጥሩ ነገር የማየት ህልሜ የተንጠፈጠፈ መሰለኝ። ብዙ ተስፋ አስቆራጭ ነገሮች ሊገጥሙኝ እንደሚችሉም ታሰበኝና ‹‹ግሩምዬ የመጣውን ሁሉ ለመታገል ቆፍጠን በል። ጠንካራ ሁን፤ ትዕግስት የለኝም የሚለው ሀሳብህ ከንግዲህ ቦታ የለውም። ብዙ ትግል ሊጠብቅህ ይችላል። አሁን የተያያዝከው ስደት ነውና የበለጠ መራር ሊሆን ይችላል። ደግሞም ነው። ጠንክር በል..›› ስል ራሴን መከርኩት። አበረታታሁት።





ይህን የሰው ልጅ ስቃይ፣ የእኔ ገጠመኝ፣ የሰማሁት..ያየሁትን መጻፍ እንዳለብኝ አመንኩ። ቢያንስ በዚህ መንገድ ሊመጣ ያሰበ አንድ ሰው ቢያነበው ሊቀር ስለሚችል የአንድ ወገኔን ህይወት ባተርፍ ደስተኛ እሆናለሁ ብዬ አሰብኩ። ማስታወሻ መያዣም ለመግዛት ወሰንኩ።

የፈጅር አዛን ካለ በኋላ እንቅልፍ ወሰደኝ። ነግቶ ረፍዶ ጠዋት 5 ሰዓት ስነሳ አቧራ ላይ ሲንከባለል ያደረ አህያ መስያለሁ። ከቁርስ በፊት ገላዬን ለመታጠብ ሄድኩ። ስመለስ ጋሽ ሰለሞን ምግብ ቤት ገባሁ። በሁለት ብረት ምጣድ ላይ እንጀራ ይጋገራል። አክንባሎ ተብዬው ቆርቆሮ ክዳንና ጋጋሪዋ እኩል ላቦት ያንቆረቁራሉ። ቀኑ አልገፋ ያላቸው ስደተኞች ቁርስ በልተው ካርታ መጫወት ጀምረዋል። ሴቶቹ ድምጻቸውን ከፍ አርገው ያወራሉ። በሆነ ነገር እጅግ መደሰታቸውን ያስታውቃሉ። ይቦርቃሉ፣ ያሽካካሉ..ያሽቃብጣሉ። አንዱን ስጠይቅ የዚህ ሁሉ ደስታ ምክንያቱ ጓደኛቸው በስደተኛው ዘንድ ጋሽ ሰለሞን የሚባለውን አሮጌ ጣሳ የመሰለ ሰውዬ ስላገባች ነው። ያጥላላሁት ቀንቼ ይሆን እንዴ?

‹‹ወንድሜ ይህን ባህር ከመሻገር አረፈች›› አለኝ አንዱ አጠገቤ ያለ። ዞር ብዬ አየሁት የፊቱን ቅርፅ ለመናገር ይከብዳል። ከእኔ የባሰ ቅርጻ ቢስ ነው። ፒንታጎን ይሁን ሄክሳጎን ለማወቅ ካርታ ማስነሳት የሚያስፈልገኝ መሰለኝ።

«ማነች? ምን ስላገኘች ነው ባህር ከመሻገር ያረፈችው?» ግራ ገባኝ።

«ያቺ መካከል የተቀመጠችውን እኮ ነው ጋሽ ሰለሞን ያገባው።»

‹‹...አገባ እንዴ? ገና ልጅ አይደለች ይሄን ሽማግሌ እንዴት ታገባለች? ባህር ከመሻገር አረፈች ያልከኝስ እሱን ስላገባች ነው?›› ሀሳቡ ሁሉ እንደ ፊቱ ቅርጽ የተጥመለመለ መሰለኝ። እድሉን እንደ በቆሎ እሸት ግጦ ጨርሶ በሰው እድል የሚያንቋልጥ አድርጌ ሳልኩት። ለነገሩ ሁሉም ናቸው ‹‹ታደለች›› ያሉት። እስተያየቱ በጠላትኛ መሰለኝ እንዲያውም በሆዱ ሁሉ ‹‹እናትን ልክዳ›› ብሎ ሳይሰድበኝ አይቀርም። ትክክለኛ አባባሉን እንዳልባልግ ብዬ አላስፈርኩትም።

ሌላኛው ‹‹..አገባ እኮ ቅድም ግብዣው ቁርስ ሲታደል አልነበርክም እንዴ?›› አለኝ።

‹‹ቢሽመግልስ? ያለው ገንዘብ ቀላል ነው እንዴ? ከዚህ በፊት ያገባት ብታያት ምን ልትል ነበር? ከዚህች ያነሰች አንዲት ፍሬ ልጅ ነበረች። እሱም ቢሆን እኮ ምስኪን ነው ያሳዝናል ሁለት ሚስቶች ሁለት አመት

ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ስለሞቱበት ሀዘን ጎዳው እንጂ ምን ይወጣለታል?...›› የመጀመሪያው ተናጋሪ ነው።

‹‹እንዴ!...ምስኪን ነው ያሳዝናል ይለኛል እንዴ? ይሄን ሁሉ ሴት መርጦ እንደፈለገው እያገባ ምኑ ላይ ነው ምስኪንነቱ?›› ይባስ ብሎ መርጦ እንደፈለገው ... ሲዳዳው ተነስቼ ወጣሁ። ሀብታም እና አንድ ፍሬ ህጻን ነው ለማለት ሲዳዳው ተነስቼ ወጣሁ። ጅብሪል ሲፈልገኝ ተገናኘን።

«ስማኝ እዚህ ሀገር ኤድስ እንዴት ነው?»

«ምነው አንዷን ደፋህ እንዴ? ነው በህልምህ ቆሞ ታየህ?» ቀለደብኝ።

«አይ! የጋሽ ሰለሞን ሚስቶች እንዴት ተከታትለው ሞቱ አሳስቦኝ ነው»

«ምን አሳሰበህ? እዚሁ ኮንደም ልትሸጥ ፈለክ እንዴ?»

‹‹አትቀልድ››

«እዚህ ውስጥ ጤነኛ አለ ብለህ ነው?›› አለኝ።

«በባህር መጪው ሁሉ በሽተኛ እንዳልሆነ አስብ።» (ሰነዓ ከገባሁ በኋላ የገጠመኝ ይሄው ነው። በዛ ያሉት በባህር የመጣ ሁሉ በኤድስ[6] የተለከፈ አድርገው ነው የሚያዩት። በዚህ በሽታ የሚረግፈውም ኢትዮጵያዊ ቁጥር ቀላል አይደለም። ስደት ላይ ሌላኛው ጠላት ማለት ይሄ ነው።)

«አስገድዶ መድፈር ባለበት በሽታ ይጠፋል ብለህ ነው? ሰለሞን ደግሞ ያገኘውን ቀሚስ ይለብሳል። ሁሉ ልኩ ነው። ታዲያ ምን ይደንቃል? ይህቺም ብትሞት ሌላ ያገባል። እሱን የሚያስቡት ገንዘብ እንዳለው ነው...»

በዝምታ መንገድ ቀጠልን። ስንቶችን ለክፎ ይሆን? ስንቶቹስ ለስንቶች አከፋፍለው ይሆን? ያልፍልኛል ብሎ ስደት ተወጥቶ ህይወት ሲጠፋ ታሰበኝ። ግን ምን ማድረግ እችላለሁ? ሁሉ ጋር ጥልቅ የሚለው ነገረኛው የስሜት ህዋሴ..ሌላ ቢያጣ በዚህ ወጥሮ ያዘኝ። ስደት የሚወጣው ሰላም ፍለጋ አለያም የተሻለ ኑሮ ለመኖር ነው። አብዛኛው እንደ እሳት እራት በመጥፊያው ላይ ሲሽከረከር፣ መጥፊያው ላይ ሲርመጠመጥ ነው ያየሁት። በሀገር ላይ ለምኖ ማደር ያቃተ ይመስል ለመለመን መሰደድ እጅግ የሚያስከፋ ነው። ትንሽዬ ጥቅም ታይቶ ህይወትን ያህል ነገር መገበር ያሳዝናል። ባል ተቸግረው የተሰደዱ ይመስላል። ያገኙትን ዜጋ አግብተው ሰርተው አብልተው ባክነው የቀሩት ቁጥር ቀላል አይደለም።

[6] እንደፈራሁትም ሆኖ ሰለሞን የሚባለው ሰው ከዛች ሰውነቱ ላይ ቀንሶ አልቆ ለመሞት ሁለት አመት አልቆየም። አይ ያቺ ልጅ ባህር ከመሻገር አረፈች የተባለችው ምን ዋጣት ይሆን?





ቦሳሶ ላይ ኢትዮጵያዊ ወገኖቼ ከዚህ ባልተለየ መልኩ ነው ያገኘኋቸው። የመንም ገብቼ ሳይ ያው ነው። ቦሳሶ በቋሚ የልመና ተግባር ላይ ተሰማርተው አመት ሁለት አመት ያስቆጠሩ፣ ጋሪ ይዘው ወደብ ላይ የሚራገፍ እቃ አመላልሰው ከቀን ቀለብ ያላለፈ ሳንቲም አግኝተው አቧራ ጠርገው አቧራ ለብሰው የሚተኙ፣ ለሶማሌዎቹ ተላልከው የተራረፈ ምግብ የሚሰጣቸው፣ ገላቸውን ሸጠው የሚያድሩ አጋጥመውኛል። የተሻለ ነገር አግኝተው ቢሆን ጥሩ ነበር። ተሰደው በዚህ ሁኔታ መኖራቸው ወርቅ ጥሎ ወደ ቆርቆሮ መሮጥ መሰለኝ። የእለት ጉርስ ለማይገኝበት ኑሮ መሰደድ።

በማግስቱ ሰናይት ጋር ሄድኩ። ሰንጫወት ካሳሁን የተባለ ልጅ ተዋወቅሁ። ጠቆር ያለ ፀጉሩ ከራሱ ላይ መሸሽ ጀምሯል። ሚስት እንዳለው እና እዛው ንግድ ቤት ከፍተው እንደሚኖሩ ሲነግረኝ ብዙ ማየት እንደሚችል ስለገመትኩ ዛሬ አብረን እንቃም አልኩት። መቃም ባልፈልግም ረጅም ሰዓት የማገኝበት መንገድ ስለሆነ ተጠቀምኩበት። ደስተኛ ሆነ።

«ተባረክ!!» አልኩና መረቅሁት በሆዴ። ምሳ በላን እና ጫታችንን ገዝተን ስሟ ደስ ያለኝ ኢትዮጵያ ሆቴል ሄድን። ውስጥ ቁጭ ብለን መንገደኛውን እንደ ልብ የምናይበት ክፍትፍት ግድግዳ አለው። ከጉጉቴ ብዛት ብዙም ሳልቆይ ጥያቄዎቼን ደረደርኩለት። «እዚህ ያሉ ስደተኞች ላይ መቼም የማይፈጸም ግፍ የለም። እዚህ ስትቆይ ያየኸው..የማትረሳው አሰቃቂ ድርጊት አለ? ለመሆኑ አንተስ እንዴት ወደዚህ መጣህ? ሌሎቹ ሲሻገሩ አንተ ለምንስ እዚህ መቅረት ፈለክ?...» የኢትዮጵያ ሆቴል ባለቤቶች ባልና ሚስት ጉራጌዎች ናቸው። ሴትዮዋን ሙሽሪት ሲሏት ሰምቻለሁ። ቡናውን አጫጨሰችው። በጣባ ተደርጎ አዙረው አሸተቱን ደስ አለኝ እግዚአብሄር ይስጣቸው ለተወሰነ ደቂቃ ሀገሬ ያለሁ እንዲመስለኝ አደረጉኝ። ባህላችንን መጠበቁ ነው መሰለኝ ደስ ያለኝ። ለነገሩ ኢትዮጵያም ሆኜ ከቡና ስነ-ስርዓት ውስጥ አንዱ የሆነው የተቆላውን አዙሮ ማሽተት ደስ ይለኛል። ካሳሁን ጫቱን ካልጎረሰ ትንፍሽ ላለማለት የማለ ይመስል በዝምታ ተሸብቦ ቆየና ቀነጣጥሶ ሲጎርስ ለመናገር ጉሮሮውን ጠራርጎ ቃላቶቹን ለማፈናጠር ምላሱን አቀባበለ።

«የእኔን ተወው ተታልያለሁ። ትንሽም ቢሆን ስራ ነበረኝ። ሰዉ ሁሉ ሳዑዲ...ሳዑዲያ ሲል ብር ዛቅ የሚደረግ ይመስል አጓጓኝ። ደላላው 2000 ካለኝ ሳዑዲ እንደሚያደርሰኝ..ከደረስኩ ደግሞ በወር 2000 የሳዑዲ ሪያል እንደሚከፈለኝ ያ-ማለት በወር 6000 የኢትዮጵያ ብር እንደሆነ ነገረኝ። ህልሜ ሁሉ ሳዑዲ ብቻ ሆነ። በእውኔ ግን አጣሁት እንጂ...» በቁጭት ይሁን በፀፀት በረጅሙ ተነፈሰና ፋታ ወሰደ። ለልብ ስቀላነት የተጠቀመበት ይመስል እንዲህ ወሬው መሀል ያቆምና የእረፍት ጊዜ ለራሱ ይሰጣል። ቀጠለ «ደላላ የመሰለኝ ሰው ደላላ አልነበረም። እሱ ሌላ ስራ ነበረው። ለካ

ቤት የሰራው እንዲሁ አይደለም:: ሌላ አንድ ልጅ ይዞ መንገዱን ስለማያውቅ ብዙም ሳንቸገር በወር ከሳምንት የመን ገባን:: ትዕዝ የሚባለው ከተማ ውስጥ የሚጠብቀው ነገር ነበረው::

«ለሁለት ሳምንት ከሰዎች ጋር እየተደዋወለ ቆየን:: ምንድን ፈልጎ እንደሆነ አልገባንም:: የያዝነው ገንዘብ ለቀለብም ለምንም ስንመነዝረው አለቀ:: እኔ እከፍልና ሰርታችሁ ትከፍሉኛላችሁ ብሎ አፅናናን:: ተባረክ ብዬ ሀሳቤን ጣልኩ:: ከሳምንት በኋላ ጉዞ ጀመርን:: ግን ባዶ እጃችንን አይደለንም:: የሆነ የታሸገ..የታሸገ ነገር ይዟል:: እኔም አብሮኝ ያለውንም ሌላ ልጅ አስይዞናል:: ምን እንደሆነ ለማወቅ ጣርኩ:: የሆነ ግማታም ጭቃ ነገር ነው:: መስታወት ማጣበቂያው የአሜሪካን ጭቃ እያልን የምንጫወትበት አይነት ነው:: የልጅነቴን አስታውሼ እዛ ውድ ቢሆን ይሆናል አልኩና ዝም:: ድንበር ላይ ደረስን:: ምሽትን ተገን አድርገን ገባን:: መቼም ድንበር ለማለፍ ያለውን ችግር አትጠይቀኝ:: በረሃው ላይ ጫማዬ ሁሉ ተገንጥሎ በእግሬ የሄድኩበት ውስጥ እግሬ ተልጧል:: የድንበር ጠባቂዎቹ ደረሱብን ጥረቴ ሁሉ ለማምለጥ ነበር:: በለስ አልቀናኝም:: ተያዝኩኝ:: ልጁም ተያዘ:: ደግነቱ የያዙን ስንያዝ እንዴት እንደሆነ እንጃ እሱ አምልጦ አልተያዘም:: ፖሊሶች ወደ 1 ቦታ ሊወስዱን ሲሉ አንዱ ወደኋላ አስቀረኝና አባቱ እረኛ እንደሚፈልግ ነገረኝ:: አባባሉ አልገባኝም:: አንደኛው አረቢኛ ይችል ስለነበር አስተረጎመልኝ:: በቀን አስር ሪያል ሊከፍሉኝ እንደሚችሉ ነገረኝ:: ከመታሰር በነፃም ቢሆን እንስራ አለኝ አብሮኝ ያለው ልጅ...»

ንግግሩን ገታና ጫቱን ቀንጠስ ቀንጠስ አድርጎ ጎመን ድስት ውስጥ እንደምትሞላ ባልቴት ጭብጥ ሙሉ ጫት ከቶ ጉንጬን ወጠቀው:: ሙሽሪት አለና የሆቴል ተብየዋን ባለቤት ጠርቶ ቡና እንድትሰጠን አዘዛት:: ሮያል የሚል የሲጋራ ፓኮውን አውጥቶ ሁለት መዘረጠና «ያዝ» አለኝ:: ስቅም..ስቅም ሰው እንዳያየኝ ተጠንቅቄ..ተደብቄ አንድ ሁለት ባጨስም እንዲህ አይነት ሲጋራ አለመድኩም:: ልምክረው የሚለው ነገር መቼም ገደል ነው የሚከተኝ ሞከርኩት:: ሁለቴ ከሳብኩት በኋላ ግን አሽቀንጥሬ ጣልኩት:: አቤት ግማቱ!

ሁለት እጅግ የተከፉ፣ ይቺ አለም ድፍት ያለችባቸው የሚመስሉ ልጆች ገቡና ኩርምት ብለው ተቀመጡ:: አይኔ እነሱ ላይ ቀረ::

«ያ ፖሊስ..» ሲል ካሳሁን ትረካውን ቀጠለ:: «...ያ ፖሊስ ወደ አባቱ ቤት ይዞን ሄደ:: ለካ የያዝነውን አይቶ ነበር:: ከተቀበለን በኋላ ከብቶቹ ያሉበት ቦታ አሰረን:: ለምን እንዲህ እንዳደረገ አብሮኝ ያለውን ልጅ ስጠይቀው የያዝኩትን እንዳላወኩት ነገረኝ:: ቀድሞ ቢያየው ኖሮ አብሮኝ እንደማይመጣ ሁሉ ሲነግረኝ ምን እንደሆነ ለማወቅ ጓጓሁ:: ለካ ሀሺሽ ነው:: ደነገጥኩ::





ወር እዛ ቤት ውስጥ ካሰረን በኋላ ከብት ጥበቃውን ለአባቱ መስራት ጀመርን:: እኔና አብሮኝ ያለው ልጅ የምንገናኘው በሁለት ሶስት ቀን ነው:: አብስዬ የምበላው ዱቄት ይሰጠኛል:: በቃ! ህይወት አስጠሊታ ሆነች:: ስቃዩ ምግብ ሰርተህ ብላ የሚባለው ነገር ነው:: አቃተኝ አንድ ቀን በተሰጠኝ ጋዝ ቂጣ ልጋግር ለኩሼ ሳለ አንደኛው ፍየል በርግጎ ይሁን እንጃ ሽምጥ ይጋልብ ጀመር:: እሱን ለማስቆም እኔ ስከተል..እሱ ሲፈረጥጥ የትናየት ካሳደድኩት በኋላ በመጨረሻ ሰውነቴ ዝሎ እንደ ምንም ያዝኩት:: ስመለስ የከብቶቹ በረት ብው ብሎ ነዷል:: ጉዴ ፈላ ምን ላድርግ? ያለኝ አማራጭ መጥፋት ነውና ጠፋሁ:: ብዙም ሳልርቅ ወዲያው ተያዝኩ::..»

ካሳሁን ይሄን ታሪኩን ሲነግረኝ አይኑ ላይ እንባ ተንቆርዝዞ ያየሁ መሰለኝ:: ነገሩ በወገኑ ይህን የመሰለ ደባ ሲፈፀምበት ቢያነባ ምን ሲደንቅ? ቢያዝ እድሜ ልክ እስር ወይም እስከ 20 አመት ሊደርስ የሚችል እስራት ሊፈረድበት እንደሚችል ሲነግረኝ ነው የመከራው ክብደትና የደባው ስፋት የታወቀኝ::

ሁለቱ ጉስቁል ያሉ ልጆች እስካሁን ኩርምት ብለው እንደተቀመጡ ናቸው:: የሆነ ነገር የጎደላቸው... ወይ እርቧቸው ይሆን? አንጀቴን በሉት:: «ገና ሚግባታቸው ይሆን?» ለካሳሁን ያቀረብኩለት ጥያቄ ነበር::

«እኔ ቤት ካረፉ 11 ቀን ሆናቸው ተዘርፈው 'ነው» አለና ምንም ሳይመስለው ወደ ራሱ ወግ ተመለሰ:: ስለ እነሱ ለማወቅ ብጓጓም የተራኪዬን ትረካ ማድመጤን ቀጠልኩ:: «ከዛ በኋላ አባቱ ቤት እረኝነት ያስቀጠረኝ ፖሊስ መያዜን ሰማና መጣ:: ጉዴ ፈላ ብዬ ፈራሁ:: የፈራሁት አልቀረም:: በረታቸው ውስጥ አድሬ ከብቶቹን ፈትቼ በረቱን አቃጥዬ መሰወሬን ተናገረ:: እውነታው ቀጥረውኝ እንደነበረ እና የተፈጠረውን ሁኔታ በምን ቋንቋ ላስረዳ? አስተርጓሚ ተፈልጎ ባስረዳም ማንም ሰሚ አልተገኘም:: ወንጀለኛ ተብዬ ሁለት አመት ተፈረደብኝ:: ከውጭው ግን እስር ቤቱ የተሻለ ነበር እና በሁለት አመት ውስጥ አስራ አምስት ሺህ የሳዑዲ ሪያል አጠራቀምኩ::..»

ጣልቃ ገብቼ በምን አይነት ሁኔታ እንዳጠራቀመው ስጠይቀው «መጣሁ» ብሎ ለሽንት ወጣ:: እኔም ስራ ከምፈታ አይነት ሁለቱን ልጆች ላናግር ፈለኩ:: «ተጫወቱ እንጂ ምነው ዝም አላችሁ? ምን ልዘዝላችሁ?» አልኩና ምላሻቸውን ጠበኩ:: «እኔ ቡና ልጠጣ?» አለና አንደኛው ፍቃድ ጠየቀኝ:: ሁለተኛው መብላት የፈለገ ይመስላል:: «የሚበላም ከፈለጋችሁ ብሉ የሚጠጣም ጠጡ» አልኳቸው:: በደስታ አዘዙ:: ሁለቱም የጎጃም ልጆች ናቸው:: ከሊቢያ ወደ ጣሊያን ሊሻገሩ ሞክረው ታስረው

መመለሳቸውን ነገሩኝ:: ይኸኔ ካሳሁን ተመልሶ ስለመጣ ሌላ ጊዜ ላወራቸው በውስጤ ለራሴ ቀጠሮ ሰጥቼ ትኩረቴን ለካሳሁን ሰጠሁ::

«እ... የሆነ ነገር ልትጠይቀኝ አስበህ ነበር አይደል?» አለኝ::

«አዎን እስር ቤት ውስጥ ሆነህ ምን ብትሰራ ነው ይህን ያህል ገንዘብ ያጠራቀምከው?»

«እስር ቤት ውስጥ ልስራ ካልክ እና ራስህን ዝቅ ካደረክ የሚሰራ ነገር ሞልቷል:: አብረውን የታሰሩ በርካታ ሳዑዲያዊ ነበሩ:: ለእነሱ ልብስ ከማጠብ ጀምሮ የማይሰራ ስራ የለም:: እኔ ሲጋራ እና ውሀ ነበር የምሸጠው:: ሽንት ቤት ማጠብ በተራ ነው:: የእነሱ ተራ ሲሆን አጥብላቸውና ይከፍሉኛል:: ልብሳቸውን አጥባለሁ፣ ጫማቸውን እጠርጋለሁ:: ብቻ ምን አለፋህ የሚሰራውን ሁሉ እሰራለሁ:: 2 አመቴን ጨርሼ ወደ ሀገር ስሳፈር የአይን አሻራ ሳይቀር ተነስቼ ዳግም ብገኝ የሚፈረድብኝ ፍርድ የከፋ እንደሚሆን ተነግሮኛል:: ያኔ የሳዑዲ ሪያል ሲዘረዘር 2 ብር ከምናምን ነበር:: 36000 ዘረዘርኩትና ሀገሬ ገባሁ:: ማለቴ ወሎ ገባሁና በ7 ሺ ብር አነስ ያለች መሬት ገዛሁ:: በ4000 ብር ቆርቆሮ ምን ምን ብዬ ቤት ቢጤ አሰፈርኩበት:: 3000 ደግሞ ለቤተሰብ ሰጠሁ:: ምርቃቴን አፍሼ ወደ አዲስ አበባ ተመለስኩ:: አሁን ባየሁት መንገድ ራሴን ችዬ ለመንዝ አሰብኩ::

መጀመሪያ ፓስፖርት አውጥቼ በህጋዊ መንገድ ወደ የመን ለመሄድ የያዝኩት ብር ይበቃኛል ብዬ ነበር:: የቀለጠው መንደር ውስጥ ሳላውቅ ገባሁ:: ፓስፖርት አወጣለሁ ብዬ ሳለሁ 1 ቀን ትንሽ መጠጥ መቀማመስ አማረኝ:: ስካር ነው በማልለው ሁኔታ ገና ስገባ ነው ልታስተናግደኝ የመጣችው ልጅ የማረከችኝ:: አየኋት..አየችኝ:: እሷ ለቢዝነሷ እኔ ለስሜቴ ተሳስበን ተያየን:: ቁጭ በይ ስላት ብሬን አፈር ድሜ እንደማበላው ተሳስበን ተያየን:: ቁጭ በይ ስላት ብሬን አፈር ድሜ እንደማበላው አላሰብኩም:: ተቀመጠች እኔ ግን በሰዓቱ ደስተኛ ነበርኩ:: ብሩ እንድ ተብሎ መመዘዝ ተጀመረ:: ምን አለፋህ ያን ማታ ጀመርኩና አብሬያት መቅበጡን ተያያዝኩት:: እሷም አቀባበጠችኝ:: አቀባበጥኳት በወር ከእስር ቀኔ ብሬ ሳስታ፣ ኪሴ ከስታ መጎረባበጥ ስትጀምር ዳግም በባህር ለመምጣት አማራጩ ግድ ሆነ::

ይህች ልጅ ይህን ያህል ጊዜ አብራኝ ነበረች:: መላመድ ፍቅር ነው:: ተግባባን የቡና ቤቱም ህይወት ሰልችቷት ነበር:: አብራኝ መጣች አሁንም አብራኝ ነው ያለችው:: አሁን ብር ፈልጋ ሳይሆን ያላትን ብር ይዛ ፍቅር ፈልጋ ነው የተሰደደችው:: መንገድ ላይ ከእኔ ጋር ያየችው መከራ የዋዛ እንዳይመስልህ:: ደብረዘይት፣ ናዝሬት፣ ሞጆ ድሬደዋ እያልን ስናቆራርጥ በየከተማው ስንደሰት፣ ስናድር፣ ስንጠጣ ጅጅጋ ደረስን:: ጅጅጋ ላይ በደላሎች ስንዋከብ ነገር አለሙ ጠፋ:: አዝማሚያቸው አላምር ሲለን ገንዘቡን እሷ እርቃ ደበቀችው:: መቼም የሴት ማራቂያ የት እንደሆነ አስብ::





ቡርአን ሁሉ በሰላም አለፍን:: የኢትዮጵያ 250 ብር ከፍለን በካርቶን የታሸገ እቃ በጫነ መኪና ላይ ነው የተጫነው:: ዋናውን መንገድ ትቶ በኮንትሮባንድ መንገድ ጉዞውን ተያያዘው:: ከ2 ቀን ጉዞ በኋላ የቦታው ስም ምን እንደሚባል አላውቅም እቆመና ውረዱ አሉን:: ቤተሰቦቹ ናቸው መሰለኝ እዛ አካባቢ ያሉ ሰዎች ከበቡን:: እኔና እሱ ከወንዶቹ ጋር የሆነ ክፍል ገባን:: እሷ ከሴቶቹ ጋር አንድ ላይ ገባች:: በምን ቋንቋ እንግባባ? ምንም አልተግባባንም:: የሚነግሩኝ ነገር ግን ማስጠንቀቂያና ማስፈራሪያነት እንዳለው ገብቶኛል:: ከዛ የሚበላ ነገር የመወርወር ያህል ተጣለልኝ:: ከረዥም ቆይታ በኋላ ከየት እንዳመጡት አላውቅም በዱላ የሚሄድ አማርኛ ትንሽ የሚችል ኢትዮጵያዊ ልጅ ይዘው መጡ:: የእሱ የመናገር ችሎታ ማነስ ለእኔ የነገሩትን ማባረሪያ ቃል ለመተርጎም አላቃተውም:: የሆሳዕና ልጅ ነው::

«አይኑ እንዳናይ በሂዎት ከዚች ሂድ አሉ ጊዜ..»

«እረ! እነሱ ናቸው ያመጡኝ ሚስቴ እዛ ነው ያለችው ጥራልኝና ሄዳለሁ» ምን እንዳሰቡ ግራ ገባኝ:: ልምጣ አላልኳቸው ወይ አሳርፉኝ አላልኩ ምን አስበው ነው? ለመሳፈሪያ የከፈልኩትን ለመክልከል ፈልገው መሰለኝ:: በሰላም ይልቀቁኝ እና እሄዳለሁ::

«ኢንጀ! ሚስጡ አልመሰለም:: ነፒሱ ለማትረፕ አንተ ሂድ..ነገሩ ነሱ በጭካን ይሰራሉ::..» እሱ ያደረገው ይመስል በእሱም ተናደድኩ::

«እህ!..ሚስቴን ይስጡኝ..ይስጡኝ እሄዳለሁ:: ያለበለዚያ እንዴት ነው ጥያት የምሄደው?» በዚህ ሀሳብ ልስማማ አልቻልኩም:: አሁን ዱላ መጣ:: እስኪበቃኝ ቀጠቀጡኝ:: እንደዛም ሆኜ ጥያት አልሄድም አልኩኝ:: ግብግብ ተያያዝን::

በዚህን ጊዜ በጥይት 2 ቦታ ተመታሁ:: ሚስቴ «እሪ....›› ብላ በጩኸት አካባቢውን ቀወጠችው:: እግሬ ላይ እና እዚህ ክንዴ ላይ ነው የመቱኝ:: መልሰው ሚስቴን ወሰዷት እኔን ያ-ልጅ አስታመመኝ:: ለካ ልጁ በዱላ የሚሄደው ደብድበውት ሚስቱንም ወስደውበት ነው:: ይዞን ወደዛ የሄደው ሹፌር ሁሌም ሚስቴን ይሄት ያድራል:: በኒካ አገባኋት አለኝ:: ሲሻለኝ እዛ አካባቢ በዱላ የምንሄድ ሁለት ኢትዮጵያዊ ሆንን:: 2 ወር ከ10 ቀን እያየኋት እንዳንነጋገር አደረጉኝ:: እያየሁ ይሄት ያድራል:: በራሴ.. ሚስት የበይ ተመልካች ሆንኩ:: በዚህን ጊዜ ሲርበኝ እንድሄድ ብለው ምግብ ከልክለውኝ ነበር:: ረሀብ ሊገለኝ ሆነ:: ለውሻው የሰጡትን ትርፍራፊ ውሻውን በያዝኩት ምርኩዝ አባርሬ በላሁበት:: ከውሻ አንሼ ከውሻ ነጠኩ:: በደንብ ሲሻለኝ እንድንጠፋ አቀድኩ:: አደረግነውም:: ምንም ያህል ሳንርቅ

ያዙን ዳግም ተደበደብኩ፡፡ የፊት ጥርሴ ወለቀ፡፡ (በጥይት የተመታውንም ሆነ ያወለቁት ጥርሱን አሳየኝ፡፡) ከአካባቢው ጥፋ አሉኝ፡፡

ከዚህ በኋላ ምን ተስፋ አለኝ? እዛ መሆን ሞቴን ማፋጠን ሆነብኝ፡፡ መንገዴን ጀመርኩ፡፡ ብዙም ሳልርቅ የሚበላ በምልክት ስለምን ስራ እንቅጠርህ አሉኝ፡፡ ሚስቴን መነጠቄን ሳልናገር የሆዴን በሆዴ አድርጌ ተቀጠርኩ፡፡ ለነገሩ ልናገርስ ብል በምን አንደበት? ቋንቋቸውን አላውቅ ተቀጠርኩ፡፡ ለነገሩ ልናገርስ ብል በምን አንደበት? ቋንቋቸውን አላውቅ

ቋንቋዬን አያውቁ፡፡ የማውቃት እንግሊዘኛ የስ..ኖ..ማዘር..ፋዘርን ነው፡፡ ይሄ ቋንቋዬን አያውቁ፡፡ የማውቃት እንግሊዘኛ የስ..ኖ..ማዘር..ፋዘርን ነው፡፡ ይሄ

እያግባባ በምን እንግባባ? ለ3 ወር ሚስቴን በአቅም ማነስ ለእሱ ሚስት እያግባባ በምን እንግባባ? ለ3 ወር ሚስቴን በአቅም ማነስ ለእሱ ሚስት

እድርጌ፤ አካሌን አጉድዬ.. እያነከስኩ ሶማሌዎቹ ምግብ ቤት ስራዬን ቀጠልኩ፡፡ እነሱ ግን እዛ አካባቢ መሆኔን አልወደዱትም፡፡ ለሚስቴ ግን በሚያነክሰው ልጅ ወረቀት ጽፌ ላኩላት፡፡ ሌሊት ለሽንት አስመስላ እንድትወጣና እንድንጠፋ ጻፍኩላት፡፡ ሌሊት አመቺ ጊዜ ጠበኩና ይዣት ጠፋሁ፡፡ በየት በየት ብለን እንደመጣን አትጠይቀኝ፡፡ ስቃያችን አይተን በ22 ቀን ቦሳሶ ገባን፡፡

እዚህ ስንደርስ ገንዘብ የሚባል ነገር የለንም፡፡ ሀገሩን በደንብ አላውቅም፡፡ የሶስት ወር እርጉዝ ናት፡፡ እሷ እኔን ብላ መጥታ ይህን ሁሉ መከራ እይታ እንድትከፋብኝም ሆነ እንድትጎዳብኝ አልፈለኩም፡፡ በዛ ላይ ከልብ ወድጃታለሁ፡፡ ግን አይኔ እያየ ሚስቴን ያሰቃየ ሰው ልጅ...አካሌን ያጎደለውን ሰው ልጅ...በጥይት ያስመታኝን አረመኔ ሰው ልጅ..እንደሆነ በሆዷ የያዘችው ሳስብ ስቅጥጥ ይለኛል፡፡ ግራ ገባኝ፡፡

ቀይ መስቀልም ተደፍራ እንደሆነ ያረገዘችው ነግራቸው ጽንሱን እንዲያስወርዱላት ብትለምናቸው እርዳታ ሊያደርጉላት፣ ሊረዷት አልፈለጉም፡፡ በሌላ ነገር ሊረዷት እንደሚችሉ ብቻ ነገሯት፡፡ ምን ላድርጋት የእዛ አረመኔ ፍሬ መሆኑን ውስጤ ቢጠላውም ለእሷ ስል ለማሳደግ ግድ አለኝ፡፡ ይሄ ጉዳይ ግን ፈጽሞ ረፍት ሊሰጠኝ አልቻለም፡፡ አንዳንዶች የሰው ዲቃላ እንዴት ታሳድጋለህ ጥለሀት ወደ የመን ተሻገር..ወደ እሱ መልሳት እና ወልዳ ጥላለት ትውጣ..የመሳሰለ አስቀያሚ አስተያየት ይሰጡኛል፡፡ እንዴትስ እሺ ብዬ ልቀበል ፍቅሬን በስንት ስቃይ እንዳስጠፋኋት ለእሷ ብዬ አካሌን እንዳጣሁላት በጥይት እንደተመታሁላት መች ተረዱኝ? ልመልሳት፣ ወይም ጥያት ወደ የመን ለመሻገር የምፈልግ ከሆነማ ሂድ ሲሉኝ ጥያት መንገዴን ብቀጥል መች ሁለቴ በጥይት እመታ ነበር? መቼ ይሆን ሰው በርሃብ ተጠብሼ ለውሻ የተሰጠ ምግብ ቀምቼ እበላ ነበር?..መቼ ይሆን ሰው የሰው ቁስል የሚገባው?..በኋላ እዛ ያሉ ልጆች አዋጥተው መድኃኒት ገዝተው እንድትውጠው ነገሯት፡፡ ወሰደችውም፡፡

በስመአብ ላትሞት በስንት ጣር በቀይ መስቀሎች እርዳታ ተረፈች፡፡ ንግግሩን አቋርጦ ትክዝ አለ፡፡ ለምን አይተክዝ? ለምን አያነባ?..እኔ





ለሰማሁትም ሰቅጥጦኛል፡፡ አስተክዞኛል፡፡ ለፍቅር የከፈለው መስዋዕትነት ደስ አለኝ፡፡

«ስደትና ፍቅር» ስል አሰብኩ፡፡ አሁን ወዴትም መሄድ አይችልም፡፡ ሳንቲም በመጠኑም ቢሆን አግኝቶ ነው ምግብ ቤቷን የከፈተው፡፡ እሷ በደረሰባት ጉዳት ከዚህ በኋላ መውለድ አትችልም መባላቸውን ነግሮኛል፡፡ እንዴት ይከብዳል? እሱ ግን ጥሩ ሰው ነው ሊርቃት አይፈልግም፡፡ ለምን እንደሆነ ባይነግረኝም ወደ የመንም ሆነ ሳውዲ አረቢያ ለመሻገር የነበረውን ሀሳብ ቀይሯል፡፡ መኖር የሚፈልገው ሶማሊያ ውስጥ ነው፡፡ ምክንያቱን ጠይቄው ነበር፡፡ በመሀል ሁለት ሆነው ከገቡት ልጆች አንደኛው እያንቀላፋ ነበር እና የጨዋታ ርዕሳችን ወደ እሱ ተለወጠ፡፡ ከዚህ ቦታ መራቅ እንዳለብኝ ተሰማኝ፡፡ የሚመጡት ሁሉ የሚያወሩት ሰላም የማይሰጥ ነው፡፡ ቆሳስለው ደማምተው እያየሁ ስሜቴ ተጎድቶ የራሴን መከራ ባልቻልኩበት ሰዓት ውስጤ በሀዘን እንዳይናወጥ ሰጋሁ፡፡ ለነገሩ ከዚህ በላይ..ከዚህ በከፋ ሁኔታ ውስጤ በሀዘን ይናወጥ ይሆን? ምን ቀረኝ ሁሉን አየሁ፡፡ ቦሳሶ ብዙ ጊዜ እንደሚቆዩት ሰዎች ብዙ ብቆይ ጨርቄን የምጥል ሁላ መሰለኝ፡፡ በሶማሊያዋ ቦሳሶ ከተማ ኢትዮጵያዊ እንደ ሰው ሲቆጠር አላየሁም፡፡ ለነገሩ ሶማሊያ ያለውን ሁኔታ አልኩ እንጂ የመንም ቢሆን ጉልህ ጥላቻ አላቸው፡፡ በተለይ ሀረድ የሚባለው አካባቢ...

የወገኔን ስቃይ ወደድኩም ጠላሁም ከማየት ወደኋላ አላልኩም፡፡ አሁንም እያየሁ ነው፡፡ የጊዜ ሂደቱ እንደቀጠለ ነው፡፡ እኔም የወገኔን መከራ ማየቴ እንዲሁ በግዴታ ቀጥሏል፡፡ ያማል..በጣም ያማል በሽታ ነው የሚሆነው፡፡ ዝርዝር የሶማሊያ መከራን መግለጽ ይከብዳል፡፡ .እኔ ራሴ ገላዬን ልታጠብ መታጠቢያ ቤት ሄጄ የገጠመኝ ሶማሊያ የሚለው ቃል በተነሳ ወቅት ብቅ ይልና ያበሳጨኛል፡፡ የምቀይረው ልብስ ይዤ የሶማሊያ 3000 ሽልንግ ተከፍሎ የምንታጠብበት ቦታ ገባሁ፡፡ በኢትዮጵያ ብር የያዝኩትን ፈርቼ የጫማዬን ገበር ገንጥዬ ከተትኩ እና ሻንጣዬ ውስጥ አደረኩት፡፡ ያን ያደረኩት ሲዘርፉ ስላየሁ እንዳይዘርፉኝ ፈርቼ ነው፡፡ ገና ወደዛ ስሄድ ገንዘቤን አዲስ የምቀይረው ልብስ ውስጥ ከትቼ ነበር፡፡ ምክንያቱም የቆሸሸውን ልብስ በዛው አጥቤ ለመመለስ አስቤ ነው፡፡

እነሱ ግን ለብሼው የነበረው ውስጥ መስሏቸው የመታጠቢያ ቤቱን በር በርግደው ገብተው ያወለኩትን ልብስ ሊወስዱ ታገሉኝ፡፡ አንደኛው ግን የተቃጠለ ዘይት ከአናቴ ጀምሮ ደፋብኝ፡፡ አይኔን ተቃጠልኩ፡፡ ይባስ ብለው ክብሪት ጭረው የሚለኩሱኝ እያስመሰሉ ማስፈራራት ያዙ፡፡ የእውነት ሊያደርጉትም እንደሚችሉ ስላሰብኩ ፈርቼ ነበር፡፡ ድጋሚ ገብቼ ታጥቤ ስወጣ ሌላ የተቃጠለ ጋዝ ከነቀየርኩት ልብስ አጥለቀለቁኝ፡፡ ምን ማድረግ እችላለሁ? ድጋሚ ከፈልኩና ልታጠብ ገባሁ፡፡ ልብሴንም አጠብኩ፡፡ ልብሴ

እስኪደርቅ ጸሀይ ላይ ስቀመጥ ሌሎች ይሁኑ እነሱ የላኳቸው መጥተው ስለት አወጡብኝና ፈተሹኝ:: ብር የተላከላቸውን ልጆች እያስገደዱ ሲዘርፉ ስላየሁ ነበር ብሬን መደበቁ:: ባልደብቀው ኖሮ በዜሮ ያስቀሩኝ ነበር:: በስለቱ ክንዴ ላይ ጫር አድርገውኝ 120 ሺህ የሶማሊያ ሽልንግ ወሰዱብኝ:: ይህ ማለት 65 የኢትዮጵያ ብር አካባቢ ነው:: ብሩ ባይጎዳኝም ጥቃቱ ግን በጣም አንገበገበኝ::

በሳሶ በቆየሁበት 5 ቀን ውስጥ የአካል ጉዳተኞች፣ ህፃናት..ነፍሰ-ጡር ሴቶች፣ በቅርቡ የወለዱ ሁለት አራሶች አይቻለሁ:: በሳሶ ውስጥ የገጠሙኝ ስደተኛው አቦይ ብርሃነ የሚሏቸው ናቸው:: በስደት 40 አመት አሳልፈዋል:: የኖሩበትንና ያዩትን ሀገር ሲናገሩ አፍ ያስከፍታሉ:: 17 አይነት ቋንቋ ያውቃሉ:: ህንድ አገር ረጅም ጊዜ ኖረዋል:: ከህንድ ብቻ 5 አይነት ቋንቋ ያውቃሉ:: የአድግራት አካባቢ ነዋሪ ቢሆኑም አማርኛ አያውቁም::

ብዙ..ብዙ ሰቆቃ ያየሁበት በሳሶን ለቅቄ ልወጣ ነው:: ለጀልባ መሳፈሪያ ክፈል የተባልኩትን የኢትዮጵያ ሶስት መቶ ብር ከፈልኩ:: ከከተማ ወጥቶ የሚገኘው መሳፈሪያ ቦታ ሊወስዱን የጭነት መኪና አቀረቡ:: ሰናይት የሚጎልሽን ብር እሞላልሻለሁ እንጂ እዚህ ይህንን ሕይወት ብለሽ አትቆይም ብያት ተዘጋጅታለች:: አጋጣሚ ጓደኛዋ ከሳውዲ አረቢያ ገንዘብ ተላከላትና እኔም ሳልሞላላቸው ለጉዞ ተዘጋጁ:: ቅዳሜ ጠዋት ለጉዞ የሚሆነንን ብስኩት ገዛን፣ ውሀ እየገዛን ቢጫ ሀያት በሚለው ባለ 4 ሊትር የዘይት ጀሪካን ሞላን:: ሁሉ ዝግጅት አለቀ:: የጭነት መኪናው ላይ ወጣን:: የከተማው መውጫ ላይ ያለ አንድ ግቢ ነገር ውስጥ እየወሰዱ አጎሩን:: ምን ሊያረጉን ይሆ፣. ከተማ ውስጥ ያላየኋቸው ሁሉ እዚህ ጊቢ ውስጥ አሉ:: ሁለት እግሩ የማይታዘዘው ታዝሎ የሚንቀሳቀስ ልጅ አየሁ:: ተጠጋኋቸው::

«ሰላም ናች ኍ? እዚህች ጋር ልቀመጥ?»

«ወረ መጋላ ታኢ!» ተቀመጥኩ:: አማርኛ የማያውቅ ከሆነ በዚህ ሁኔታ እያለ ለምን ሀገሩን ጥሎ እንደሚሄድ ለማወቅ የፈለኩት ላይሳካ ነው? በውስጤ ያሰላሰልኩት የግል ሀሳቤ ነው::

«አማርኛ አትችልም?»

«እችላለሁ ምን ፈለክ?» ጥርት ባለ አማርኛ

«ምንም እንዲሁ ለሎጨዋወተ ያህል ነው:: አማርኛ ካልቻልክ አንግባባም ብዬ ነው:: የአዲስ አበባ ልጅ ነኝ አንተስ?»

«ናዝሬት ነኝ መናኸሪያ አካባቢ ነው መኖሪያ ም መስሪያዬም»



«መስሪያዬም ነው ያልከው? ምን ትሰራ ነበር?»

«ልብስ ሰፊ ነበርኩ..» ገረመኝ:: ሁለት እግሩ ከመታመሙ ጋር እንዴት እንደሚሰፋ ጠይቄው በሰጠኝ መልስ ይበልጥ ተገረምኩ:: በእግር የሚረገጠውን ብረት በሁለት ገመድ አስሮ..ቁጭት ተሰማኝ:: ምነው በጋዜጠኝነት ስራዬ ላይ..እያለሁ ባገኘሁት አልኩ:: ስንት ሙሉ አካል እያላቸው ለልመና ቅርብ የሆኑ ሰዎችን ጥሩ ማስተማሪያ በሆነኝ ነበር::

«ለምን መጣህ እዛ መስራቱ አይሻልም ነበር?» አየኝ:: አስተያየቱ የጤና አልነበረም:: ብዙ ከተጨቃጨቅን በኋላ ነው አሳምኜው በሰላም ያወራነው:: ተነስ ሂድልኝ ብሎኝ ሁሉ ነበር:: ለማወቅ ስለፈለኩ ጥንካሬው ስላስደሰተኝ ተለማመጥኩት::

«እዚህ ለመስራት የሚያግደኝ ነገር አለ? የትም ቢሆን እሰራለሁ:: እሰራለሁ ካልኩ የሚያግደኝ የለም:: ናዝሬት ነኝ ያልኩህ የመጨረሻ መነሻዬን ነው..በትክክል ትውልዴ ወለጋ ነው:: በአንድ የተረገመ ቀን ምክንያቱ ሳይታወቅ የ11ኛ ክፍል ተማሪ ሆኜ ከዛሬ ሰባት ዓመት በፊት ነው እንዲህ የሆንኩት:: በሰላም ተኝቼ ስነሳ በአንድ ሌሊት እንዲህ ሆንኩ:: እግሮቼ አልታዘዝ አሉኝ:: ያኔ ግማሽ ቀን ልብስ ስፌት እየሰራሁ እማራለሁ:: የሁሉ ከንፈር መምጠጥ ከቤት እንዳልወጣ አደረገኝ:: የሚያውቀኝ ሰው በሙሉ ሲያየኝ ምን እንዲህ አደረገህ በሚለው ጀምሮ የማይጠይቀኝ ጥያቄ የለም:: በመጨረሻም ያቺኑ የሰው ስሜት የምታከላሽ ከንፈር መጠጣቸውን ይቸሩኛል:: «ምዕ!!..» ባሉኝ ቁጥር ልቤ ሲደማ ውሉ ሲደማ ያድራል::

«ከንፈር መጠጣ አዘኔታ አይደለም:: ደም መጠጣ ነው::..» ልቤ ልክ መሆኑን ደጋግሞ አስመረበት:: ንግግሩን ቀጠለ «...መስራት እየቻልኩ ሠውን ሽሽት ቤት በመዋሌ ተጧሪ ሆንኩ:: ትምህርቴም ቀረ:: ከዛ መረረኝ፣ የሰው እጅ አይቶ መኖሩ አስጠላኝ ጠፋሁ እና ሆለታ ገባሁ:: ግን ሆለታስ ቢሆን ማን ትሰራለህ ብሎ አምኖ ያስራኝ? ሁሉም ሊረዱኝ እንጂ ሊያስሩኝ አልደፈሩም:: ከዓመት በኋላ አማራጭ በማጣቴ ወደ አዲስ አበባ አቀናሁ:: አውቶቡስ ተራ ለትንሽ ጊዜ በልመና ተሰማራሁና የስፌት መኪና ገዝቼ መርካቶ ሸራ ተራ መስፋት ጀመርኩ:: ለብዙ ጊዜ ሰራሁ ከአራት አመት በኋላ ነገሮች ተበላሹብኝ ወደ ናዝሬት ሄድኩ...» ተስፋ ያስቆረጠው ነገር እንዳለ ገባኝ::

«መርካቶ ጥሩ ትሰራ ከነበረ ለምን ወደ ናዝሬት መሄዱን ፈለክ? የተበላሸብህ ነገር...» አላስጨረሰኝም:: ቶሎ ይቆጣል::

«ይኸውልህ የተሻለ ለመስራት የራሴን ሱቅ ለመክፈት እሰብኩና እቁብ ገባሁ:: መሀል ላይ አንድ ባለሱቅ ቁልፉን ሊሸጥ ሲል ልገዛው ተነጋገርን::

እቁቡን እንዲሰጡኝ ጠየኩ:: አሳሳፊሩኝም ሰጡኝ:: ሰውየው ቁልፉን የሚሸጥበት ብር እና እኔ የያዝኩት ብር ስላልተቀራረበ ለጊዜው ተቀብሎኝ እየሰራሁ ቀሪውን ልሰጥ ስደራደር እንደዚህ ልጅ እያዘለ የሚያንቀሳቅሰኝ እየሰራሁ መክፈሉን ተያያዝኩት:: ብለው ልጅ 12000 ብሩን ሰርቆኝ ጠፋ:: እየሰራሁ መክፈሉን ተያያዝኩት:: ብለው ..ብለው አላልቅ አለኝ:: ስለቾኝ የተሰረኩትን ብር እንደሆነ የምከፍለው ሳስብ ደግሞ ኑሮ ሁሉ ይመረኝ ጀመር:: በዚህን ጊዜ ጥዬ ጠፋሁ:: ናዝሬት እንደጠበኩት ባይሆንም ተቀጥሬ መስራት ጀመርኩ:: የሚያስጠላኝ ነገር ግን መከሰቱ አልቀረም:: ሁሉም ከንፈር ይመጡና በሀዘኔታ እንደሚያሰሩኝ ይነግሩኛል:: ተስፋዬ በመለምለም ፋንታ ጠወለገ:: የተረጂነት ስሜት ከውስጤ አልወጣም አለ:: ለምን ከንፈር ይመጡልኛል? ለምን የመስፋት ችሎታዬን እያደንቁልኝም? ውስጤ ተጎዳ..» የልጁ ታሪክ ደስ የሚል ጥንካሬ የታከለበትና አሳዛኝነት ያለው ቢሆንም እንቅልፍ እያንጎላጀጀኝ ነው የሰማሁት:: አቃተኝ ሙቀቱም አይጣል ነው:: ድንጋይ ተንተርሼ ለምን ያህል ጊዜ እንደተኛሁ ሳላውቀው ራስና አንገቴን ሲያመኝ ነቃሁ::

### ***ቅዳሜ 6 ሰዓት፦***

ከብዙ ቆይታ በኋላ መኪና መጣና ከግማሽ መንገድ በለጥ ያለውን እንደወሰዱን ውረዱ አሉን:: ቀሪውን በእግር ተጓዙ ተባልን:: አስቸጋሪና ወጣ ገባውን መንገድ ነው እየተጓዝን ያለነው:: ነጭ ላብ ከፊት ክጀርባዬ ይንዠቀዠቃል:: ወደ አንድ ሰዓት እንደተጓዝን አንድ ጋራ ስር በርካታ ጥቁርቁር..ጉስቁልቁል ያሉ ሰዎች አገኘን:: ጠጋ ብለን እንዳናናግራቸው ዱላ የያዙ ጠባቂዎቻቸው ከለከሉን:: በርቀት ግን ከቡርአ በቀጥታ እንደመጡ እዚሁ ጋራ ስር 4 ቀን እንደቆዩ፣ ኤልያስ የሚባለው አንዱ ደላላ ኢትዮጵያዊ መሆኑን ነገሩኝ:: ምን ማድረግ እችላለሁ? ለገንዘብ ሲል ከሶማሊያዊያኑ ጋር አብሮ ወገኖቹን አግቶ ማየት እንዴት ያናድዳል? እእነሱን እንዳለፍን እግሩን የሚያመው ልጅ አንድ ድንጋይ ላይ ተቀምጦ አገኘነው:: አዝሎት የነበረው ልጅ ደክሞት ለእረፍት ነበር ያወረደው:: እሱ ሰናይት..ጓደኛዋ..እኔና ጅብሪል ትናንሽ ሻንጣዎች ይዘን ደክሞናል:: እሱ ሰውን ያህል ነገር ተሸክሞ ቀድሞን እዚህ መድረሱ ገረመኝ:: እኛ ስንጠባበቅ ጉዞ ጀምሮ መሆን አለበት ስል አሰብኩና ተጠጋኋቸው::

«ትንሽ ላግዝህ?» ሻንጣዬን ለጅብሪል ሠጠሁትና ልጀግን ብዬ እንደ ጉልበታም ልጁን አዘልኩት:: የአምስት ደቂቃ መንገድ ሳልሄድ ሰውነቴ ተብረከረከ፣ እግሬ ተንቀጠቀጠ፣ ..ልጥለው ደረስኩ፤ አስቀመጥኩት:: «አመሰግናለሁ!» ንግግሩ ትህትና በተላበሰ ሁኔታ ነው:: ጅብሪል ቢቀጥንም ከእኔ የተሻለ ነው:: ከመቶ ሜትር የበለጠ ወሰደው:: እየተጠባበቅን ተጉዘን ለአይን ያዝ ሲያደርግ ጀልባዎቹ የቆሙበት ቦታ ደረስን:: ሁሉም ስለደከመው በየቦታው ተዘረረ:: እኔም ተዝለፍልፌያለሁ ተዘረረኩ::





ከቦሳሶ ከተማ ወጥቶ ያለው በህገ-ወጥ መንገድ
በጀልባ የሚጫንበት ቦታ ያለው ሁኔታ ይህን ይመስላል:: (ፎቶ ከኢንተርኔት የተወሰደ)

ምን ያህል እንዳረፍን አላስታውስም:: እነሰናይት በሶ አበስብሰው ሸለብ ካደረገኝ እንቅልፍ ቀሰቀሱኝ:: ደስ ባይለኝም ቅር እንዳይላቸው ስል በላሁ:: ከምሽቱ 2 ሰዓት ካለፈ በኋላ ሶማሊያዊያኑ የጀልባው ዘዋሪዎች መጡ:: አቤት! የሰዓቱ አፈጣጠን? ሶማሊያ ውስጥ ስላለሁ እሱም እንደነሱ እየተንቀለቀለ ያለፈኝ እንጂ እውነት ያን ያህል አርፌ አልመሰለኝም:: ተሰለፉ ሲባል ሁሉም ወደ ኋላ ይላሉ:: እኔ ግን ከፊት ተሰልፌ ቀድሜ ገብቼ ጥሩ ቦታ መምረጥና መቀመጥ አሰብኩ:: በይሉኝታ የበላሁት በሶ ሰላም አልሰጥ ብሎ ይጓጉጠኛል:: በጀልባው ቁጥር ሲሸነሽኑን፣ የከፈለና ያልከፈለ እያሉ ልክ እንደጉልት ዕቃ ሲመድቡን ቆዩ::

### ቅዳሜ ከምሽቱ 4 ሰዓት አካባቢ

ጀልባው ላይ መውጣት ተጀመረ:: የባህሩ ውሀ ሲነካን ሽታው ያስጠላል ብለው ሽቶ ሲቀቡ ልጆች በግድ ቀብተውኝ ነበር:: የከፋ ሽታ እንደማይገጥመኝ ገመትኩ:: የያዝኳትን የጀርባ ቦርሳ ውሀ እንዳይነካብኝ ስጨነቅ ሶማሊያዊው የጀልባ ዘዋሪ እየጮኸ ተንደርድሮ በቦክስ መንጋጋዬን



ከቦሳሶ ከተማ ወጣ ብሎ ያለው በህገ-ወጥ መንገድ
በጀልባ የሚጫንበት ቦታ ያለው ሁኔታ ይህን ይመስላል። (ፎቶ ከኢንተርኔት የተወሰደ)

እዞረው:: ወፌ ቆመች..ወፌ ቆመች..ተብሎ ተንገዳግዶ እንደሚወድቅ ህጻን ተንገዳግጄ ድፍት አልኩ:: የባህሩን ውሀ ትንሽ ተጎነጨሁ:: እልህ ተናነቀኝ:: ተነስቼ ልመታው ፈለኩ:: በኋላ ባህር ላይ እንዳይተናኮሉኝ ፈራሁ::

ስደት ወንድ ሆኖ ወንድ የማያደርግ እንደሆነ ተሰማኝና ውስጤን የሚንጥ እልህ ተጫረብኝ:: የፈለኩትን አለመፈጸሜ ስሜቴን አኮላሸው:: ሻንጣዬን ከራሴ በላይ ተሸክሜ በአንድ እጄ ገመዱን ይዤ ወደ ጀልባው ጉዞ ጀመርኩ:: ቁመቴ 1.74 ሜትር ቢሆንም ውሀው አፌ ሊገባ ትንሽ ቀረው:: ከእኔ ወደ ጀልባው ስቀርብ ዋና በትንሹ ባልችል ውሀ ለጉድ እጠጣ ነበር:: የግድ ያን ግም ውሀ አጠር የሚሉት እንዴት ሆነው እንዳለፉት ግራ ገባኝ፤ ተጎንጭተው እንደሚሆን አመንኩ:: እንደምንም ጀልባው ላይ ወጣሁ::

ጀልባው ላይ የነበረው ሶማሌ አንደርድሮ እየገፈታተረ የሆነ ጉድጓድ ውስጥ ከተተኝ:: ቀጥሎም ወደ ውስጥ ሞተሩ ጋ ግባ አለኝ:: ለካ ይህን ሽሽት ነበር ሁሉም ወደኋላ ያፈገፈጉት:: በዱላው መታኝና ወደ ውስጥ አስገባኝ:: የናፍጣው ሽታ አፈነኝ:: ሳይስማማኝ ቀርቶ ከነበረው በሶ ጋር ተባበሩብኝ:: የተቀባሁትም ሽቶ የባህሩ ውሀ ሲነካው ጥንብ..ጥንብ አለ:: መቋቋም አልቻልኩም አጥወለወለኝ:: የያዝኩት ላይተር ላይ ያለችውን ባትሪ አበራሁና «ፈቅ..ፈቅ..» የሚለውን ሞተር ሁኔታ አየሁት:: ያለው ክፍተት ወደኋላ ሊያሾልከኝ የሚችል መሆኑን አጤንኩ:: ዞር ማለታቸውን በያዙት የእጅ ባትሪ ብርሃን አረጋገጥኩና ሾለኩኝ::

ከሲኦል ወደ ገነት ሾልኬ የመግባት ያህል ነው ያስደሰተኝ:: ወደላይ ወጣሁና ዘዋሪዎቹ/በሶማሊኛ ናኩዳ ነው የሚባሉት/ ያስቀመጧቸው ሴቶችና ሶማሌዎች ጋር ተቀመጥኩ:: በእርግጫ ጀርባዬን ደልቆ «ወደኋላህ ተጠጋ» አለኝ:: ውስጤ ያቅለሸለሸኝ ነገር ተፈትልኮ ሊወጣ ነበር ሲደልቀኝ:: ዞር ስል በጎኔ ግርግዳውን ነው የተደገፍኩት ከዛ እልፌ ወዴት ልሂድ? የመማታት ሱስ አለባቸው:: ነገሮች ሁሉ ምርር አሉኝ:: መለስ ብሎ «እግርህን ሰብስብ» መሰለኝ ያለው አምባርቆ ቁርጭምጭሚቴን ቆጋኝ:: አሁን መናገርም ምንም ሳይሆን እንባ ነው የቀደመኝ:: እኔን ብቻ ጠምዶ የያዘኝ መሰለኝ:: ግን ሁሉንም ነበር የሚማታው:: በሰው ስቃይ የመደሰት መጥፎ ሱስ የተጠናወታቸው ናቸው:: አንዳችንን በአንዳችን ላይ ጠቅጥቀው/ደራርበው/ ጫኑን:: እነሰናይት አልፈውኝ ሊሄዱ ሲሉ ጠርቻቸው አጠገቤ ተቀመጡ::

ጠቅጥቀው ከጫኑን በኋላ ዝም ብለው ቆሙ:: ስልችት የሚል ነገር ነው:: በዛ ላይ ሰውነቴ ተርገደገደ..ህመም ተሰማኝ:: ጥብቅብቅ ብለን ላንላቀቅ የተጣበቅን እንመስላለን:: አብረውን የተጫኑት ሶማሊያዊያን በጣም ጥቂት ናቸው:: ከነዛ ውስጥ ሴቶቹ አነስተኛ ቁጥር አላቸው:: ከአስር የሚበልጡ አይመስለኝም:: ሀያ የሚሆኑ ወንዶች አሉ:: የኢትዮጵያዊያን ቁጥር ግን ከዘጠና በላይ ነው:: በተለይ የወሎ፣ የአርሲ፣ የሐረር ልጆች፣



ይበዛሉ:: ገበሬው እየተሰደደ ነው:: ሶማሊያዊያኑ ስስ ፌስታል ያድሉን ጀመር:: አብዛኛው የባህሩን ውሀ ስለጠጣ ለማስመለስ ቅርብ ሆነ:: ወዲያው ፌስታሉን ጥቅም ላይ አዋሉት:: እነሱን እያየሁ እኔም ይጓጉጠኝ ጀመር:: «ጅብሪል የት ይሆን? እግሩን የታመመው ልጅስ? በሀሳቤ ፈለኳቸው:: በአይኔማ እንዳልፈልጋቸው ሶማሌዎቹ ባለጀልባዎች ባትሪያቸውን አጥፍተው ወርደው እራታቸውን መብላት ጀምረዋል::